ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

**አዲስ አበባ**

**ጥቅምት 2014 ዓ.ም**

## ይዘት


1. ደርሞ /Executive Summary/ .... 4
2. መግቢያ .... 5
3. ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ .... 5
   3.1. የአነስተኛ ይዞታ አዝዕርት ልማት .... 5
   3.2. የመካከለኛ እና ሰፋፊ ሰብል ልማት ኢንቨስትመንት .... 6
   3.3. አነስተኛ ሆርቲካልቸር ልማት .... 6
   3.4. የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት .... 7
   3.5. የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማሳደግ .... 7
   3.6. የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማጠናከር .... 8
   3.7. የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና .... 9
   3.8. የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋት፣ .... 10
   3.9. የእፀዋት ግብዓቶችና ምርቶች ጤንነት፣ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ .... 11
   3.10. የምርጥ ዘር ጥራት፣ ቁጥጥርን ማሳደግ፤ .... 11
4. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማትን ማሳደግ .... 12
   4.1. የእንስሳት ምርት .... 12
   4.2. መኖ ልማት .... 13
   4.3. ዝርያ ማሻሻል .... 13
   4.4. እንስሳት ጤና .... 14
   4.5. የኤክስፖርት ቄራዎች ኢንስፔክሽንና ሰርቴፊኬሽን አገልግሎት .... 14
5. የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት .... 15
   5.1. አፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት .... 15
   5.2. የግብዓት ግዥ ፋይናንስ አቅርቦት .... 15
   5.3. የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት .... 16
6. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም .... 17
   6.1. የተፋሰስ ልማት .... 17
   6.2. የአፈር ለምነት ማሻሻል .... 18
   6.3. የአፈር ሀብት መረጃና ካርታ ዝግጅት .... 19
   6.4. አነስተኛ መስኖ ልማት .... 19
   6.5. የመሬት አስተዳርና አጠቃቀም .... 19
   6.6. የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ሥራዎች .... 20

7. የግብርና ምርምር ........ 21
8. ህብረት ስራ ማህበራት ........ 27
9. ግብርና ትራንስፎርሜሽን ........ 30
10. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ........ 32
10.1. የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ........ 32
10.2. የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ........ 33
10.3. የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ........ 34
10.4. ምግብና ስርዓተ ምግብ ........ 35
10.5. ኤች አይቪ ኤድስ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ........ 37
11. የኦዲት ግኝት ........ 45
12. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ ........ 45
13. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 45
14. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ........ 46
15. ማጠቃለያ ........ 55
16. አባሪ ፡ የቁልፍ ውጤት አመልካቾች ዝርዝር አፈፃፀም ........ 57

## 1. ደርሞ /Executive Summary/

የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ  በመኸር ከታቀደው 13.23 ሚሊን ሄ/ር መሬት ለመሸፈን ታቅዶ 13.13 ሚሊየን ሄ/ር(99.23) መሬት በዘር መሸፈን ሲቻል፤  በመስኖ ስንዴ ልማት 400,000 ሄ/ር ለማልማት በዕቅድ ተይዞ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ አትክልትና ፍራፍሬ 459 ሺ ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 408.1 ሺ ሄ/ር ማሳ በማልማት የእቅዱን 89% ማልማት ተችሏል፡፡ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን የ2013 የበልግ የአትክልትና ስራ ስር ምርት ግምት 37.5 ሚሊየን ኩ/ል እንደተገኘ ያሳያል፡፡

በባለሀብት እርሻ 1,171,327 ሄ/ር መሬት በማልማት 25,757,617 ኩንታል ምርት እንዲመረት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ በዚሁ መሰረት በመጀመሪያው ሩብ አመት ከ7 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ህ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሶማሌ) ወደ ስራ በገቡ 3,339 ባለሀብቶች 641,892 ሄ/ር በዘር ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን  አፈፃፀሙ 54.8% ነው፡፡

በ30,123 ሄ/ር ላይ የተከሰተውን የበረሃ አንበጣ የመከላከል ሥራ የተከናወነ ሲሆን 325 ሄ/ር በሰው ሃይል በሚታዘሉና በተሽከርካሪ በሚጠመዱ መርጫ መሳሪያና 6,497 ሄ/ር በአውሮፕላን በድምሩ በ6,822 ሄ/ር ላይ በኩብኩባ (hopper)፣ በማደግ ላይ ያለ (Immature) እና ያደገ (mature) የዕድገት ደረጃ ያላቸው ላይ መከላከል ተሰርቷል፡፡ ለመከላከሉም ሥራም 6,652.5 ሊትር ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሩብ ዓመቱ 2076.6 ሚሊየን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 2026 ሊ/ር ወተት ለማግኘት ተችሏል፡፡ የሥጋ ምርትን ለማሳደግ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየልና ከግመል የሥጋ ምርት አጠቃላይ የሥጋ ምርት 118.3 ሺህ ቶን ለማግኘት ታቅዶ 139.5 ሺህ ቶን የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙም 118 በመቶ ሲሆን ከዓመት ዕቅዱ 28 በመቶ ተከናውኗል፡፡ የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘ እቅድ 7.6 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 15 ሺህ ቶን ተመርቷል ይህም የእቅዱ +100 በመቶ የተከናወነ ሲሆን በተመሳሳይ 325.47 ሚሊዮን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 343 ሚሊዮን እንቁላል ተመርቷል ይህም የእቅዱን +100 በመቶ ለማምረት ተችሏል፡፡

ለ2014/15 ምርት ዘመን 2,032,770.95 ሜ/ቶን የማዳበሪያ ፍላጎት ከክልሎች መሰበሳብ ተችሏል:: በተሰበሰበው ፍላጎት መሰረት 2,032,770.95 ሜ/ቶን የተለያዩ የአፈር ማዳበሪያ በግዥ ለማቅረብ የጨረታ ሰነድ እንድዛጋጅ በማድረግ የኢግሥኮ ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጥቷል፡፡ ለመስኖ ጥቅም ላይ የሚውል በሩብ አመቱ  100,000.00 ሜ/ቶን ዩሪያ ግዥ ተፈፅሟል፡፡

በሩብ ዓመቱ 74,700.36 ቶን የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት በመላክ 245.70 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 88,920.66 ቶን (ከዕቅዱ 119%) በመላክ 333.5 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር (ከዕቅዱ 136%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 32,031.71 ቶን (56.31%) በገቢ ደግሞ 144.49 ሚሊዬን ዶላር (76.45%) ጭማሪ ተመዝግቧል፡፡ ለሆርቲካልቸር አምራች ኩባንያዎች የተቀናጀ ድጋፍ በማድረግ የኤክስፖርት ምርት መጠንና ገቢ ከማሳደግ አንጻር በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 67,452 ቶን የሆርቲካልቸር ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 83,403.41 ቶን ምርት ወደ ውጭ መላክ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር 123.65 በመቶ አፈጻጸም የሚያሳይ ሲሆን ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ38.17 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

## 2. መግቢያ

የ2014 ዓመታዊ ዕቅድ የዘርፉን ቁልፍ የውጤት መስኮችና ውጤቶችን ለማሳካት የሚያስችሉ የትግበራ መስኮችን መሰረት በማድረግና ግልፅ ዒላማዎችን በማስቀመጥ ዒላማዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በማካተት እንዲዘጋጅ በማድረግና በዕቅዱ ላይ የሚመለከታቸውን የፌደራልና የክልል ፈፃሚ አካላት ጋር መግባባት በመድረስ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪው ሩብ ዓመት አፈፃፀም በቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ሪፖርቱ የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም በዋና ዋና አመልካቾች፣ ፕሮግራም በጀት አፈፃፀም፣ የኦዲት ግኝት አፈፃፀም፣ የተቋማዊ ለውጥና አገልግሎት አሰጣጥ እና ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍን አካቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

## 3. ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

### 3.1. የአነስተኛ ይዞታ አዝዕርት ልማት

በምርት ዘመኑ 13,238,699.99 ሄ/ር መሬት በተገቢው ድግግሞሽ ታርሶ በዘር እንዲሸፈን ለማድረግ ታቅዶ እስከዚህ ሩብ ዓመት ድረስ 13,137,284.40 ሄ/ር መሬት (99.23 በመቶ) ከዚህም ውስጥ 2,044,934 ሄ/ር (80.29 በመቶ) በዘመናዊ የእርሻ ትራክተር ታርሶና በአግባቡ ተዘጋጅቶ ፣ 12,772,904 ሄ/ር (96.48 በመቶ) መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡ እስካሁን በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥም 4,739,837 በክላስተር (ኩታ ገጠም እርሻ ዘዴ የለማ መሆኑን ከክልሎች የተገኘ የሰብል

ልማት የመኸር እርሻ አፈፃፀም ሪፖርት ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን የ2013 የበልግ እህል ሰብል ምርት ግምት 14.7 ሚሊየን ኩ/ል እንደተገኘ ያሳያል፡፡

በቀጣይ ምርት ዘመን ሊያጋጥም የሚችለውን የምርጥ ዘር ችግር ለመቅረፍ በምርት ዘመኑ 82,227 ሄ/ር መሬት ሄ/ር መሬት በማልማ ታቅዶ 47,786 (58.11 በመቶ) ማከናወን ተችሏል፡፡

በሩብ ዓመቱ ሚዲዎችንና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አ/አደሩ ምክረ ሀሳብ እንዲያገኝ ለማድረግ በተሰራው ስራ ከማሳ ዝግጅት እስከ አረም ቁጥጥር ባሉት ተግባራት በቴሌቪዥንና በሬዲዮ መልዕክቶች እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡ የአግሮ ሜትሮሎጂ ምክረ ሀሳብን በየ10 ቀኑና በወቅቱ ሳይስተጓጎል ለተጠቃሚው እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

### 3.2. የመካከለኛ እና ሰፋፊ ሰብል ልማት ኢንቨስትመንት

በበ2013/14 ምርት ዘመን በባለሀብቶች እርሻ 1,171,327 ሄ/ር መሬት በማልማት 25,757,617 ኩንታል ምርት እንዲመረት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ በዚሁ መሰረት በመጀመሪያው ሩብ አመት ከ7 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ህ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሶማሌ) ወደ ስራ በገቡ 3,339 ባለሀብቶች በዘር የተሸፈነ ደግሞ 641,892 ሄ/ር ሲሆን አፈፃፀሙ 54.8% ነው፡፡

ለሶስት ባለሀብቶች (ጋምቤላ 2፣ አፋር 1) ከየክልሉ ለእርሻ ኢንቨስትመንት ከተረከቡት 4,700 ሄ/ር መሬት በበልግና በመኸር የተመረተው ምርት 54,450 ኩ/ል (ሰሊጥ 10,000 ኩ/ል፣ ማሾ 17,000 ኩ/ል፣ አኩሪ አተር 16,000 ኩ/ል፣ ቦለቄ 11,450ኩ/ል) የገበያ ሁኔታ እንደመቻቸችላቸው ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በቀጣይ በደበብ ኦሞ፣ቤንቺሸኮ፣ ካፋ እና ምዕ/ኦሞ ዞኖች ለአዳዲስ ባለሃብቶች መተላለፍ የሚችል በድምሩ 131,043ሄ/ር መሬት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 3.3. አነስተኛ ሆርቲካልቸር ልማት

በ2014 በጀት ዓመት በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ግብ ተጥሎ እየተሰራ የመኸር አትክልትና ፍራፍሬ ልማትን በተመለከተ 459 ሺ ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 408.1 ሺ ሄ/ር ማሳ በማልማት የእቅዱን 89% ማልማት ተችሏል፡፡ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን የ2013 የበልግ የአትክልትና ስራ ስር ምርት ግምት 37.5 ሚሊየን ኩ/ል እንደተገኘ ያሳያል፡፡

በሀገር ደረጃ የአረንጓዴ አሻራ ልማትን ለማጠናከር በተደረገው ርብርብ በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ በቁጥር 83,554,458 ችግኝ በማዘጋጀት 69,910,015 (83.67 በመቶ) የፍራፍሬ ችግኝ ተከላ

የተከናወነ ሲሆን 60,664 ሄ/ር መሬት በፍራፍሬ ተሸፍኗል፡፡ ይህም ከተዘጋጀው ችግኝ 83.667% መተከሉን ያመላክታል፡፡ተከላ ተካሂዷል፡፡

### 3.4. የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት

በ2013/14 ምርት ዘመን የቡና ማሣ ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በመፈፀም ለምርት የደረሰውን 931,728 ሄ/ር (በአርሶአደር 818,611 እናአልሚ ባለሃብት 113,117) የቡና ማሣ አማካይ ምርታማነቱን በሄ/ር 7.5 ኩ/ል ከነበረበት ወደ 7.6 ኩ/ል በማድረስ 708 ሺ ቶን ምርት ለማምረት ግብ የተያዘ ሲሆን ሀገራዊ የምርት ትመና ሪፖርት እስከአሁን ስላልወጣ አፈፃፀሙ በዚህ ሪፖርት ማካተት አልተቻለም፡፡

በ2013/14 ምርት ዘመን ምርት ከሚሰጠዉ የአልሚ ባለሀብቶች 2,760 ሄክታር ይዞታ ላይ  በዓመቱ ከታቀደዉ 10,732.1 ቶን፤ በሩብ ዓመቱ 2,683.03 ቶን የደረቀ ሻይ  ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,734.8 ቶን (65%) የደረቀ ሻይ  ምርት ተመርቷል፡፡ እንዲሁም በ2013/14 ምርት ዘመን ምርት ከሚሰጠዉ የአውት ግሮወርስ 501 ሄክታር ይዞታ ላይ  በዓመቱ ከታቀደዉ 1,217.43 ቶን፤ በሩብ ዓመቱ 304.4 ቶን የደረቀ ሻይ ምርት ለማምረት ታቅዶ 158.3 ቶን (52%) የደረቀ ሻይ  ምርት ተመርቷል፡፡

የቅመማ ቅመም ምርታማነት በማሳደግ ረገድ በ2014 በጀት ዓመት ዋና ትኩረት በተሰጣቸው ላይ በማተኮር በቅመማ ቅመም ክላስተር በታቀፉ እና ዳይቨርሲፋይ በሚያደርጉ አካባቢዎች 448,434 ሄ/ር መሬት የማሳ ሽፋን በማልማት እና ምርት መስጠት ከሚችለዉ 398,320 ሄ/ር ላይ የእንክብካቤ ስራዎችን በማከናወን በዋና ዋና የቅመማ ቅመም ምርቶች በ2013 የምርት ዘመን ከተደረሰበት 644.3 ሺ.ህ ቶን ወደ 705.14 ሺ.ህ ለማድረስ ታቅዶ በተለያዩ ዋና ዋና ቅመማ ቅመሞች 370,398 ሄ/ር (93%) በመልማት ላይ ይገኛል፡፡

### 3.5. የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማሳደግ

የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም በማሳደግ የሰብል፤የእንስሳትና ምርትና ምርታማነት/ጥራትን ለማሳደግ፡፡ በተመረጡ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጠት ስራ የልቀት ማዕከል እንዲሆኑ ለማስቻል እየተሰራ ይገኛል፡፡ በሀገር ደረጃ ለሚቋቋሙ የሜካናይዜሽን ማእከላት መካከል በበደቡብ ክልል፣ ቸሃ ወረዳ የቦታ መረጣ፣ ማሽነሪ ማሰራጨት፣ ስልጠና መስጠት እና ወደ ስራ የማስገባት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ለወረዳው እንድ ትራክተር ከማረሻ፣ መከስካሻ፣ ካልቲቬተር ጋር እና በትራክተር የሚሰራ መውቂያ ማሽን እና በቆሎ መፈልፈያ ማሽን እና የትራክተር ጋሪ ለወረዳው ግብርና ጽ/ቤት የማስርከብ ስራ ተካሄዷል፡፡ እንዲሁም በማሽነሪ አጠቃቀም፣ ጥገናና አስተዳደር እና በንግድ ስራ

እና ፋይናንስ አስተዳደር ላይ ለ17 ሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡የተለያዩ የፀ-ረሰብል ኬሚካል መርጫዎችን ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደሩ ለማስተዋወቅ በርካታ ተግባራት እየተከናወነ ሲሆን ከዚህ ስራ ጋር ተየይዞ የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫዎችን ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደሩ ለማስተዋወቅ በቁጥር 60 የነፍስ ወከፍ መርጫ እና 3 ባለ ሞተር የኬሚካል መርጫ መሳሪያ የተሻለ ጥራት ያላቸውን ለአርሶ/አርብቶ አደር ለማስተዋወቅ በግ/ቴ/ሞ/ማሰልጠኛ እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ተሰራጭተዋል፡፡በሩብ ዓመት በቁጥር 81000 የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫዎችን ቴክኖሎጂ የጥራት ፍተሻ ቁጥጥር በማድረግ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫዎችን ወደ ሃገር ውስጥ ገብተው ስራ ላይ እንዲውሉ በቴክኒካል ስራ በመደገፍ ቁጥሩ ከፍ እንዲል ለማስቻል በሩብ ዓመቱ ለ45 የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫ አስመጪ ባለጉዳዮች የቴክኒክ ምርመራ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ ለ43 (95 በመቶ) አስመጪዎች ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

### 3.6. የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማጠናከር

በበጀት ዓመቱ የኤክስቴንሽን ስርዓቱን አስቻይ ብቃት በመፍጠር፤ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ አካላት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ዓይነትና የኤክስቴንሽን አሰራር ስልቶች በብዝሃነት በመጠቀም፤ የግብርና ልማት አካላትን ግንኙነት በማጠናከር እና የኤክስቴንሽን ዕቅድ፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን ቁጥር በማሳደግ አሁን ካለበት 11,195,000 ወደ 11,982,000 ከፍ ለማድረግ በርካታ ተግባራት ታቅደው በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለግብርና ኤክስቴንሽን ሰርዓት ማዋል እንዲቻል በሀገር አቀፍ ደረጃ በዲጂታል ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ልየታ በማከናወን የክልል የኤክስቴንሽን ዳይሬክተሮች፣ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት መሰረት ያደረገ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች፣በሴክተሩ ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በድምሩ 60 (7 ሴቶች) የተሳተፉበት አንድ ሀገር አቀፍ ዲጂታል ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ፎረም ተመስርቷል፤ ውይይትም በማካሄድ ለቀጣይ የሚሰሩ ሥራዎች ዕቅድ ተቀምጧል፡፡ የዲጂታል ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ፍኖተ ካርታ አካላትን በማሳተፍ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡

በአርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶአደሮች ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ላይ በክልሎች በመገኘት የተካሄደው የዳሰሳ ጥናት ውጤት በዚህ በሩብ ዓመት ሪፖርቱ ተደራጅቶ ተጠናቋል፡፡

በበጀት ዓመቱ የአሰራር መመሪያዎችና ማንዋሎች (የልማት ጣቢያ ባለሙያዎች የማበረታቻ መመሪያ፣ የልማት አካላት የአፈጻጸም መመሪያ፣ የአርሶና አርብቶ አደር ማሰልኛ ማእከላት

መመሪያ፣ የምርጥ ተሞክሮ መመሪያ፣ የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ሥርዓት፣ የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር የመስክ ትምህርት መመሪያ፣ የአሰልጣኞች ሥልጠና መመሪያ፣ የክትትልና ግምገማ መመሪያ) አዘጋጅቶና ያሉትንም ከልሶ በማሳተም ለሁሉም ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ለማሰራጨት እቅድ የተያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ 3 ለማከናወን ተይዞ 4ቱ (የአርሶና አርብቶ አደር ማሰልኛ ማእከላት መመሪያ፣የልማት አካላት የአፈጻጸም መመሪያ፣የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ሥርዓት፣ እና የአርብቶ አደር የማሳ ሥራ ቦታ ት/ቤት (A/PFS ተከልሰው ተጠናቀዋል፤) ተጠናቀዋል፡፡

### 3.7. የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና

የኮቪድ 19 ፕሮቶኮል ታሳቢ ባደረገ መልኩ በ10 የሥልጠና መስኮች 10193 ወንድ 6404 ሴት 3789 (ሰብል ልማት፣ እንስሳት እርባታ፣ እንስሳት ጤና፣ ተፈጥሮ ሀብት፣ አነስተኛ መስኖ፣ ግብርና ሜካናይዜሽን (ኦፕሬሽን እና ሜይንቴይናንስ) ፣ ኀ/ሥራ (ሥራ አመራር፣ ሂሳብ አያያዝ እና ግብይት እዲሁም መሬት አስተዳደር) ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተሰሩ ያሉ ሲሆን የመማር ማስተማር ስራዉ ተማሪዎችና መምህራን የእረፍት ጊዜያቸዉን ጨርሰዉ በመግባት ላይ ያሉ በመሆኑ ትምህርትና ስልጠናዉ አልተጀመረም፡

ለትምህርትና ሥልጠናው መጀመር የተከናወኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በተመለከተ፡ የተማሪ ቀለብ ግዥ፣የመማሪያ ክፍሎች እና ዶርሚተሪ ግድግዳና ኮርኒስ ቀለም የመቀባት ሥራ፣የኤሌክትሪክ መስመር ጥገና፤ መጸዳጃ ቤቶችን፣ ሻወር ቤቶችን፣ የነጭ ሰሌዳ የመግጠም ፣እንዲሁም ሌሎች አገልግሎትና ስልጠና መስጫ ቦታዎች ጥገና ስራዎች ናቸው፣ተማሪችን ማሰልጠኛ ሞጁሎች የማዘጋጀት፣ሰርቶ ማሳያዎች፤ ወርክሾፖች፣ ላብራቶሪዎች የማጠናከርና የማደራጀት ስራዎች በመስራት ለመማር ማስተማር፤ ለተግባር ልምምድና ለቴክኖሎጂ ብዜት ስራዎች ዝግጁ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን መምህራን ከነበሩበት እረፍት ላይ ወደ ስራ ቦታቸዉ ተመልሰዉ ለመማር ማስተማር ስራዉ እራሳቸዉን ዝግጁ አድርገዉ እንዲጠብቁ ተደርጓል ፡፡

ሀገር አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 4 ተመዛኖችን የብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲወስዱ ለማድረግ በቂ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ የሰልጣኞቹን መግባት በመጠባበቅ የሚገኙ ሲሆን ሰልጣኞችን ወደ ሀገር አቀፍ ምዘና ከመግባታቸዉ በፊት የተለያዩ የማጠናከሪያ ትምህርት እና የኮምፒዉተር ክህሎት የማነቃቂያ ስልጠና እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

### 3.8. የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋት፣

የድንበር ዘለል ተዛማች ተባዮች አሰሳና መከላከል ቅልጥፍናና ጥራት በማሳደግ የምርት ብክነት ለመቀነስ እና ለምርታማነት ዕድገት አስተዋፅኦ ለማድረግ በሩብ ዓመቱ በርካታ ተግባራት ተከናውኗል፡፡

በዚሁ መሰረት በ60 ወረዳዎች ላይ የበረሃ አንበጣ አሰሳና መከላከል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ50 ወረዳዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ በ4 ክልሎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር (አማራ 12፣ አፋር 17፣ ኦሮሚያ 2፣ ሶማሌ 18 እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 1 ክላስተር) በ2,209,241 ሄ/ር ላይ የአሰሳ ሥራ ተሰርቶ በ30,123 ሄ/ር ላይ የተከሰተውን የበረሃ አንበጣ የመከላከል ሥራ የተከናወነ ሲሆን 325 ሄ/ር በሰው ሃይል በሚታዘሉና በተሸከርካሪ በሚጠመዱ መርጫ መሳሪያና 6,497 ሄ/ር በአውሮፕላን በድምሩ በ6,822 ሄ/ር ላይ በኩብኩባ (hopper)፣ በማደግ ላይ ያለ (Immature) እና ያደገ (mature) የዕድገት ደረጃ ያላቸው ላይ መከላከል ተሰርቷል፡፡ ለመከላከሉም ሥራም 6,652.5 ሊትር ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በ30 ወረዳዎች የአዲሱ መጤ ተምች አሰሳና መከላከል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ39 ወረዳዎች ላይ (አማራ 13፣ ኦሮሚያ 18 እና ደቡብ 8) የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ6 ክልሎች (በደቡብ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ) እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከተዘራው 1,786,375 ሄ/ር ውስጥ 508,023 ሄ/ር ላይ የተከሰተ ሲሆን በባህላዊ 305,683 ሄ/ር በጸረ-ተባይ ኬሚካል 103,889 ሄ/ር በድምሩ 409,572 ሄ/ር የመከላከል ስራ በክልሎች ተሰርቷል፡፡ ጥቅም ላይ የዋለ ፀረ- ተባይ ኬሚካል 109,150 ሊትር ነው፡፡

የግሪሳ ወፍ ክትትል፤ አሰሳና የመከላከል ስራ በ10 የወፍ ማደሪያ ስፍራ ለማከናወን ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን በ7 ወረዳዎች (ዝዋይ ዱግዳ፣ ሉሜ፣ አዳሚ ቱሉ፣ ቦራ፣ ሊበን ጩቋላ፣አዳማ እና ቦሰት) 20 ሚሊዮን ወፍ እና በአሪሲ ዞን በአራት ወረዳዎች (ዶዶታ፣ሲሬ፣ጀጁ እና መርቲ) 6 ሚሊዮን በድምሩ 26 ሚሊዮን የግሪሳ ወፍ በ14 የመማደሪያ ቦታዎች ላይ ከ10 ቀናት በፊት ተከስቶ በሰብል ላይ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ አርሶ አደሩ በባህላዊ ዘዴ ሰብሉን ከወፍ ጥቃት የመጠበቅ ልምዱ ዝቅተኛ በመሆኑ እና በዚህ በ10 ቀናት ውስጥ ወፉ ያደረሰው ጉዳት 130,000 ኩ/ል ወይም 13,000 ቶን የሰብል ውድመት ደርሷል፡፡ ለዚህም ሰብል መጥፋት ከፍተኛውን ድርሻ የሚውስደው በምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከል ድርጅት (DLCO-EA) ከኬኒያ ፓይሌቶችን ማስመጣት አለመቻሉ ነው፡፡

በሩብ ዓመቱ 200,000 ሊትር ፀረ - ተባይ ከአዳሚቱሉ የፀረ - ተባይ ማዘጋጃ ፋብሪካ ለመግዛት ታቅዶ 55,000 ሊትር 50% ኢ.ሲ ማላተሂን፣ 5000 ሊትር 60% ኢ.ሲ ዲያዚኖን እና 28,000 ሊትር ማላታይን 95% ዩ.ኤል.ቪ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተገዛ ሲሆን ከFAO 50 ሊትር 92.5 ዩ.ኤል.ቪ ኬሚካል ለወረርሽኝ ተባዮች ተገዝቶ ገቢ ተደርጓል፡፡ ኢትዮጵያ አባል ከሆነችባቸው 4 ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓመታዊ መዋጮን ለመክፈል በዕቅድ 1 ተይዞ 1 ተከናውኗል፡፡

### 3.9. የእፀዋት ግብዓቶችና ምርቶች ጤንነት፣ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

ወደ ዉጪ ሀገር ለሚላክ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር በሚካሄድባቸዉ ቁሳቁሶችን በላብራቶሪ በመታገዝ ፍተሻ በማካሄድ የዕፅዋት ምርት የጤናና ጥራት በማረጋገጥ 157,500 ቶን ለመላክ ታቅዶ 124,083 ቶን (79%) ምርት ወደ ተለያዩ ሃገራት እንዲላክ ተደርጓል፡፡ ምርት በብዛት በሚላክባቸው ጥቂት አካባቢዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት አፈፃፀሙ በተጠበቀው ልክ አልተከናወነም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ውጪ ለሚወጣ የዕፅዋት ምርት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት መስጠት በሩብ ዓመቱ በቁጥር 9,000 ለመስጠት ታቅዶ 11,017 (122.4%) ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ውጪ ለሚላክ 63,000 ቶን የዕፅዋት ምርት የማጠንት /Fumigation/ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 56,905 (90%) ተከናውኗል፡፡

ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች፣ የግብርና ግብዓቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች በ37,500 ቶን ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ በመስራት እና መስፈርቱን አሟልተው እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ በ16,356 ቶን ላይ ምርመራ በማካሄድ ጤንነታቸውንና ጥራታቸውን በማረጋገጥ ወደ ሀገር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይህ የእቅዱ 44 ከመቶ ሲሆን አፈጻጸሙ ያነሰው አገልግሎቱ ተገልጋይ ተኮር በመሆኑ አገልግሎት የሚፈልጉ ተገልጋዮች በታቀደው ልክ ባለመቅረባቸው ነው፡፡

### 3.10. የምርጥ ዘር ጥራት፣ ቁጥጥርን ማሳደግ፣

የዝርያ ምዝገባና የዘር ቁጥጥር ቅልጥፍናና ጥራትን ለማሳደግ፣ በዚህ ሩብ ዓመት ከተለያዩ ከተለያዩ የምርምር ተቋሞች፣ ዩንቨርሲቲዎች እና የግል ኩባንያዎች የቀረቡ 10 ዕጩ ዝርያዎችን በሩብ ዓመቱ ውስጥ በመስክ ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 12 ዝርያዎች (120%) በመስክ ተገምግመዋል፡፡

የአትክልት ዝርያዎችን ከውጪ በማሰገባትና ለአርሶአደሩ ለማቅረብ ጥያቄ ለሚያቀርብ ለ2የአትክልት ዘር አስመጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ (›100%) ዘር አስመጪ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡

80 በተለያዩ የአትክልትና የሰብል ናሙናዎች ላይ ናሙና በመውሰድ በላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ዉጤት ለማሳወቅ ታቅዶ በ 27 (33%) የተለያዩ የአትክልት የሰብል ናሙናዎች ላይ

የጥራት ፍተሻ ተካሂዶ ውጤቱ አገልግሎቱን ለማግኘት ጥያቄ ላቀረቡ ድርጅቶች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

## 4. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማትን ማሳደግ

### 4.1. የእንስሳት ምርት

አጠቃላይ የወተት ምርት 2076.6 ሚሊየን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 2026 ሊ/ር ወተት ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም አፈጻጸሙ 98 ከመቶ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከዳልጋ ከብት ይገኛል ተብሎ የታቀደዉ የወተት ምርት 1695.5 ሚሊየን ሊትር ሲሆን  የተገኘ ወተት ምርት 1773 ሚ/ን ሊትር (+100%) ነዉ፡፡ ከግመል 332.7 ሚ/ን ሊትር ወተት ለማምረት ታቅዶ  206 ሚ/ን ሊ/ር (62%) የወተት ምርት ተገኝቷል፡፡ ከቆላማዉ ስነ ምህዳር የፍየል የወተት ምርት 48.4 ሚ/ን ሊትር ለመድረስ ታቅዶ 47 ሚ/ን ሊ/ር የተመረተ ሲሆን አፈፃጸሙም 97 በመቶ ደርሷል፡፡

አጠቃላይ የሥጋ ምርት 118.3 ሺህ ቶን ለማግኘት ታቅዶ 139.5 ሺህ ቶን የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙም 118 በመቶ ሲሆን ከዓመት ዕቅዱ 28 በመቶ ተከናውኗል፣ ይህም ዓመታዊ ግባችንን በተቀመጠው ጊዜ ልናሳካ እንደምንችል የሚያመላክት አፈጻጸም ሆኗል፡፡የቆዳና ሌጦ ምርትን ማሳደግ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየል የቆዳና ሌጦ ምርት 3.85 ሚሊየን ለማግኘት ታቅዶ 4.26 ሚሊየን የተገኘ 110 በመቶ ሲሆን ከዓመት ዕቅዱ 26 በመቶ ተከናውኗል፡፡

የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘ እቅድ 7.6 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 15 ሺህ ቶን ተመርቷል ይህም የእቅዱ +100 በመቶ የተከናወነ ሲሆን በተመሳሳይ 325.47 ሚሊዮን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 343 ሚሊዮን እንቁላል ተመርቷል ይህም የእቅዱን +100 በመቶ ለማምረት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ 3 ሚሊዮን ጫጩት ለማሰራጨት ታቅዶ 17 ሚሊዮን ጫጩቶች ተሰራጭተዋል ይህም የእቅዱ 57 በመቶ ተከናውኗል፡፡ ከሁሉም የውሃ አካላት የዓሳ ምርት 15 ሺ ቶን የሚሸፍን ሲሆን የተመረተው 11.25 ሺ ቶን ሲሆን የዕቅዱን 75 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡

የማርና ሐር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘ እቅድ 6.90 ሺህ ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ 7.2 ሺህ ቶን ማር ተመርቷል ይህም የእቅዱ 104 በመቶ ተከናውኗል፡፡በተመሳሳይ በ2014 በጀት ዓመት 0.45 ሺህ ቶን ሰም ለማምረት ታቅዶ 0.5 ሺህ ቶን ተመርቷል ይህም የእቅዱ 100 በመቶ ተከናውኗል፡፡በሩብ ዓመቱ የሐር ኩኩባ ምርት የታቀደ ዕቅድ ባይኖርም 0.4 ቶን ኩኩባ ለማምራት ተችሏል፡፡

### 4.2. መኖ ልማት

ከሁሉም የእንስሳት መኖ ምንጮች (የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት፣ በመስኖ የለማ መሬት፣ በጓሮ መኖ ልማት፣ በወል ግጦሽ መሬት የለማ መኖ፣ ወዘተ) 20.3 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 19.9 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 97.8 በመቶ ነው፡፡

የተለያዩ የተፈጥሮ ግጦሽ የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመተግበር እና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ 4 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 6.7 ሚ/ን ቶን በማምረት ከእቅድ በላይ ተፈፅመል፡፡ ለዚህም በዚህ ዓመት በአርብቶ አደር አካባቢ የመኸር የዝናብ ስርጭት የነበረ በመኖሩ የግጦሽ ልማቱን የተሻለ አድርጎታል፡፡

የሰብል ተረፈ ምርትን በተገቢዉ በማሰባሰብ ለመጠቀም እንዲቻል 3 ሚ/ን ቶን በአሰባሰብ በተገቢዉ በማከማቸት ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ 2.5 ሚ/ን ቶን የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ 83 በመቶ ነው፡፡ የኢንዳስትሪ (ስኳርና ሌሎች) ተረፈ ምርቶችን 1.5 ሚ/ን ቶን በማምረት ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ 1.1 ሚ/ን ቶን ሲሆን 73.3 ተፈጽሟል።

የወል ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን የተለያዩ ማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመጠቀምና ድጋፍ በማድረግ 7.4 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 5.4 ሚ/ን ቶን የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙ 73 በመቶ ነው፡፡ ከግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን በማሻሻል 440 ሺ/ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 910 ሺህ ቶን በማምረት ከእቅድ በላይ ተፈፅመዋል፡፡ ለአፈፃፀሙ ከፍ ማለት በኦሮሚያ ክልል ላይ በግጦሽ መሬት ማልማት ላይ የተሻለ ስራ የተሰራ መሆኑ በመሆኑ ነዉ፡፡

### 4.3. ዝርያ ማሻሻል

በሩብ ዓመቱ ዉስጥ 350,000 ዶዝ አባለዘር ለማምረት ታቅዶ 345,688 ዶዝ የዕቅዱን 98.8% ዶዝ አባለዘር እንዲመረት ተደርጓል፡፡ ከተመረተው ውስጥ 244,780 ዶዝ በኢንስቲትዩቱ የተመረተ ሲሆን ቀሪዉ 100,908 ዶዝ በሦስቱ የክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት ማለትም በነቀምት 40,601 በባህርዳር 32,417 በሀዋሳ እና 27,890 ዶዝ የተመረተ ነው፡፡

የአባለዘር ሥርጭትን በተመለከተ በአንደኛ ሩብ ዓመት በክልሎችና በኢንስቲትዩቱ 300,000 ዶዝ አባለዘር ለማሰራጨት ታቅዶ 198,870 ዶዝ አባለዘር የዕቅዱን 66.29% ተከናውኗል፡፡ ሥርጭቱ ያነሰበት ምክንያት ሩብ ዓመቱ በአብዛኛው ለክልሎች የዝግጅት ምዕራፍ በመሆኑና አብዛኞቹ ክልሎች የድቀላን ሥራ በመደበኛ ከሚሠሩት ውጪ በሲንክሮናይዜሽን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እንስሳት ለማዳቀል ከዚህ ወር ጀምሮ ለመተግበር እየተዘጋጁበት ስለሆነ አፈጻጸሙ በቀጣይ ወራት ከፍተኛ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህ ስርጭት በክልሎች እና በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨዉን

ያካተተ ሲሆን 155,965 ዶዝ በኢንስቲትዩቱ ሲሠራጭ ቀሪዉ 42,905 ዶዝ በአራቱ የክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት የተሠራጨ ነው፡፡

ፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትን በተመለከተ በአንደኛ ሩብ ዓመት ዉስጥ በክልሎች በኢንስቲትዩ ዉስጥ 96,250 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለማምረት ታቅዶ 77,055 ሊትር የዕቅዱን 80% ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን እንዲመረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ 14,082 ሊትር ቀሪው 62,973 ሊትር በአራቱ የክልሎች ፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከላት የተመረተ ነዉ፡፡ በሩብ ዓመቱ ዉስጥ 86,500 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለማሠራጨት ታቅዶ 52,525 ሊትር የዕቅዱን 60.7% ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ 42,666 ሊትር በክልሎች የተሠራጨ ሲሆን ቀሪዉ 9,859 ሊትር ደግሞ በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨ ነው ፡፡

### 4.4. እንስሳት ጤና

የክትባት ምርትን በተመለከተ 87.56 ሚሊዮን ዶዝ የተለያዩ ክትባቶችን ለማምረት ታቅዶ 70.11 ሚሊዮን ዶዝ በማምረት የዕቅዱን 80% ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም የቀነሰበት ምክንያት የግብዓት ዕጥረትና የማምረቻ መሳሪያ ብልሽት በመከሰቱ  ነው፡፡ የምርት ዕቅድ ክንውን ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን በ6.52 ሚ/ዶዝ /8.51%/ ዝቅ ያለ አፈፃፀም ያሳያል፡፡ የክትባት አቅርቦት 79.19 ሚሊዮን ዶዝ የተለያዩ የእንስሳት ክትባቶችን በማቅረብ 54.07 ሚሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ 44.39 ሚሊዮን ዶዝ ክትባቶችን በማቅረብ 31.82 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱን 56% እና 58.85% በቅደም ተከተል መከናወኑን ያሳያል፡፡ አፈፃፀሙ የቀነሰበት ምክንያት በአንዳድ ክትባቶች ላይ የምርት ዕጥረት በመከሰቱ ነው፡፡ የእንስሳት መድሀኒት አቅርቦት 1.09 ሚ/ቦለስ መድኃኒት ለማምረት ታቅዶ 111,000 ቦላስ መድኃኒቶችን በማምረት የዕቅዱን 10% ማከናወን ተችሏል፡፡

### 4.5. የኤክስፖርት ቄራዎች ኢንስፔክሽንና ሰርቴፊኬሽን አገልግሎት

እንሰሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ 464,500 ለማካሄድ ታቅዶ 531,927 (114.51 በመቶ) እንሰሳት ለመመርመር ተችሏል፣በተመሳሳይ 459,500 እንሰሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 520,078 (113.183 በመቶ) እንሰሳት መመርመር ተችሏል፣በተጨማርም ለ 3875 ቶን ሥጋና 400 ቶን ተረፈ ሥጋ ምርት ወደ ውጪ ለመላክ ታቅዶ፣ 3714.92(95.86በመቶ) ቶን ሥጋና 345 (86.25 በመቶ) ቶን ተረፈ ሥጋ ወደ ውጪ ተልኳል፤እንድሁም 3000 የምግብ ደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 2241 (112 74.7) በመቶ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል፡፡

ወደ ውጭ ለሚላኩ 101030 የቁም እንስሳት የጤና ምርመራ አድርጎ አለም አቀፍ የጤና ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ 9 ሺ ቁም እንስሳት ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ተቀባይ ሀገር እንዲሄዱ ተደርጓል።

## 5. የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት

### 5.1. አፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት

በ2013/14 ምርት ዘመን 1,816,921.60 ሜ/ቶን የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ 1,630,828.70 ሜ/ቶን (89.76%) የቀረበ ሲሆን አጠቃላይ ከቀረበው ውስጥ በሩብ ዓመቱ 181,274.15 ሜ/ቶን ማቅረብ ተችሏል፡፡ በ2013/14 ምርት ዘመን 1,745,602.06 ሜ/ቶን የአፈር ማዳበሪያ ለማሰራጨት ታቅዶ 1,480,758.74 ሜ/ቶን (84.83%) ተሰራጨ ሲሆን አጠቃላይ ከተሰራጨው ውስጥ በሩብ ዓመቱ 454,000.00 ሜ/ቶን ለማሰራጨት ታቅዶ 469,588.73 ሜ/ቶን (103.43%) ተሰራጭቷል፡፡ ለ2014/15 ምርት ዘመን 2,032,770.95 ሜ/ቶን የማዳበሪያ ፍላጎት ከክልሎች መሰበሳብ ተችሏል:: በተሰበሰበው ፍላጎት መሰረት 2,032,770.95 ሜ/ቶን የተለያዩ የአፈር ማዳበሪያ በግዥ ለማቅረብ የጨረታ ሰነድ እንድዛጋጅ በማድረግ የኢግሥኮ ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጥቷል፡፡ ለመስኖ ጥቅም ላይ የሚውል በሩብ አመቱ 100,000.00 ሜ/ቶን ዩሪያ ግዥ ተፈፅሟል፡፡

በ2013/14 ም/ዘመን 329,060 ክ/ል የግብርና ኖራ ለማቅረብ ታቅዶ 153,240.00 ኩ/ል በማቅረብ 114,993.50 ኩ/ል ለአርሶ አደሩ የተሳራጨ ሲሆን በሩብ ዓመቱ 56,576.00 ኩ/ል የግብርና ኖራ ቀርቦ 18,389.00 ኩ/ል ለአርሶ አደሩ ተሳራጭቷል፡፡

በ2013/14 ምርት ዘመን 1200000 ኩ/ል የተለያዩ የዕፅዋት ምርጥ ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 932,886.7 (53.53%) በማቅረብ 883,030.60 ኩ/ል ከቀረበዉ (94.66%) ለአርሶ አደሮች ማሳራጨት የተቻለ ሲሆን በዚህ በሩብ ዓመቱ 404,483.50 ኩ/ል ማሳራጨት ተችሏል፡፡ ለ2014/15 ምርት ዘመን 1,634,898 ኩ/ል የተለያዩ የዕፅዋት ምርጥ ዘር ፍልጎት ከሁሉም ክልል በዚህ ሩብ በጀት ዓመት መሰበሳብ ተችሏል፡፡

### 5.2. የግብዓት ግዥ ፋይናንስ አቅርቦት

በ2013/14 ምርት ዘመን 37.3 ቢሊየን ብር የብድር ፍላጎት የቀረበ ሲሆን ለ2014/15 ምርት ዘመን 51.2 ቢሊየን ብር ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀርቦ 29.993 ቢሊየን ብር ወይም 950 ሚ/አሜሪካን ዶላር የግብዓት መግዣ ብድር መመቻቸት ተችሏል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ዉዝፍ ለመመለስ ከታቀደው 7,599,504,235.19 ብር ውስጥ በሩብ ዓመቱ 1,907,376,058.80 ብር ለመመለስ ታቅዶ 838,922,483.08 ብር (43.98 %) መመለስ ተችሏል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ከ2009/10 እስከ 2011/12 ምርት ዘመን ያልታመለሰ ውዝፍ የግብርና ብድር 3,904,509,288.01 ብር ለመመለስ ከታቀደው ውስጥ በሩብ ዓመት 987,931,265.73 ብር ለመመለስ ታቅዶ 47,215,774.90 ቢ/ብር (4.78%) መመለስ ተችሏል፡፡

### 5.3. የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት

የቡና ኤክስፖርት መጠንና ገቢ እንዲያድግ ከአምራች እስከ ገበያ መዳረሻ በማስተባበር፣ በመከታተል፣ በመደገፍና በመምራት በመጀመሪያ ሩብ ዓመት 70,880.90 ቶን ቡና ለመላክና 239.85 ሚሊየን ዩ.ኤስ ዶላር ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ 86,288.14 ቶን (122%) በመላክ 327.87 (137%) ሚሊዮን ዩ.ኤስ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን 32,845.09 ቶን (61.46%) እና በገቢ 143.08 (77.43%) ሚሊዮን ዩ.ኤስ ጭማሪ አሳይቷል፡ ፡ ለታየው ከፍተኛ ጭማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቡና ዋጋ መሻሻል፣ የተለያዩ የግብይት አማራጮችን ተግባራዊ በማድረግ የምርት አቅርቦቱ እንዲጨምር በመደረጉ፣ በዝቅተኛ ዋጋ ስሸጥ የነበረዉን ቡና ዝቅተኛ የዋጋ ተመን ተግባራዊ በማድረግና በመቆጣጠር ጠቅላላ ገቢ ማሻሻል መቻሉ እና በኤክስፖርት ሂደቱ ሲያጋጥሙ የነበሩ ማነቆዎችን ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገምና እልባት መሰጠቱ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው።

ሻይ በሩብ ዓመቱ 666.83 ቶን በመላክ 1.12 ሚሊየን ዩ.ኤስ ዶላር ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ 34.48ቶን (52%) በመላክ 0.63 (56%) ሚሊዮን ዩ.ኤስ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን -236.39 ቶን (40.7%) እና በገቢ -0.35 (35.4%) ሚሊዮን ዩ.ኤስ ዶላር ቅናሽ አሳይቷል፡፡

ቅ/ቅመም በሩብ ዓመቱ 3,152.63 ቶን በመላክ 4.73 ሚሊየን ዩ.ኤስ ዶላር ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ 2,289.04 ቶን (73%) በመላክ 5.01 (106%) ሚሊዮን ዩ.ኤስ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን -576.9 ቶን 20.13%) ቅናሽ እና በገቢ 1.76 (54.2%) ሚሊዮን ዩ.ኤስ ዶላር ጭማሪ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከሦስቱም ምርቶች በሩብ ዓመቱ 74,700.36 ቶን የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት በመላክ 245.70 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 88,920.66 ቶን (ከዕቅዱ 119%) በመላክ 333.5 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር (ከዕቅዱ 136%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 32,031.71 ቶን (56.31%) በገቢ ደግሞ 144.49 ሚሊዩን ዶላር (76.45%) ጭማሪ ተመዝግቧል፡፡

ለሆርቲካልቸር አምራች ኩባንያዎች የተቀናጀ ድጋፍ በማድረግ የኤክስፖርት ምርት መጠንና ገቢ ከማሳደግ አንጻር በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 67,452 ቶን የሆርቲካልቸር ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 83,403.41 ቶን ምርት ወደ ውጭ መላክ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር 123.65 በመቶ አፈጻጸም የሚያሳይ ሲሆን ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ38.17 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የሩብ ዓመቱ አፈጻጸም በምርት ዓይነት ሲታይ በአበባ 26,830፣ በአትክልት 29,261 እና በፍራፍሬ 11,361 ቶን ለመላክ ታቅዶ እንደ ቅደም ተከተላቸው 27,256.66፣ 47,246.73 እና 8,900.02 ቶን ምርት ለውጪ ገበያ የተላከ ሲሆን 101.59፣ 161.47 እና 78.34 በመቶ አፈጻጸም በቅደም ተከተል ተመዝግቧል፡፡

ወደ ውጭ ገበያ ከተላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ገቢን በተመለከተ በ2014 የበጀት አመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከሆርቲካልቸር ምርት ኤክስፖርት በድምሩ 125.98 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 142.79 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (113.35 በመቶ) ገቢ የተገኘ ሲሆን ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ25.29 በመቶ ብልጫ አሳይቷል፡፡ የሩብ ዓመቱ የገቢ አፈጻጸም በምርት ዓይነት ሲታይ በአበባ 110.05 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ በአትክልት 11.30 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እና በፍራፍሬ 4.63 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እንደ ቅደም ተከተላቸው 122.49፣ 15.56 እና 4.74 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን 111.30፣ 137.70 እና 102.38 በመቶ አፈጻጸም በቅደም ተከተል ተመዝግቧል፡፡

## 6. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

### 6.1. የተፋሰስ ልማት

“ኢትዮጵያን እናልብሳት” በሚል መሪ ቃል በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 6 ቢሊዮን ችግኞች በአገር ውስጥና 1 ቢሊዮን ችግኞች በጎረቤት አገራት ለመትከል ታቅዶ

ከ6.7 ቢሊዮን ችግኞች በላይ የተተከለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህም ውስጥ 3.02 ቢሊዮን የደን ዛፍ፣ 3.3 ቢሊዮን የጥምር ደን እርሻ፣ 371.9 ሚሊዮን የፍራፍሬ እና 62.9 ሚሊዮን ደግሞ የከተማ ውስጥ ተከላ ናቸው፡፡ በተካሄደው የችግኝ ተከላ 2.104 ሚልየን ሄ/ር መሬት ለመሸፈን የተከላ ቦታ ልየታ የተካሄደ ሲሆን ከተወሰኑ ክልሎች በደረሰን መረጃ መሠረት የ304,257ሄ/ር የመጠነ-ዙሪያ ልኬት የጂፒኤስ (Polygon sides GPS) መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ይህም በጎግል ኧርዝ (Google Earth) ካርታ ላይ በማሳረፍ የተለያዩ አካላት ክትትል ሊያደርጉ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በጎረቤት አገራት ለሚደረግ ተከላ ችግኞቹን ለማጓጓዝ

የሚያስፈልገውን ወጪ የኢትዮጵያ መንግስት  የተሸፈነ ሲሆን  ተከላው የተካሄደበት ሀገራት ሶማሊያ፣ ዩጋንዳና ደ/ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ፑንትላንድ ሶማሊያ፣ ሶማሊላንድና ጂቡቲ እንዲሁም በዲኤችኤል ፖስታ ኬንያና ለርዋንዳ ሲሆኑ እስከአሁን በተደረገ ችግኝ የማቅረብ ሥራ 80,000 የተለያዩ ችግኞችን ኤርትራ፤ ለጂቡቲ 40,000 የተለያዩ ችግኞች እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ ለሶማሊላንድ (ሐርጌሳ) እና ለፑንትላንድ ሰማሊያ (ጋርዌ) ደግሞ የሶማሌ ክልል አካባቢ፣ ደንና ዓ/ን ለውጥ ኮሚሽን ኃላፊነቱን ወስዶ ለእያንዳንዳቸው 20,000 የተለያዩ ችግኞች የሚያደርስ ይሆናል፡፡

### 6.2. የአፈር ለምነት ማሻሻል

የአፈርን ምርታማነት በመጠበቅ ረገድ አዳዲስ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጤንነቱና ለምነቱ የተጠበቀ መሬት ሽፋን በማሳደግ ረገድ የኮትቻ አፈር በአይባር ቢ.ቢ.ኤምና በባህላዊ ዘዴ ለማንጣፈፍ የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአርሶ አደሮችን ግንዛቤ በማሳደግ 550,000 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 523,415 ሄ/ር የለማ ሲሆን ይኼውም አፈፃፀም ከመቶ ሲታይ 95.16% መሆኑን ያመላክታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን በጨዋማ አፈር ችግር ለመቅረፍ ጨዋማነትን የሚቋቋሙ ሰብሎችንና የመኖ ዘሮችን በአርሶ አደር ማሳ ላይ የማባዛት ስራዎች ተናውኗል፡፡

አሲዳማ አፈርን በግብርና ኖራ አክሞ ከማልማት አንፃር ከክልል የግብርና አመራሮች ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ 38800 ሄ/ር መሬት በግብርና ኖራ ለማከም የታቀደ ሲሆን ለኖራ ግዥ የሚሆን በጀት ለማስመደብ መግባባት ላይ በተደረሰው መሠረት አማራ ክልል 198,231,984.11 ብር፣ ኦሮሚያ  660,773,280.36 ብር፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ 6,607,732.80 ብር፤ ሲዳማ 8,424,859.32 ብር እና ቤ/ጉሙዝ 1,321,546.56 ብር ሲሆን በአጠቃላይ 875,359,403.15 ብር ለኖራ ግዥ የተመደበ ሲሆንበዚሁም በበጀት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ 9058 ሄ/ር በአሲድ የተጠቃ መሬት ለማከም ተችሏል፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በጥራጥሬ ሰብሎች 150,000 ሄ/ር መሬት በህየወ ማዳበሪያ ለማልማት ታቅዶ 38,039.50 ሄ/ር መሬት ለማልማት የተቻለ ሲሆን ለዚህም 152,158 ሳቼት ህየወ ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡  የአፈር ጤንነትና ለምነትን በማሻሻል የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር 4,500,000 ሜ3 ኮምፖስት ለማምረትና ለመጠቀም ታቅዶ 1,038,628 ሜ3 ኮምፖስት ተዘጋጅቷል፡፡ የባዮስላሪ ምርቱን ለዘር የሚውሉ የተለያዩ የሰብል፣ የጥራጥሬና የአትክልት ዘሮችን አሽቶ በመዝራት 109 ሰርቶ ማሳያዎች በአ/አደርና በገማማ በማከናወን እያመጣ ያለውን የምርት ጭማሪ ማየት ተችሏል፡፡

### 6.3. የአፈር ሀብት መረጃና ካርታ ዝግጅት

የአፈር ሀብት ዓይነትና ባህርይ በመስክ በመለየት ካርታ ከማዘጋጀት አንፃር በተለያየ ጊዜያት በፌደራልና ክልል ባሉ ተቋማት የተሰበሰቡ 6,500 ፕሮፋይል (profile) እና 33,944 የአፈር ንጣፍ ውርስ (legacy data) የአፈር ዓይነት መረጃዎችን የማጥራት ስራ የተሰራ ሲሆን ወደ መረጃ ቋት ለማስገባት እና መረጃው ለተገልጋዮች ተደረሽ እንዲሆን እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን መረጃዎችን የማጥራት እና የማጠቃለል ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

ማዕከላዊ የአፈር መረጃ ቋትና ጂኦፖርታል በጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር ከስራ ክፍሉ እና ተያያዥነት ካላቸው ከሌሎች ስራ ክፍሎች የሚመለከታቸው ባለሙያዎች በማሳተፍ የአፈር መረጃ ቋትና ጂኦፖርታል ግንባታ አፈጻጸምና የመረጃ ሥርዓቱ የተጠቃሚ ተቀባይነት ግምገማ (User Acceptance Testing) ተካሂዷል፡፡ በአፈር መረጃ ስርዓት ግንባታ ዙሪያ ለክልሎች ስልጠናና ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አኳያ አንድ ዙር ስልጠና ለመስተት ታቅዶ ስልጠናውን ለመስጠት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ስራዎች በመከናወን ላይ ሚገኝ ሲሆን አፈጻጸሙም 40% ነው፡፡

### 6.4. አነስተኛ መስኖ ልማት

የአነስተኛ ባለይዞታዎች የተለያዩ ውሀ አማራጮችን በመጠቀም የመስኖ ሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ውሀ አቅርቦት ላይ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህም አንፃር በያዝነው በጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 260.9 ሂ/ር የማልማት አቅም ያላቸውና 662 አ/አደር ተጠቃሚ የሚያደርጉ 5 የመስኖ አውታሮች ግንባታ የማጠቃለል ሥራ የተከናወነ ሲሆን እየተገነቡ ባሉትና በተጠናቀቁት የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በጊዜያዊነት 1,723 ወጣቶችን በማሳተፍ የጊዜያዊ ሥራ ዕድል ተጠቃሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ከማቅረብ አኳያ 130 ሶላር ፓምፖችን ግዥ ለማከናወን የግዥ ጥያቄ ቀርቦ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡በተመሳሳይ መልኩ ለፕሮጀክቱ አገልግሎት የሚውሉ የጉድጓድ ቁፋሮ ማሽን፣ ሌሎችም ለጥናትና ዲዛይን የሚውሉ ዕቃዎች እና የተሽከርካሪ ግዥ ለማከናወን የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች ተሠርቷል፡፡በተጨማሪም በክልል ደረጃ በባለሙያዎች ያለውን የአቅም ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ለመስጠት የስልጠና ፍላጎትና ክፍተት ዳሰሳ በማድረግ በተለዩ የስልጠና ርዕሶች ላይ ስልጠና ለመስጠት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል፡፡

### 6.5. የመሬት አስተዳርና አጠቃቀም

ለአንድ ሚሊዮን ማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ309,000 ማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት ስራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 30.9 ከመቶ ብቻ ሲሆን

የአፈፃፀሙ ዝቅተኝነት ተግባሩ በሚከናወንበት ክልልሎችና ወረዳዎች የጸጥታው ችግር ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ በዕቅድ ያልተያዘ የመሬት ልኬትና ምዝገባ ሥራ ለ503,000 ማሳዎች ተከናውኗል፡፡ ለ0.286 ሚሊዮን ባለይዞታዎች (0.2 ሚሊዮን አባወራ እና 0.086 ሚሊዮን እማወራ) የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 0.088 ሚሊዮን ባለይዞታዎች (0.0.062 ሚሊዮን አባወራ እና 0.026 ሚሊዮን እማወራ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጣቸው ሲሆን አፈፃፀሙም 30.77 ከመቶ ነው፡፡

### 6.6. የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ሥራዎች

ለፕሮግራሙ ማስፈፃሚያ ማለትም ለቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች፣ ለማህበረሰብ ልማት ክፍያ፤ የፌደራል መጠባበቂያ በጀት፤ ካፒታል በጀት፣ ወረዳ አስተዳደራዊና የደመወዝ በጀት፤ለክልሎች አስተዳደራዊ በጀት፤ ለክልሎች አቅም ግንባታ በጀት፤ ለኤሌክትሮኒክ ክፍያ እና ለወረዳ አቅም ግንባታ የሚውል ብር 635,051,888 ወደ ክልሎች ለማስተላለፍ ታቅዶ ብር 2,014,745,429 (100% በላይ) ለማስተላለፍ ተችሏል፡፡የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያ ወቅቱን ጠብቆ መጠናቀቁን ክትትል በማድረግ ከማረጋገጥ አንፃር በተለያዩ ምክንያቶች ክፍያው ሳይጠናቀቅ ከ2013 ወደ 2014 በጀት ዓመት የተላለፈው የገንዘብ ክፍያ ብር 83,698,247 ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያ ለመፈፀም ታቅዶ ብር 44,621,668 (53%) ክፍያው የተፈፀመ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የምግብ ክፍያውን በተመለከተ 320,738.70 ኩንታል ለመክፈል ታቅዶ 241597.73 ኩንታል (75%) ወደ ወረዳ ተጓጉዞ ለተጠቃሚዎቹ ተከፍሏ፡፡አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በአንዳንድ አከባቢዎች በተከሰተው የፀጥታ ችግር ምክንያት እንደሆነ በተደረገው ክትትል ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ለፕሮግራሙ ቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች (PDS) ብር 375,569,630 ለክልሎች በማስተላለፍ ክፍያ ለመፈፀም ታቅዶ ብር 1,462,127,920 ለክልሎች የተላለፈ ሲሆን ብር 497,956,621 (132.5%) ለተጠቃሚዎች ክፍያው የተፈፀመ ሲሆን አፈፃፀሙ ከፍ ያለበት ምክንያት ለተጠቃሚዎች በወቅቱ መክፈል እንዲቻል ከሩብ ዓመቱ ውጪ ላሉ ማለትም ለጥቅምትና ህዳር ወር ክፍያ የሚሆን በጀት አስቀድሞ ለክልል በመተላለፉ ነው፡፡

6,803,770 የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን በህብረተሰብ ተሳትፎ የማህበረሰብ የልማት ስራዎች በማከናወን የወል ጥሪት እንዲገነባ ከማድረግ አንፃር በማህበረሰብ ልማት ሥራዎች ተያያዥነት ባላቸው በተለያዩ ርዕሶች ላይ ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአፈፃፀም ላይ የምክክር መድረኮችን ከማካሄድ አንፃር ዕቅድ ላይ ከክልሎች ባለድርሻ ኣካላት ጋር የምክክር መድረክ ተካሄዷል፡፡

የማህበረሰብ ስራዎች የሚከናወኑባቸው ተፋሰሶችን የተሟላ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች፣ ክትትል ድጋፍ፣ ልየታ፣ እንዲሁም የአተገባበር ሪፖርቶችን በGIS በተደገፈ መልኩ የተሟላ ለማድረግ እንዲቻል ለ65 (ሴ2) ለክልሎችና ፌዴራል ባለሙያዎች  አቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡የማህበረሰብ ስራዎች ስነ-ምህዳራዊ ዘላቂነት እንዲኖራቸው፣ የማህበረሰብ ተቀባይነት እንዲኖራቸው፣ እንዲሁም ከኢኮኖሚ አንጻር አዋጭ በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ ከማድረግ አንፃር ለክልልና በፌዴራል ዳረጃ ለ80 ባለሙያዎች በአካባቢና ማኅበራዊ ደህንነት ርዕስ ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡የማህበረሰብ ስራዎች የካርታ መረጃ ቋት (map data base) ስራ የሶስተኛ ፍተሸ በማድረግ ስራውን ከአማካሪ ድርጅቱ ለመረከብ የተቻለ ሲሆን በመረጃ ቋት የተሰሩ ስራዎችን በሙሉ ለማስገባት፤ በአምስተኛው ምዕራፍ የተካተቱ አዳዲስ አሰራሮችን እንዲያካትት እና ስራው አገራዊ እንዲሆን ለማድረግ የተጨማሪ ስራ በመጠየቅ ይሁንታ በማግኘት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም አቅምን ያገናዘበ እና ተገቢ የሆነ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ አገልግሎትን ለ121000 ቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች በማቅረብ ተጠቃሚዎቹ በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እንዲገነቡ ከማድረግ አንፃር:-ለክልሎች በዕቅድ ዝግጅት ላይ ድጋፍ በመስጠት፣ በሁሉም ክልሎች የተጠቃሚዎችን ክፍያ 70 በመቶ በላይ በወቅቱ የከፈሉ  ወረዳዎችን ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች ትግበራ በመምረጥ በክልል ደረጃ የሚደርሳቸውን ቁጥር በማሳወቅ ተጠቃሚዎች መሰረት ያደረገ እቅድ እንዲያዘጋጁ ተደርጓል፡፡

## 7. የግብርና ምርምር

**የምርምር ሙከራዎች/ጥናቶች**

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሚጠበቅበትን የምርምር ውጤቶች ለማውጣት በበጀት ዓመቱ በ71 የምርምር ፕሮግራሞች ስር የተነደፉ 2,584 የምርምር ሙከራዎችን ማካሄድ የሚጠበቅት ሲሆን፤ 2,224 የምርምር ሙከራዎችን ለማካሄድ አቅዶ 2,088 (94 በመቶ) ሙከራዎች የተከናወኑ ሲሆን የ5 ሙከራዎች ጥናት ተጠናቋል፤ 184 በጸጥታ ችግር፣ መሳሪያዎቹ በገበያ ላይ ማግኝት ስላልተቻለና ግብአቶች በጊዜ ባለመቅረባቸው ምክንያት ያልተጀመሩ ሲሆን 14 ሙከራዎች በዘር እጥረት፣ በተከሰተው ከፍተኛ ዝናብ፣ ሙከራዎች በበሽታ በመመታታቸው እና በጸጥታ ችግር ምክንያቶች ለጊዜው ተቋርጠዋል፡፡

የቴክኖሎጂ እና መረጃ አቅርቦት ሥራዎች

ኢንስቲትዩቱ የተጣለበትን አገራዊ የቴክኖሎጂ ማቅረብ ኃላፊነት ከመወጣት አኳያ ቀደም ሲል በተለያዩ የምርምር መስኮች በተጀመሩና በበጀት ዓመቱ ተከናውነው በሚጠናቀቁ የምርምር ተግባራትና መዳረሻ ውጤቶች ላይ የተመሰረቱ 133 ቴክኖሎጂዎች እና 358 መረጃዎች በድምሩ 491 ውጤቶችን እንደሚያቀርብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 24 የምርምር ውጤቶች (8 ቴክኖሎጂና 16 መረጃዎች) ለማውጣት ታቅዶ፤ 25 የምርምር ውጤቶች (8 ቴክኖሎጂዎችና 17 መረጃዎች) ተገኝተዋል፡፡

## የቴክኖሎጂ ማላመድ ሥራዎች

ለአገሪቱ የግብርና ቀጠናዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመደበኛ ፕሮግራም በምርምር ከማፍለቅ ጎን ለጎን ከውጭ አገር ያለቀላቸውን ቴክኖሎጂዎች በማስመጣትና በማላመድ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት ለማቅረብ ከተነደፈው አቅጣጫ አንጻር በ2014 የበጀት ዓመት 99 (83 የሰብል፣ 3 የእፅዋት ጥበቃ፣ 3 የእንስሳት፣ 8 የግብርና ምህንድስና ምርምር እና 2 የግብርና ባዮቴክኖሎጂ) ዝርያ/ቴክኖሎጂዎችን በማስመጣት የማላመድ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ ሥራዎች

ኢንስቲትዩቱ በ2014 የበጀት ዓመት አዳዲስና ነባር ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን ለ30,883 (23,084 ወንድና 7,799 ሴት) አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የዘር አባዦች፣ የግል ባለሃብቶች እና ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አካላት የማስተዋወቅ ሥራዎችን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ሶስት ወራት ለ9,878 (7,591 ወንድና 2,287 ሴት) ተጠቃሚዎች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ ታቅዶ ለ9,500 (7,438 ወንድና 2,062 ሴት) የእቅዱን 96 በመቶ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ለማስተዋወቅ ተችሏል፡፡

## የቴክኖሎጂ ማስፋት ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ ለ20,914 (15,470 ወንድ እና 5,444 ሴት) ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የቅድመ ማስፋት ሥራዎችን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን፤ ይህን ለማሳካት በመጀመሪያው ሶስት ወራት 8,411 (6,767 ወንድ እና 1,644ሴት) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ታቅዶ ለ11,802 (10,022 ወንድ እና 1,780 ሴት) ከዕቅዱ በላይ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## የምርምር ውጤቶች አህዝቦትና ተደራሽነት ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 1 የፕሬስ ኮንፍረንስ፣ 4 የመስክ ቀኖች፣ 4 የሚዲያ ሽፋን፣ 1 የሚዲያ ሞኒተሪንግ፣ 2 የቴሌቪዝን ፕሮግራም፣ 3 የሬዲዮ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት፣ 12 አርቲክሎችን በማዘጋጀትና በማሳተም ለማሰራጨት፣ 1 የዜና መጽሔት ለማዘጋጀት፣ 3 የቨርቹዋል ሥርዓቶችን ለመዘርጋት፣ 2 በራሪ ወረቀቶች፣ ቡክሌቶች፣ ፓስተሮች፣ ባነሮች ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት፣ 1 የመረጃ አያያዝ ዘዴን ለመተግበር፣ 1 ጊዜ የፋናንስ አጠቃቀምን መከታተልና በዳታ ቤዝ ለመመዝገብ፣ 3 ለዶክመንቴሽን እና ኮሙኒኬሽን የተገነቡትን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሶፍትዌሮች ጥቅም ላይ ለማዋልና 1 በኮሙኒኬሽን እና መረጃ አያያዝ ዙሪያ የልምድ ልውውጥ መርሃ-ግብሮችን በማዘጋጀት የባለሙያውን አቅም ለማሳደግ ታቅዶ 2 የመስክ ቀኖች የማድረግ፣ 2 የሚዲያ ሽፋን ስራዎች፣ 1 የሚዲያ ሞኒተሪንግ የማድረግ፣ 2 የሬዲዮ ፕሮግራሞችን የማድረግና 2 አርቲክሎችን በማዘጋጀትና በማሳተም የማሰራጨት ስራዎች ተከናውኗዋል፡፡ ታቅደው ያልተከናወኑ ስራዎች ደግሞ በበጀት እጥረት ምክንያት፣ የአርሶ አደር መስክ ቀኖች ገና ስላልተካሄዱ እና ስራዎቹ ሂደት ላይ በመሆናቸዉ ነዉ፡፡

## ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች

በበጀት ዓመቱ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የአሰራር ዘዴ (አመራረት)፣ አያያዝ (እንክብካቤ)፣ በእንስሳት እና እፅዋት በሽታዎች ቅድመ መከላከልና ቁጥጥር ዘዴዎች በጠቅላላው ለ60,963 (42,645 ወንድና 18,318 ሴት) አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የዘር አባገሮች፣ የግል ባለሀብቶች እና ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አካላት የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ለመስጠት ከታቀደው ዕቅድ ውስጥ በመጀመሪያው ሶስት ወራት 10,247 (7,145 ወንድና 3,102 ሴት) ተጠቃሚዎችን ለማሰልጠን የታቀደ ሲሆን፣ ለ10,481 (7,423 ወንድና 3,058 ሴት) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ማሰልጠን ተችሏል።

## የቴክኖሎጂዎች ብዜት ሥራዎች

### የሰብል ምርምር ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በበጀት ዓመቱ በብርዕ ሰብሎች፣ በአገዳ ሰብሎች፣ በጥራጥሬ ሰብሎች፣ በቅባት ሰብሎች፣ በኢንዱስትሪ ሰብሎች፣ በአትክልት ሰብሎች፣ በስራስር ሰብሎች፣ በመዓዛማና መድሃኒት ሰብሎች፣ በቅመማ ቅመም ሰብሎች፣ በፍራፍሬ እና በቡና ሰብሎች 1,352 ኩንታል፣ 91,950 ችግኝ እና 372,200 ቁርጥራጭ እና 22,000 ቀንበጥ በአራቢ የዘር ደረጃ ለማባዛት ከታቀደው ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 50.4 ኩንታል፣ 2,500 ችግኝ ለማባዛት ታቅዶ 38.9 ኩንታል ሊባዛ ችሏል፡፡ በተጨማሪም የፍራፍሬ ችግኝ ዘሮች የተጠቃሚዎች ፍላጎት ከፍ በማለቱ 13,490 ችግኞች ተባዝተዋል፡፡

በቅድመ-መስራች ዘር ደረጃ በበጀት ዓመቱ 315 ኩንታል ሁለት የድንች ዝርያዎች ዘር እና 8,100,000 የሰብል ቁርጥራጮች ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት በዕቅድ የተያዘ የሰብሎች ዘር ምርት ባይኖርም ዘግይቶ በመጣ የተጠቃሚ ፍላጎት መሰረት 0.4 ኩንታል መነሻ ዘር ሊባዛ ተችሏል፡፡

በመስራች ዘር ደረጃ በበጀት ዓመቱ 435 ኩንታል ሁለት የድንች ዝርያዎች ዘር እንዲሁም 6,850 የሰብል ችግኞች ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 3,350 ችግኞችን ለማባዛት ታቅዶ 4,693 ችግኞችን ማባዛት ቢቻልም፣ በችግኝ ጣቢያ ባለዉ ከፍተኛ የመስኖ ዉኃ እጥረት ምክንያት እናት ግንዶች በቂ ችግኞች ሊያቆጠቁጡ ባለመቻላቸዉ የአፕል ችግኝ ብዜት ከዕቅድ በታች ሊሆን ችሏል፡፡

## የእንስሳት እና የእንስሳት መኖ ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በእንስሳት ቴክኖሎጂዎች ብዜት በበጀት ዓመቱ 1,550 ሌይንግ የሐር ትል እንቁላል፣ 70 እናት ንብ፣ 120 የንብ ጠላት ማጥመጃ ቀፎ፣ 170 የቀንድና የዳልጋ ከብቶች፣ 420 በግና ፍየሎች፣ 420,000 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩት እንዲሁም 1,150,000 የዓሳ ጫጩት ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 43 ጊደሮች፣ 4 ኮርማዎች፣ 205 በግ፣ 80,000 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩት፣ 190,000 የዓሳ ጫጩት፣ 500 እንቁላል ጣይ የሐር ቢራቢሮ፣ 35 እናት ንብ፣ 30 የንብ ጠላት ማጥመጃ ቀፎ  ለማባዛት ታቅዶ 42 ጊደሮች፣ 4 ኮርማዎች፣ 120 በግ፣ 7,358 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩት፣ 162,300 የዓሳ ጫጩት፣ 800 እንቁላል ጣይ የሐር ቢራቢሮ፣ 35 እናት ንብ፣ 30 የንብ ጠላት ማጥመጃ ቀፎ  ተባዝቷል፡፡ የበግ፣ የዓሳ ጫጩት፣ እና የ 1ቀን የዶሮ ጫጩት ብዜት አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነው  በበግ ምርምር የሙከራ እንስሳቱ በመውለድ ላይ ስለሆኑ ሙሉ የብዜት መረጃው ወደቀጣዩ ሩብ አመት በመሸጋገሩ፣ በዓሳ ጫጩት የሚባዙ ቴክኖሎጂዎች የክረምቱ ዝናብ የፈጠረዉ ከባድ ቅዝቃዜ ወላድ ዓሳዎች ላይ ባሳደረዉ አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት ሲሆን የ 1ቀን የዶሮ ጫጩት ብዜት ወላጅ ዶሮዎቹ አርጅተው (72 ሳምንት ዕድሜ ስለሞላቸው) በመወገዳቸው ነው፡፡

የእንስሳት መኖን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 176.20 ኩንታል ዘር፣ 12,000 ቁርጥራጭ፣ 5,385,000 ዝንጣይ እንዲሁም 25,000 ችግኝ ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 1,155,000 ዝንጣይ፣ 1.5 የሐር ትል መኖ፣ 3,000 ቁርጥራጭ እንዲሁም 25,000 ችግኝ ለማባዛት ታቅዶ 4,175,000 ዝንጣይ፣ 1.28 ኩንታል የሐር ትል መኖ፣ 2,500 ቁርጥራጭ እንዲሁም 38,500 ችግኝ ተባዝቷል፡፡

## የተፈጥሮ ሃብት ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ልማት የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ በበጀት ዓመቱ 7,000 ፓኬት የራይዞቢያ ሕየው-ማዳበሪያ (ባዮፈርቲላይዘር)፣ 2 ኩንታል የቨርሚኮምፖስት ትል እንዲሁም 30

ኩንታል ቨርሚኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 1,500 ፓኬት የራይዞቢ.ያ ሕየው-ማዳበሪያ፣ 0.5 ኩንታል የኮምፖስት ትል፣ 7.5 ኩንታል ቨርሚኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ለማባዛት ታቅዶ 1,548 ፓኬት የራይዞቢ.ያ ሕየው-ማዳበሪያ፣ 0.81 ኩንታል የኮምፖስት ትል፣ 17.75 ኩንታል ቨርሚኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ተባዝቷል፡፡

**የግብርና ባዮቴክኖሎጂ ቴክኖሎጂዎች ብዜት**

በግብርና ባዮቴክኖሎጂ በመደገፍ በበጀት ዓመቱ 242,000 (19,000 የቡና፣ 60,000 የዝንጅብል፣ 84,000 የአናናስ፣ 2,000 የአፕል፣ 5,000 የፕለም፣ 20,000 የድንች፣ 10,000 የስኳር ድንች፣ 2,000 እንሰት እና 40,000 የሙዝ ችግኞች ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 54,000 (8,000 የቡና፣ 10,000 የዝንጅብል፣ 21,000 የአናናስ፣ 5,000 ድንች እና 10,000 የሙዝ) ችግኞች ለማባዛት ታቅዶ 45,500 (6,500 የቡና፣ 5,000 የዝንጅብል፣ 21,000 የአናናስ፣ 3,000 የድንች እና 10,000 የሙዝ) ችግኞች ተባዝተዋል፡፡ በድንች ማሻሻያ ፕሮግራም በመባዛት ላይ ያሉት ዝርያዎች በሌላ የድንች ዝርያዎች እንዲተኩ ስለተፈለገ የአዲሶቹን ዝርያዎች የመነሻ ተክል ወደ ላብራቶሪ በማስገባት ሂደት ውስጥ በመገባቱ የነባሮቹ ዝርያዎች ብዜት እንዲቀንስ ምክንያት ሆኗል፡፡

**የግብርና ምህንድስና ቴክኖሎጂዎች ብዜት**

በግብርና ምህንድስና መስክ በበጀት ዓመቱ ለምግብ ዋስትና እና ለተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ጠቀሜታ የሚሰጡ 203 ልዩ ልዩ የቅድመ-ምርት፣ ምርት እና ድህረ-ምርት የእርሻ መሣሪያዎችን ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 20 የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችን ለማባዛት ታቅዶ በዕቅድ በተያዘው መሠረት ሙሉ በሙሉ ተባዝተዋል፡፡

የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ምርምርና ኤክስቴንሽን ቴክኖሎጂ ብዜት

በአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ምርምር በበጀት ዓመቱ 20 ኩንታል ለዉዝ፣ 30 ኩንታል ማሾ፣ 600 የሙዝ ሳከርና 1,000 ቡና ችግኝ እንዲሁም 3,000 የዶሮ ጫጩትና 14 ኩንታል መኖ ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 600 የሙዝ ሳከርና 1,000 የቡና ችግኝ ለማባዛት ታቅዶ 600 የሙዝ ሳከርና 1,500 የቡና ችግኝ ተባዝተዋል። እንዲሁም በሁለተኛ፣ በሶስተኛና አራተኛ ሩብ ዓመት ታቅደው ከነበሩት ውስጥ 1 ኩንታል ማሾ፣ 1000 የዶሮ ጫጩትና 4 ኩንታል መኖ በዚህኛው ሩብ ዓመት የተባዙ ሲሆን ከዓመታዊ ዕቅድ ዉጭ 5 ኩንታል የቅድመ መስራች ሽንኩርት ዝርያዎችና 3,200 የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ማባዛት ተችሏል፡፡

**የተቀናጀ ግብርና የቴክኖሎጂ ብዜት ዕቅድ**

በተቀናጀ ግብርና ምርምር በበበጀት ዓመቱ 1,156.65 ኩንታል የሰብል ዘር፣ 15,000 የፍራፍሬ ችግኞች፣ 15 ጊደሮችና ኮርማዎች፣ 230 ላሞችን በተሻለ የኮርማ ዘር ለማዳቀል እንዲሁም 10

ኩንታል የእንስሳት መኖ ዘር ለማባዛት ከተያዘው ዕቅድ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 60 ኩንታል የሰብል ዘር፣ 4 ጊደሮችና ኮርማዎች፣ 70 ላሞችን በተሻለ የኮርማ ዘር ለማዳቀል እንዲሁም አስር ኩንታል የእንስሳት መኖ ዘር ለማባዛት ታቅዶ 10 ኩንታል የሰብል ዘር፣ 4 ጊደሮችና ኮርማዎች ለማባዛት የተቻለ ሲሆን ምርት ባለመሰብሰቡ የሰብሎች እና የእንስሳት ዘር ብዜት አፈጻጸም እንዳይኖረው ሊያደርግ ችሏል፡፡

***ሀገራዊ የምርምር ስርዓት መገንባት***

ከክልል የግብርና ምርምር ተቋማትና ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት አባል ዩኒቨርስቲዎች በተውጣጣ ቡድን የተመራማሪዎችን የሥራ ተነሳሽነት ለማሳደግና የምርምር ስነ-ምግባርን ለማስጠበቅ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ የሚመራበት የአሰራር መመሪያዎች ማዕቀፍ (ሌጂስሌሽን) ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ በማድረግ ተቋማት እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

በሴክሬታሪቱ የበጀት ድጋፍ ከኒም ፍሬ በሚገኝ የኒም ዘይት አዲሱን መጤ ተምች (FALL ARMY WORM) ለስነ ምህዳር ተስማሚ በሆነው ስነ-ሕይወታዊ ፀረ-ተባይ ለመቆጣጠር በሴክሬታሪያቱና በደቡብ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የጂንካ ምርምር ማዕከል ትብብር የተሰራው የመስክ ሙከራ ተጠናቋል፡፡

በዕፅዋት ተባዮች (አረም፣ በሽታና ነፍሳት ተባዮች) ምክንያት የሚከሰተውን የምርት መጠንና ጥራት መጓደልን በመቀነስ የምግብና የሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማጎልበት እንዲያስችል ሴክሬታሪያቱ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በትብብር ሲያዘጋጀው የነበረው የኢትዮጵያ የዕፅዋት ጥበቃ ፍኖተ ካርታ ለባለድርሻ አካላት ቀርቦ ፀድቋል፡፡

የመስኖ ስንዴ ሰርቶ ማሳያ ስራዎች ለመተግበር የእርሻ መሬት መረጣ፣ ተሳታፊ ባለሀብቶችን የመለየት፣ አተገባበሩ ላይ ውይይት የማድረግና የመሬት ዝግጅት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ለሰርቶ ማሳያው የሚውሉ አራት የተለያዩ ዝርያዎች (ሉሲ፣ አሚባራ 2፣ ወረር 2 እና ደንደአ) ከወረር ግብርና ምርምር ማዕከል ተጠይቀው ወደ ደቡብ ኦሞ የተጓጓዙ ሲሆን፣ ማዳበሪያም (ዩሪያ እና ኤን.ፒ.ኤስ) የማጓጓዝ ስራ ተከናውኗል፡፡ እስከ አሁን ድረስ በተደረገው የማላመድ ሙከራ የኦሞ ሽለቆ ለአኩሪ አተር፣ ለውዝ፣ ሰሊጥና ሱፍ ተስማሚ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት ሴክሬታሪያት የምርምር ተቋማት የሚያካሂዷቸው የግብርና ኢኮኖሚክስ/የኤክስቴንሽን የምርምር ስራዎች የመረጃ መሰብሰብ ተግባር አውቶሜትድ የመረጃ መሰብሰቢያ ቱሎችን (ኮምፒውተር፣ ታብሌት እና ስልክ) በመጠቀም ይካሄድ ዘንድ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት 15 ማዕከላት ለተውጣጡ 17 ተመራማሪዎች በአሁኑ ወቅት በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን "CSPRO (CENSUS AND SURVEY PROCESSING) SOFTWARE" መሰረት ያደረገ አቶሜትድ የምርምር መረጃ አሰባሰብና አያያዝ ዘዴን በጥልቀት በማሰልጠን፣ ተመራማሪዎቹ በ2014 ያቀዱአቸውን የምርምር ስራዎች ኦቶሜትድ መረጃ መሰብሰቢያ ቋት

በማዘጋጀት እንዲሰበስቡ ለማስቻል ለ10 ተከታታይ ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ከICIPE ጋር በመተባበር በመጤ ተምች ሥነ-ሕይወታዊ ቁጥጥር ዘዴ ላይ ከዕፅዋት ጥበቃ ክሊኒኮች፣ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከግብርና ምርምር ተቋማት ለተወጣጡ 30 ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች የአጭር ግዜ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በምዕራብ ጎጃም አኩሪ አተር በ25 ሄክታር ላይ እንዲሁም በአዊ ዞን ጃዊ ወረዳ በግልገል በለስ ስኳር ፕሮጀክት እርሻ ማሳ ላይ አኩሪ አተር በ5 ሄክታር እና ሱፍ በሩብ ሄክታር ላይ እየተባዛ ይገኛል፡፡

ቢጋምቤላ ክልል በአቦቦ የግብርና ምርምር ማዕከል የምርምር ማሳ ላይ 1.3 ሄ/ር ሰሊጥ እንዲሁም በኢታንግ ወረዳ ልዩ ስሙ አኩላ በተባለው ስፍራ በሚገኝ የባለሀብት ማሳ ላይ ከጋምቤላ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በ10ሄ/ር መሬት ላይ የሱፍና ሰሊጥ ሠርቶ ማሳያ እየተካሄደ ነው፡፡

## 8. ህብረት ስራ ማህበራት

በበጀት ዓመቱ 21,058 በሩብ ዓመቱ ደግሞ 2,106 ማህበራት ለማጠናከር ታቅዶ፤ 556 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከር ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 410 በሁለገብ፣ 31 ሸማች፣ 79 ቁጠባና ብድር፣ 36 ሌሎች መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማጠናከር የዕቅዱን 26.4% ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ከፍተኛ ኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉዋቸዉ እና በሥራዉ ከፍተኛ ተሳታፊ የነበሩ እንደ ኦሮሚያ አማራ ደቡብ ክልሎች ማስፋፊያዎች ሪፖርት ባለመላካቸዉ ነዉ፡፡

እንደ ሴክተር በአጠቃላይ ኅብረት ሥራ ማህበራት ባልተዳረሱባቸዉ አካባቢዎች እና ችግሮቻቸውን በተናጠል መፍታት ያልቻሉ የማህበረሰብ አካላትን በፍላጎታቸው መሠረት ትኩረት በመስጠት በበጀት ዓመቱ 1,000 በሩብ ዓመቱ 100 አዳዲስ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት ታቅዶ፤ በሩብ ዓመቱ ከዕቅድ በላይ 363 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት ተችሏል፡፡

አዳዲስ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት እና ነባሮችን በማጠናከር አዳዲስ አባላትን ማፍራት በዓመቱ 1.7 ሚ (ወንድ 850,000 ሴት 850,000 ከዚህ ውስጥ ወጣት 200,000) በሩብ ዓመቱ 170,000 (ወንድ 85,000 ሴት 85,000 ከዚህ ውስጥ ወጣት 20,500) ታቅዶ፤ 165,402 (ወንድ 109,832 ሴት 55,570) ማሳካት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተሰማሩበት ዘርፍ ጠንካራና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውስጥ የካፒታል አቅማቸዉን ለማሳደግ የማጠናከር ሥራ በመስራት እንዲሁም አዳዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጠንካራ የካፒታል አቅም ለማቋቋም በዓመቱ ብር 2,280,000,000 በመጀመሪያ ሩብ ዓመት 228,000,000 ታቅዶ፤ በመሠረታዊ ብር 276,006,961.89 እና በዩኒየን ብር 111,971,042.66 በአጠቃላይ በብር 387,978,004.55 የካፒታል አቅማቸዉን ማሳደግ የተቻለ ሲሆን

አፈጻጸሙም ከዕቅዱ (100%) በላይ ነው፡፡ በዚህም የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ኦሮሚያ እና ሲዳማ ክልሎች ናቸዉ፡፡

የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች በስራቸው የሚያቅፏቸውን ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር በበጀት ዓመቱ 2,375 በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ደግሞ 238 የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የዩኒዬን አባል ለማድረግ ታቅዶ፤ 78 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በዩኒየኖች አባል ማድረግ ተችሏል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአገር ውስጥ የግብርና ምርት የግብይት ተሳትፎ እና ድርሻ ለማሳደግ በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 20 ከመቶ በ 2014 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 24 በመቶ ለማድረስ ግብ የተጣለና የግብርና ምርቶችን ለአገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ በዓመቱ 1,680,000.00 ሚሊዮን ቶን፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 168,000.00 ሺ.ህ ቶን ለማቅረብ ታቅዶ፤ 66,293.80 ሺ.ህ ቶን ምርት ለአገር ዉስጥ ገበያ እንዲቀርብ በማድረግ የዕቅዱን 39.5%ን ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት በአብዛኛዉ ከፍተኛ ኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉዋቸዉ እና በስራዉ ከፍተኛ ተሳታፊ የነበሩ ኦሮሚያ፣ አማራ እና ደቡብ ክልሎች ማስፋፊያዎች ሪፖርት ባለመላካቸዉ ነዉ፡፡ በአገር ውስጥ 22,988 የቁም እንስሳት ግብይት ተካሂዷል፡፡

በኑሮው የተረጋጋ ሕብረተሰብ እንዲኖር ከማድረግ አንጻር በበጀት ዓመቱ 12 ቢሊዮን ብር በሩብ ዓመቱ 1.2 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ የተለያየ የግብርና የኢንዱስትሪ ሸቀጦችና መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ ምርቶች ግብይት ለማካሄድ ታቅዶ፤ በሩብ ዓመቱ ብር 155,246,629 የሚያወጣ የተለያየ የግብርና የኢንዱስትሪ ሸቀጦችና ምርቶች እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ ምርቶች ግብይት በማካሄድ አባላትን እና ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ቀርቦ የሚሠራጨውን የአፈር ማዳበሪያ (የግብርና ምርት ማሳደጊያ) ግብዓት ስርጭት ድርሻ በ2013 ከደረሰበት 98.25 በመቶ ወደ 98.5 በመቶ እና ፀረ-ተባይ፣ ፀረ-በሽታ እንዲሁም ፀረ-ፈንገስ ከ553 ቶን ወደ 581 ቶን ለማድረስ ታቅዶ፤ 2013/14 ምርት ዘመን እስካሁን ድረስ የተሰራጨ ማዳበሪያ 1,386,851.55 ሜ/ቶን ከዚህ ውስጥ ከሀምሌ እስከ መስከረም 30/2014 የተሰራጨው ደግሞ 542,573.44 ሜ/ቶን ማዳበሪያ በኅብረት ስራ ማህበራት እንዲሰራጭ የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡ 8 ሚሊየን ብር የሚያወጣ የኬሚካል እና ሌሎች የእርሻ መሳሪያዎች ግብይት ተከናውኗል፡፡

23 ህብረት ስራ ዩንየኞችና 248 መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት አማካኝነት በ10 ሰብል አይነት እና ከ39 በላይ የተለያዩ ዝርያዎችን ተባዝቶ የነበረን 38,351.29 ቶን ምርጥ ዘር ለስርጭት ዝግጁ በማድረግ ባለፈው ዓመት ተባዝቶ ሳይሰራጭ ከቀረው 29,881.31 ቶን ምርጥ ዘር ውስጥ በዚህ ሩብ ዓመት 24,840.713 ቶን ለተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በመጋዘናቸው 30,406 ቶን ምርጥ ዘር ይገኛል፡፡

3,000.00 ቶን የተለያዩ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በመላክ 16,823,529.41 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ፣ 5,175 ቶን በ 15 ኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የተለያዩ የግብርና ምርቶችን (ቡና፣ ሰሊጥ፣ ቦለቄና አኩሪ አተር) ለውጭ ገበያ በመላክ 23,959,685 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

የውጭ ግብይት ዝርዝር አፈፃፀም

| የምርት አይነት | የመስከረም ወር አፈጻጸም | | ከሀምሌ እስከ መስከረም ወር | | አማካኝ የመሸጫ ዋጋ በሜ/ቶን |
|---|---|---|---|---|---|
| | መጠን በሜ/ቶን | ዶላር | መጠን በሜ/ቶን | ዶላር | |
| ቡና | 1,420.50 | 7,185,759.33 | 4,511.30 | 23,271,230.41 | 5,158 |
| የተቆላ ቡና | 0.00 | 0.00 | 1.52 | 15,274.20 | 10,049 |
| ሰሊጥ | 0.00 | 0.00 | 108.00 | 183,600.00 | 1,700 |
| ቦሎቄ | 0.00 | 0.00 | 400.00 | 355,600.00 | 889 |
| አኩሪ አተር | 0.00 | 0.00 | 154.00 | 133,980.00 | 870 |
| ድምር | 1421 | 7,185,759 | 5175 | 23,959,685 | |

የግብርና ቅድመ ምርት ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ የመካናይዜሽን መሳሪያዎች በማስገባት በበጀት ዓመቱ 70 ህብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸዉ አገልግሎት እንዲሰጡ ታቅዶ በሩብ ዓመቱ የተያዘ ዕቅድ ባይኖርም 1,267 ሄክታር በማረስ ለማህበራቱ 3,407,543 ብር ከአገልግሎቱ የተገኘ ሲሆን 730 አርሶ አደሮች (ወንድ 652 ሴት 78) ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ለማሳደግ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብር 300,000,000 ለመቆጠብ ታቅዶ፣ 369,818,732 በመሰብሰብ ከዕቅድ በላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው የኦሮሚያ ክልል እና በፌዴራል የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው፡፡

በሩብ ዓመቱ ብር 300,000,000 ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ፣ ብር 411,437,915.86 ለ69,414 አባላት በማሰራጨት በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በሩብ ዓመቱ ለ112,000.00 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ 69,414 ዜጎች (ወንድ 35,211 ሴት 34,203) ብድር በወሰዱ አባላት የተፈጠረ የስራ እድል ሲሆን፣ በሌሎች በተለያዩ ዘርፎች ለ

718 ዜጎች (ወንድ 486 ሴት 232) ቋሚ የስራ ዕድል እና ለ 15,447 ዜጎች (ወንድ 10,944 ሴት 4,503) ጊዜያዊ የስራ ዕድል በድምሩ ለ 16,165 (ወንድ 11,430 ሴት 4,735) ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የኦዲት አገልግሎት ሽፋን በሩብ ዓመቱ 2,138 ለማድረስ ታቅዶ፣ 1,302 (61%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህ 1ኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ከተደረጉት ማህበራት ውስጥ 986 ማህበራት 112,482,513.8 ትርፍ ያገኙ ሲሆን፣ 130 ማህበራት 7,833,253.2 ብር ኪሳራ 1 ዩኒዬን 314,983.3 ብር ኪሳራ አስመዝግቧል፡፡ 186 ኅብረት ሥራ ማህበራት ያለ ትርፍ እና ኪሳራ ባሉበት ቀጥለዋል፡፡

## 9. ግብርና ትራንስፎርሜሽን

የግብርና ግብዓትና አገልግሎት ፕሮጀክት በተመለከተ በዚህ ሩብ ዓመት በሶስት ክልሎች ውስጥ 166 ማዕከላት ለ803,851 አ/አደሮች የተለያዩ ግብዓቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከ600 ሚሊዮን ብር በላይ የሽያጭ ገቢ አግኝተዋል፡፡ በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል የሚገኙ ማዕከላት የሽርክና ማህበር በማቋቋም የግብዓት አስመጭ በመሆን የግብዓት ችግሮችን ለመፍታት ስራ ጀምረዋል፡፡

የኅብረት ስራ ማሕበራት አቀፍ ዘር ብዜት ፕሮጀክት በተመለከተ አዳዲስ የዘር ብዜት ዩኒየኖች ለማቋቋም የሚያስችል የአዋጭነት ጥናትና ማረጋገጫ ሥራ በደቡብ/ብ/ብ/ህ ክልል ተጠናቋል፡፡ 12 ዩኒየኖች የብድር ፍላጎት ተጠናቅሮ ለክልል የመንግስት አካላት ቀርቧል፡፡

የተቀናጀ ጥልቅ ያልሆነ የከርሰ ምድር ውሃ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተመለከተ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ግምገማ መሣሪያ እና የሰብል የቀን መቁጠሪያ ዝግጅት ላይ ከደቡብ ብ/ብ/ሕ በኦሮሚያ እና ከአማራ ክልል ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳዎች ለተውጣጡ 103 (14 ሴት) ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ከደቡብ እና አማራ ክልሎች ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳዎች ለተውጣጡ 53 (9 ሴት) ባለሙያዎች በመስኖ ውሃ አስተዳደር፣ በመስኖ እርሻ እና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች የሰብል ጥበቃ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት የሙከራ ፕሮጀክት በተመለከተ የማዕከላት ግንባታ ጋለማ 82%፣ አምቦ 80%፣ ሲኮማንዶ 84%፣ ጊቤ ዴዴሳ 92 %፣ መሊቅ 80%፣ ወላይታ 52 %፣ ማንዴላ ተመስገን፣ 81%፣ ቡሬ ዳሞት 65% እና ጎዛምን 10% ደርሰዋል፡፡ በኦሮሚያ 4 ማዕከላት፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ 2 ማዕከላት፣ በአማራ 2 ማዕከላት፣ በአጠቃላይ 8 ማዕከላት የመስክ ጉብኝት በማካሄድ የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማ የዓቅም ግንባታ ፕሮጀክት በተመለከተ ለ173 (15 ሴት) የገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት ዩንየን ማናጀሮች፣ የብድርና የሂሳብ ባለሙያዎች እንዲሁም የክልልና የዞን ኅ/ሥራ ባለሙያዎች በአቅም ምዘናና ክፍተት መለያ ዘዴ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጧል፡፡ የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማህበራትን የዉስጥ አሰራርን ለማሻሻል፤ ለማቀድና ለመተግበር የሚረዱ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እንዲኖራቸዉ በስጋት/አደጋ ማኔጅመንት (RISK MANAGEMENT)፣ ገንዘብ ዕዳና ንብረት አስተዳደር (LIQUIDITY-ASSEST-LIABILITY MANAGEMENT) ፖሊሲና መመሪዎችን የመጀመሪያ ድራፍት ማንዋሎች ተዘጋጅተዋል፡፡

የግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ ሥርዓት ፕሮጀክት በተመለከተ በመጀመርያ ሩብ አመት 5.3 ሚልዮን አርሶአደሮች የግብዓት ኩፖን ሽያጭ ስርዓትን በመጠቀም 11.5 ሚልዮን ኩንታል ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር እና ኬሚካሎችን በ16.89 ቢልዮን ብር ገብይተዋል። በአማራ ክልል ብቻ 473.8 ሺ.ህ (87% ሴት) አርሶአደሮች 1.5 ቢልዮን ብር የግብዓት ብድር አግኝተው 1.4 ሚልዮን ኩንታል ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር እና ኬሚካሎችን ግብዓት ገብይተዋል።

የ8028 የአርሶ አደሮች ነፃ የድምፅ ቅብብሎሽ ምላሽ ፕሮጀክት በተመለከተ መሰረታዊ የገንዘብ አያያዝ እና የቁጠባ ግንዛቤን በአርሶ አደሩ ዘንድ ለማሳደግ የሚያስችል የሥልጠና ሞጁል ተዘጋጅቶ ወደ 8028 የአርሶ አደሮች ነፃ የግብርና መረጃ ስርአት እንዲካተት የተደረገ ሲሆን ስልጠናው አራት የሃገር ውስጥ ቋንቋዎችን በመጠቀም ለተጠቃሚዎች ተሰጥቷል፡፡

ሀገር አቀፍ የገበያ መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት በተመለከተ ተጠቃሚዎች ግብይታቸውን በመረጃና በዕውቀት ላይ ተመስርተው እንዲወስኑ በሩብ ዓመቱ 7,304 ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡ ሳምንታዊ የገበያ መረጃ በ6077 የመልዕክት የቴሌ መስመር ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል:: ከመረጃ ስርዓቱ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡ የገበያ መረጃዎችን ለማግኘት 66,033 አዳዲስ ተጠቃሚዎች ወደ መረጃ ስርዓቱ በመደወል ተመዝገበዋል፡፡

የአርሶ አደር ምርት ክለስተር-በሰብል ምርት በአጠቃላይ የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክለስተር በአምስቱ ዋና ዋና ሰብሎች (ስንዴ፣በቆሎ፣ጤፍ፣ቢራ ገብስ እና ሰሊጥ) 2.5 ሚሊዮን ሄክታር ማሳ 3.6 ሚሊዮን አርሶ አደሮችን በማሳተፍ በሰብል ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም ውስጥ 1.3 ሚሊዮን ሄክታር ማሳ በ1.8 ሚሊዮን የአርሶ አደር ምርት ክለስተር ተሳታፊ አርሶ አደሮች የተሸፈነ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2014 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ 1.8 ሚሊዮን አርሶ አደሮችን ያቀፉ 73,300 የአርሶ አደር ምርት ክለስተር ተመስርተዋል፡፡ የግብርና ግብዓት ተደራሽ የሆኑ የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክለስተር አርሶ አደሮች፤ ለምርጥ ዘር ተደራሽ የሆኑ 2.3 ሚሊዮን ለማዳበሪያ ተደራሽ የሆኑ 3.1ሚሊዮን እና ለግብርና ግብዓት ብድር ተደራሽ የሆኑ 473,000 ናቸው፡

፡ ከዚህም ውስጥ በቅደም ተከተል 65%፣ 61% እና 67% የአርሶ አደር ምርት ክለስተር አርሶ አደሮች ናቸው፡፡

በአማራ፣ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች የቅድመ ምርት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክለስተር አርሶ አደሮች ብዛት 1.13 ሚሊዮን ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ 827,700 (73%) አርሶ አደሮች-የአርሶ አደር ምርት ክለስተር አርሶ አደሮች ናቸው፡፡

በአምስቱ ዋና ዋና የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክለስተር-የአርሶ አደር ምርት ክለስተር ሰብሎች (ስንዴ፣በቆሎ፣ ጤፍ፣ ቢራ ገብስ እና ሰሊጥ) 693,000 ኩንታል ምርት የኮንትራት ሽያጭ ውል የተፈረመ ሲሆን የምርቱ ዋጋም 1.6 ቢሊዮን ብር ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 685,400 ኩንታል ምርትና 1.58 ቢሊዮን ብር የአርሶ አደር ምርት ክለስተር ድርሻ ነው፡፡

በሩብ ዓመቱ የተከናወኑ የጥናት ስራዎች ከፊል ገበያ ተኮር የዶሮ ልማት ፕሮጀክት ዲዛይን፣ የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክላስተር የማርኬቲንግ ክፍል የትግበራ ድጋፍ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ዘርፍ አጠቃላይ አፈፃፀም የዳሰሳ ጥናት፣ የግብርና ሚኒስቴር 10X10 ፕሮግራም ዲዛይን፣ የዶሮ እርባታ ፕሮግራም ዲዛይንን ዲኤሴምቲ-ኢ በተባለ መተግበርያ የዲዛይን ሙከራ፣ የግብርና ግብዓትና አገልግሎት /AOSS የግማሽ ጊዜ ግምገማ እና የተቀናጀ የንብ ማነብ ዋጋ ሰንሰለት ፕሮጀክት/IAVCP የማጠቃለያ ግምገማ ናቸው፡፡

## 10. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 10.1. የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ

የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም የማሳደግ ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመሆን የስራ ፈላጊዎች ምዝገባና ልየታ 859,906 የታቀደ ሲሆን፤ 1,099,430 የስራ ፈላጊዎች ምዝገባና ልየታ ተከናውኗል፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ 128% ነው፡፡ በክልሎች ደረጃ ለተለየዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም የዩኒቨርሲቲና ኮሌጂ ምሩቃን እና ሌሎች ስራ ፈላጊ ዜጎችን ጨምሮ በቁጥር 1,176,211 ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ563,945 ህ/ሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 22% ነው፡፡ የስራ ፈላጊ ዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንፃር በቋሚ ብቻ በገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ በግብርና 80,936፣ በኢንዱስትሪ 20,547፣ በአገልግሎት 20,445 እና በቅጥር 33,837 በአጠቃላይ ለ155,765 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ በግብርና 64,757፣ በኢንዱስትሪ 18,569፣ በአገልግሎትና በቅጥር 42,079 በአጠቃላይ በቋሚ ወንድ 92,566 ሴት 32,839 በድምሩ 125,405 (81%) የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በጊዜያዊ ስራ ዕድል ወንድ 17,044 እና ሴት 9,137 በድምር 26,181 ሲሆን በአጠቃላይ ለ151,586 ሥራ ፈላጊዎች በቋሚና በጊዜያዊ ሥራ መስኮች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡

የገጠር ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ከማጎልበት አንፃር የመሬት አቅርቦትን በተመለከተ 11,164 ሄ/ር ለመስጠት ታቅዶ፤ 9597 (85.9%) ሄ/ር መሬት ለማስተለላፍ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የገበያ

ትስስር ለመፈጠር ብር 3,412,631,314 ለ102,692 ኢንተርፕራይዞች ለመፍጠር ታቅዶ፤ ብር 943,143,991 ድጋፍ በማድረግ የ102,692 ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ ለ2,670 ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ ለ6,624 ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ እና ለ3,935 ኢንተርፕራይዞች የኦዲት አገልግሎት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ፤ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለ317 ኢንተርፕራይዞች፣ የሂሳብ አያያዝ ለ4,068 ኢንተርፕራይዞች እና የኦዲት አገልግሎት ለ2,980 ኢንተርፕራይዞች ተሰጥቷል፡፡

የባለ-ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አሰራር ስርዓት ከማሻሻል አንፃር በሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች ለ110,299 ወጣቶችን፣ ለ77,408 ሴቶችን እና ለ239 አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በተፈጠረው የስራ ዕድል 24% ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግርን በተመለከተ ከጀመሪ ወደ ታዳጊ 5012፣ ከታዳጊ ወደ መከካለኛ 924 እና ከመከካለኛ ወደ ከፍተኛ 73 በአጠቃላይ ለ6,009 ኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር ለማድረግ ታቅዶ፣ ከጀመሪያ ወደ ታዳጊ 2,364፣ ከታዳጊ ወደ መከካለኛ 324 እና ከመከካለኛ ወደ ከፍተኛ 14) በድምሩ 2,702 ኢንተርፕራይዞች እንዲሸጋገሩ ተደርጓል፡፡

### 10.2. የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ

የሃብት ግኝትን ለማሳደግና ሃብት ለማፈላለግ 2 ፕሮፖዛሎችን ለማዘጋጀትና ሃብት ለማግኘት ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡ የሃብት ግኙቱም ከጂአይዘድ እና የልማታዊ ሴፍትኔት የፓሪስ ስምምነት ማስፈጸሚያ የሆነው ፍቃደኝነት የተመሰረተ ሃገራዊ አስተዋጾ (NDC) እና ለዘላቂ ልማት ግቦች (SDG) ያለውን አስተዋጾ ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ከ31 oct - 12 Nov ድረስ በሚካሄደው የአባል ሃገራት የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ (CO 26) ላይ ክቡር ሚንስትሩ ባሉበት የሚቀርብ አንድ ሰንድ (በቪዲዎ፣ በባነርና በብሮሸር) ተዘጋጅቷል፡፡ በአለም አቀፍ የአየር ንብረት ፈንድ (GCF) እና የማጣጣሚያና ማስተሳሰሪያ ፕሮጀክት (AF) አተገባበር በክልሎች ያለበት ደረጃ እና የተገኙ ውጤቶችን ለመከታተልና ለመደገፍ ታቅዶ፣ በአማራና በደቡብ ክልሎች እስከ ቀበሌ ድረስ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም የታዩ ክፍተቶች እንዲሻሻሉ እና መልካም ተሞክሮዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በየደረጃው ግብረ-መልስ በመስጠት ስራውን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ መገምገሚያ መስፈርት (EIS Review criteria for agricultural investment projects) እንዲሁም የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተጽዕኖ ዘገባ ለመመርመርና ለመገምገም ደረጃውን የጠበቀ የአሰራር-ስርዓት መመሪያ (standard

operating procedure/SOP for review and evaluation of EIS report) በእንግሊዝኛ የተዘጋጀውን ማኑዋል ከ GIZ ጋር በጋራ በመሆን ወደ አማርኛ የመቀየር ስራ ተሰርቷል፡፡

የዳይሬክቶሬቱን ባለሙያዎች አቅም በመገንባት ተግባሮች በተሻለ ጥራት እንዲፈፀሙ ለማስቻል የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህም በዳይሬክቶሬቱ ስር ያሉ ሁሉም (17) ባለሙያዎች በARC GIS እና R-Software ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም 4 ባለሙያዎች በሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬት እና በdata base management ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በክፍሉ ለክልሎችና በክልል ፕሮጀክታቸውን ለሚተገብሩ አካላት ኃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት ዕውን ለማድረግ የሚያስችል የማህበራዊና አካባቢ መመሪያን መሰረት ያደረገ የክሎት ስልጠና በአማራና ጋምቤላ ክልሎች ለመስጠት ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡ በዚህም በግብርናው ዘርፍ ለተሰማሩ 26 ባለሀብቶች በSECOP, CRGE strategy, climate smart agriculture ፅንስ ሀሳብ እና አተገባበር ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከፌደራል እና ከሁሉም ክልሎች ለተውጣቱ 30 ባለሙያዎች (4 ሴት) ከእንስሳት ሃብት ልማት የሚለቀቅ ሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬት በ"Tier 2" ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለ 5 ቀን ተሰጥቷል፡፡

የGCF እና AF ፕሮጀክት እየተተገበረባቸው ባሉ ክልሎች ያሉ ባለሙያዎች በተገኙበት የእቅድ አፈፃፀም ውይይትና የቀጣይ ስራዎች አተገባበር ላይ የ5 ቀን 43 (ሴት-3) ተሳታፊዎች በተገኙበት ወርክሾፕ እንዲካሄድ በማድረግ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

### 10.3. የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ

በሚንስቴር መ/ቤቱ ዉስጥ እየተገነባ ከሚገኘዉ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ጎን ለጎን የህፃናት ማቆያ ማዕከላትን በአዋጁ መሰረት በማቋቋም ወደ ስራ ለማስገባት እየተሰራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ሁሉም ተጠሪ ተቋማት የህፃናት ማቆያ ማዕከል (Childeren Care Center) እንዲያቋቁሙ የክትትልና ድጋፍ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የአርብቶ አደር ክልሎችን ጨምሮ ከየደረጃው ለተዉጣጡ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች የስራ ክፍል ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች እንዲሁም የፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞ ፈፃሚዎችና አስተባባሪዎች (በሴክተሩ ለሚገኙ የስራ ክፍል ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች ሴት 354 ወንድ 146 በድምሩ 500 እንዲሁም ለክልል፣ ለወረዳ፣ ለቀበሌ ፈፃሚዎችና የፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞ አስተባባሪዎች ሴት 50 ወንድ 60 በድምሩ 100) በስርዓተ-ፆታ ጽንሰ ሀሳብ፣ ስርዓተ-ፆታን አካቶ መስራት፣ በወጣቶች ጉዳይ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ፣ የእቀባ እርሻን በተመለከተና በሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ የስልጠና/የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ተችሏል፡፡

ሴቶችን፣ ህፃናትና ወጣቶችን አስመልክቶ በሚከበሩ ዓለም ዓቀፍና ሀገር አቀፍ ኩነቶች የግንዛቤ ማስጨባጫ መድረኮችን ለመፍጠርና ልዩ ልዩ ድጋፎችን ለማድረግ በታቀደው መሰረት የዘመን መለወጫ በዓልን አስመልክቶ ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድ ሁድ የካንሰር ህሙማን ድርጅት እንዲሁም ደብረ-ሊባኖስ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ከብር 41,725.00 በላይ የሚያወጡ የምግብና የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ለሚገኙ 11 የተቋሙ ፈፃሚዎች ከብር 22,792.00 በላይ የሚያወጡ የምግብ ዘይት፣ ዱቄትና ሌሎችም ድጋፎች ተደርጓል፡፡

የሚ/ር መ/ቤቱ የሴት ሠራተኞች ፎረምን ለማጠናከር በተያዘው ዕቅድ መሰረት ለ500 የፎረሙ አባላትና ሌሎች ሴት እና ወንድ ፈፃሚዎች (50 በመቶ ወጣቶች) በስርዓተ-ፆታ ጽንሰ ሀሳብና በሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ የስልጠና/የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ተችሏል፡፡

ለክልሎች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በታቀደው መሰረት በሚንስቴር መ/ቤቱና በክልሎች በሚካሄዱ የልማት ተግባራት ውስጥ የአርሶ/አርብቶ አደር አካባቢ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ፍትሀዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማጎልበት ከላይ እስከ ታች እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብና ሲዳማ ክልሎች ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 10.4. ምግብና ስርዓተ ምግብ

በምግብ ንጥረ ይዘታቸው የበለጸጉ እና በምርምር ተለቀው ፓኬጅ ለሌላቸው ዝርያዎች (አማራንተስ፣ ኬንዋ፣ ሲናር እና ካሚሊና) ከስርዓተ ምግብ አንጻር ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ፓኬጅ ማዘጋጀት/መከለስ በሚል ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተዘጋጅቷል፡፡ ስነምህዳርን ማዕከል ያደረገ የተሰባጠረ ምግብ አዘጋጃጀት መመሪያ (Agro-ecology based Recipe) ማዘጋጀትና በአውደጥናት ማዳበር በሚል ታቅዶ የሚለከታቸው አካላት በተገኙበት አውደ ጥናት ላይ በተገኘው ግብአት መሰረት የማዳበር ስራ ተሰርቷል፡፡

ከ2016 እስከ 2020 የተተገበረው የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ስትራተጂ የትግበራ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ጥናቱ በአማካሪ ማሰራት ይቻል ዘንድ የቅድመ ዝግጅት ቢጋር በማዘጋጀት በጋዜጣ ማስታወቂያ ለማውጣት የበጀት የማስፈቀድ ስራ ተሰርቷል፤ በኦሮሚያ፣ አማራና ሶማሊ ክልሎች በ2013 ዓ.ም. ለተካሄደው የምግብ ስብጥር ዳሰሳ የጥናት ውጤትና ትንተና ተሰርቷል፡፡ IFAD አዲስ ፕሮጀክት ለመቅረጽ በሚደረገው የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ላይ በአራቱ ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ሲዳማ) ከስርዓተ ምግብ አንጻር ያሉ ችግሮችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተለዩ ችግሮች መሰረት የፕሮጀክት መነሻ ሃሳብ ተዘጋጅቷል፡፡

የምግብና የስርዓተ-ምግብ አጋር አካላት የጋራ መድረክ (Platform) ለማደራጀት ታቅዶ በአማራ፣ ኦሮሚያ እና ሶማሊ ክልሎች አጋር አካላትን የመለየትና የአጋር አካላትን ሙሉ መረጃ የማጠናቀር ስራ ተሰርቷል፡፡

የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር መፍጠር በሚል የተቀረጸው ፕሮጀክት ወደ ተግባር ለማስገባት ድጋፍ ከሚያደርገው የጃይካ (JICA) ፕላኒንግ ሚሽን ጋር በኦሮሚያ እና አማራ ክልል ላይ የመስክ ምልከታ የማድረግ እና በተዘጋጀው የፕሮጀክት ሰነድ ላይ የጋራ መግባባት እንዲፈጠር በተደጋጋሚ የምክክር ስብሰባዎች ተደርጓል፤

የኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት አቋም (postion paper) ሰነድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማዘጋጀት በሮም (pre-summit) በክቡር የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር አማካኝነት የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት አቋም (postion paper) ሰነድ እና የምግብ ሥርዓት ረቂቅ ፍኖተ ካርታ (Ethiopia`s Food System Road map) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማዘጋጀት በኒዮርክ የተባበሩት መንግስታት (UN Food System) የምግብና ስርዓት ምግብ ስብሰባ ላይ በክቡር የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር አማካኝነት የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፤

በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የ2013 ዓ.ም አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም እና የ2014 የእቅድ ዝግጅት ላይ የምክክርና የግምገማ አውደ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ከፌዴራልና፤ ከክልል ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና አጋር አካላት 81 (70 ወ እና 11 ሴት) ተሳታፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል፤ በመድረኩም የአፈፃፀም ሪፖርቶች እና ዕቅዶች ቀርበው ውይይት ተደርጓል፡ ፡ የአውደ ጥናቱ ሪፖርትም ተዘጋጅቷል፤

ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለበጀት ዓመቱ ወጥነት ያለው ዕቅድ ማዘጋጀት እንዲችሉ የምግብና ስርዓት ምግብ ስትራቴጂው መነሻ በማድረግ ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች የመለየት ስራ ተሰርቷል፣ በተለዩት ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች ላይ ግልፅነት መፍጠሪያ ውይይት ተካሂዷል፣ በዕቅድ ዝግጅት ሂደታቸው በስልክና በኢሜይል ድጋፍ ተደርጎ ዕቅዳቸውን ለማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ እንዲልኩ ተደርጓል።

በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ከፌዴራል እስከ ወረዳ (ኦሮሚያ እና ሶማሊ) ለተቀጠሩ 28 (5ሴት እና 23 ወንድ) ባለሙያዎች እና በማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በመደበኛ ለተቀጠረ አንድ ባለሙያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአማራ ክልል ለተቀጠሩ ባለሙያዎች በወቅታዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት መስጠት ያልተቻለ ሲሆን በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል፡፡ Inclusive and Value Chain development project የበጀት ድጋፍ አማካኝነት ፕሮጀክቱ

ከሚተገበርባቸው ክልሎች ለተውጣጡ 29 (24 ወንድ እና 5 ሴት) የግብርና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፤ አትክልትና ፍራፍሬ በአነስተኛ ደረጃ ማቀነባበር ላይ ለተደራጁ ማህበራት ከሆርቲካልቸር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር በመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል ለ38 (20 ሴት 18 ወንድ) ለ3 ቀናት በተግባር የተደገፈ ሥልጠና ተሰጥቷል፤ በተዘጋጀው የከፊል አርብቶ አደሮች ሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ማሰልጠኛ ማኑዋል ላይ በጅግጅጋ ለ19 (18 ወንድ እና 1ሴት) ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል::

### 10.5. ኤች አይቪ ኤድስ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

በተቋማችን ሠራተኞች በተቋቋመው የኤድስ ፈንድ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው 11 ሠራተኞች እና ወላጆቻቸውን በኤድስ ምክንያት ያጡ 7 ህጻናት በዚህ ሩብ ዓመት 32,700.00 ብር ከኤድስ ፈንድ ወጭ በማድረግ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ በሩብ አመቱ ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝባቸውን ፈቃደኛ የሆኑ 5 ሰራተኞችን በማግኘት የስነ ልቦና የምክር ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ ኤች አይቪ በደሙ የሚገኝና የገንዘብ ድጋፍ ሲደረግለት የነበረ በሞት ምክንያት የተለየንን የተቋማችን የስራ ባልደረባን ሚስት ወደ ፈንዱ ለማስገባት ተችሏል፡፡ በሩብ አመቱ ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝ 2 (ሁለት) የተቋማችን ሰራተኞች ወደ ድጋፍና እንክብካቤው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በሩብ ዓመቱ 2,000 ኮንዶም ለማሰራጨት ታቅዶ 2016 የወንድ ኮንዶም ለተቋሙ ሰራተኞችና ለቀን ሰራተኞች ተሰራጭቷል፡፡

በሩብ ዓመቱ የስደተኛ ተቀባይ ክልሎችን ሶማሌና አፋር ክልል ግብርና ቢሮዎች እንዲሁም አዲስ አበባና ኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኤች አይቪን አካተው እንዲሰሩና በትግበራ ወቅት ያጋጠማቸውን ችግር በጋራ ለመፍታት የሚያስችል ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለ 5 ተጠሪ ተቋማት (ለፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ፣ ለግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት፣ ለቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ ለመድሀኒት መኖ ቁጥጥርና አስተዳደር ባለስልጣን እና ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻልና ማዳቀል ኢንስቲቲዩት) ስለ 2 ፐርሰንት በጀት አመዳደብና አጠቃቀም እና ስለ ኤድስ ፈንድ አደረጃጀትና አጠቃቀም በተመለከተ ከኤች አይቪ ፎካል ፐርሰኖችና ከተቋሙ አመራሮች ጋር በጋራ ውይይት በማድረግ ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለተጠሪ ተቋማት ማለትም ለቡናና ሻይ ባለስልጣን ሰራተኞች እና በስሩ ለሚገኝ ለቡና ጥራት ቁጥጥር ማዕከል ሴት 55 ወንድ 121 በድምሩ 176 ሰራተኞች መድረክ እንዲያዘጋጁ በማድረግ ለሁለት ቀናት የኤች አይቪ ሜኒስትሪሚንግና የኤድስ ፈንድን በተመለከተ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራት 2 ፐርሰንት ከስራ ማስኬጃ በጀት እንዲመድቡና ኤድስ ፈንድ እንዲያቋቁሙ ተደርጓል፡፡

### የፕሮግራም በጀት የአንደኛው ሩብ ዓመት አፈፃፀም

የፋይናንስ አጠቃቀም በሚመለከት በ7 ፕሮግራሞች በ2014 አንደኛው ሩብ ዓመት በመደበኛ 239 ሚሊየን ብር ታቅዶ 174 ሚሊየን ብር (73%) ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የካፒታል በጀት ደግሞ 3.04 ቢሊየን ብር በዕቅድ ተይዞ 2.24 ቢሊየን ብር (72.8%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛና በካፒታል 3.28 ቢሊየን ብር በዕቅድ ተይዞ 2.41 ቢሊየን ብር (73.5%) ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

| የፕሮግራም / ን. ፕ. ስም | የ2014 አመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | ክንውን | አፈፃፀም ሩብ | አፈፃፀ ም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| የመ/ቤቱስም:-የግብርናሚኒስቴር | 16,131.55 | 3,287.70 | 2414.2521 | 73.43 | |
| መደበኛ | 1,165.33 | 239.95 | **174.711** | 72.81 | 14.99 |
| ካፒታል | 14,966.21 | 3,047.75 | **2239.5411** | 73.48 | 14.96 |
| የፕሮግራምስም፡ሥራአመራርናአስተዳደር | 292.76 | 20.13 | | | |
| መደበኛ | 254.35 | 14.37 | 10.94 | 10.94 | 4.30 |
| ካፒታል | 38.41 | 5.76 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስምምነት የስርዓት ምግብ ተግባራት | 175.00 | | | | |
| መደበኛ | 254.35 | 14.37 | 0.16 | 1.11 | 0.06 |
| ካፒታል | 0.00 | 0.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የፕሮግራምስም፡የእርሻልማት | 1,854.84 | 322.43 | | 0.00 | |
| መደበኛ | 196.67 | 33.19 | **6.844** | 20.62 | 3.48 |
| ካፒታል | 1,658.17 | 289.24 | **240.86** | 83.27 | 14.53 |
| የንዑስ ፕሮግራም ስም፡እርሻ ኢንቨስትሜንት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 5.68 | 0.92 | | | |
| መደበኛ | 5.68 | 0.92 | 0.691 | 75.11 | 12.17 |
| ካፒታል | 0.00 | | | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡ ለአርሶአደሩናከፊልአርብቶአደርየግብርናኤክስቴንሽንአገ | 1,163.93 | 269.53 | | | |
| መደበኛ | 5.76 | 1.34 | 0.807 | 60.22 | 14.01 |
| ካፒታል | 1,158.17 | 268.19 | 147 | 54.81 | 12.69 |
| የንዑስ ፕሮግራም ስም፡ የዕፅዋት ምርት ጤና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት | 15.71 | 3.82 | | | |
| መደበኛ | 15.71 | 3.82 | 2.089 | 54.69 | 13.30 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የን.ፕሮግራምስም፧- የሰብል ልማት | 5.60 | 1.20 | | | |
| መደበኛ | 5.60 | 1.20 | 0.727 | 60.58 | 12.98 |
| ካፒታል | 0.00 | | | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራም ስም፡ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚሰጡ ድጋፎችን ማስተባበር | 507.22 | 22.52 | | | |

| የፕሮግራም / ን. ፕ. ስም | የ2014 አመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | ክንውን | አፈፃፀም ሩብ | አፈፃፀ ም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| መደበኛ | 7.22 | 1.47 | 1.056 | 71.84 | 14.63 |
| ካፒታል | 500.00 | 21.05 | 93.86 | 445.98 | 18.77 |
| የነዑስ ፕሮግራም ስም: እፅዋት ጥበቃ | 143.53 | 22.69 | | | |
| መደበኛ | 143.53 | 22.69 | 0.948 | 4.18 | 0.66 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራሙስም፡ የግብርናመሳሪያዎችአያያዝናአጠቃቀምለማሻሻልናአቅር | 2.62 | 0.47 | | | |
| መደበኛ | 2.62 | 0.47 | 0.207 | 44.04 | 7.90 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የፕሮግራምኃላፊ፡አነስተኛ አርሶ አደርሆርቲ ካልቸር ልማት | 4.32 | 0.85 | | | |
| መደበኛ | 4.32 | 0.85 | 0.299 | 35.18 | 6.92 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የን.ፕሮግራምስም፤የዕጽዋት ዝርያለቀቃ፣ ጥበቃ እና የዘር ጥራት ቁጥጥር | 6.23 | 0.43 | | | |
| መደበኛ | 6.23 | 0.43 | 0.711 | 165.35 | 11.41 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የፕሮግራሙ ስም፡የተፈጥሮ ሃብት ልማት እና ምግብ ዋስትና ዘርፍ | 11,506.02 | 2,494.37 | | | |
| መደበኛ | 52.94 | 11.59 | **5.07** | | |
| ካፒታል | 11,453.08 | 2,482.77 | **165.5** | 0.00 | |
| የንዑስፕሮግራም ስም፡ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም | 960.77 | 192.48 | | | |
| መደበኛ | 6.24 | 1.56 | 1.557 | 99.81 | 24.95 |
| ካፒታል | 954.53 | 190.92 | 74.119 | 38.82 | 7.76 |
| የፕሮገራም ስም ፤፡ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት | 3.02 | 0.76 | | | |
| መደበኛ | 3.02 | 0.76 | 0.533 | 70.50 | 17.63 |
| ካፒታል | 0.00 | | | | |
| የንዑስ ፕሮግራም ስም፡ የአፈር ለምነት ማሻሻያና የናሙና ምርመራና ትንተና አገልግሎት | 12.51 | 2.71 | | | |
| መደበኛ | 12.51 | 2.71 | 1.0724 | 39.65 | 8.57 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ን.ፕሮግራም ስም ፡አፈር ሀብት መረጃና ካርታ ዝግጅት | 3.56 | 0.71 | | | |

| የፕሮግራም / ን. ፕ. ስም | የ2014 አመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | ክንውን | አፈፃፀም ሩብ | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| መደበኛ | 3.56 | 0.71 | 0.527 | 74.23 | 14.80 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ን. ፕሮግራም ኃላፊ አፈር ለምነት ማሻሻያዳይሬክቶሬት | 4.08 | 0.60 | | | |
| መደበኛ | 4.08 | 0.60 | 0.827 | 137.83 | 20.29 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ን.ፕሮግራም ስም፣ አነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት | 1,507.53 | 145.15 | | | |
| መደበኛ | 4.98 | 1.30 | 0.561 | 43.12 | 11.27 |
| ካፒታል | 1,502.55 | 143.85 | 91.43 | 63.56 | 6.08 |
| የገጠር ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም | 9,000.13 | 2,148.76 | | | |
| መደበኛ | 4.13 | 0.76 | **106.422** | | |
| ካፒታል | 8,996.00 | 2148.00 | **1462.127** | 68.07 | |
| ን.ፕሮግራም ስም፣ ሰርዶ የተቀናጀ የግብርና ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት | 7.38 | 1.79 | | | |
| መደበኛ | 7.38 | 1.79 | 25.832 | 1,443.13 | 350.03 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የገጠር ስራ እድል ፈጠራ | 7.04 | 1.41 | | | |
| መደበኛ | 7.04 | 1.41 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የፕሮግራም ስም፡የግ/ቴ/ሙ/ት/ስልጠና | 546.85 | 143.47 | | | |
| መደበኛ | 516.85 | 138.97 | 30.7 | 22.09 | 5.94 |
| ካፒታል | 30.00 | 4.50 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡የአጋርፋግብርናቴ/ሙ/ት/ሥኮሌጅ | 148.34 | 34.37 | | | |
| መደበኛ | 118.34 | 29.87 | 11.63 | 38.94 | 9.83 |
| ካፒታል | 30.00 | 4.50 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡አላጌግብርናቴ/ሙ/ት/ሥኮሌጅ | 147.45 | 36.86 | | | |
| መደበኛ | 147.45 | 36.86 | 17.76 | 48.18 | 12.04 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡ አርዳይታ ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ | 118.23 | 29.55 | | | |

| የፕሮግራም / ን. ፕ. ስም | የ2014 አመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | ክንውን | አፈፃፀም ሩብ | አፈፃፀ ም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| መደበኛ | 118.23 | 29.55 | 8.3 | 28.09 | 7.02 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስ ፕሮግራም ስም፡ በገዋኔ ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ | 50.89 | 19.15 | | | |
| መደበኛ | 50.89 | 19.15 | 5.32 | 27.78 | 10.45 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡ሚዛንግብርናቴ/ሙ/ት/ሥኮሌጅ | 69.98 | 20.55 | | | |
| መደበኛ | 69.98 | 20.55 | 6.41 | 31.19 | 9.16 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡ ግብርናቴ/ሙ/ት/ሥኮሌጅማስተባበሪያጽ/ቤት | 11.96 | 2.99 | | | |
| መደበኛ | 11.96 | 2.99 | 0.47 | 15.72 | 3.93 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የፕሮግራምስም፡- የእንስሳትናዓሳሃብትልማትዘርፍ | 1,718.74 | 249.09 | 172.5 | 69.25 | 10.04 |
| መደበኛ | 25.76 | 4.60 | **7.9** | 171.77 | 30.67 |
| ካፒታል | 1,692.99 | 244.49 | **164.6** | 67.32 | 9.72 |
| ን/ፕሮግራምስም፡- መኖሃብትልማት | 4.69 | 0.77 | | | |
| መደበኛ | 4.69 | 0.77 | 4.69 | 607.51 | 100.02 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ን/ፕሮግራምስም፡- የሥጋ፣ ቆዳናሌጦሀብትልማትዳይሬክቶሬት | 2.83 | 0.32 | | | |
| መደበኛ | 2.83 | 0.32 | 0.9 | 282.13 | 31.85 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ን/ፕሮግራምስም፡- የወተት ሀብትልማትዳይሬክቶሬት | 808.97 | 161.79 | | | |
| መደበኛ | 2.90 | 0.44 | 0.43 | 98.82 | 14.82 |
| ካፒታል | 808.97 | 161.79 | 8.74 | 5.40 | 1.08 |
| የንዑስፕሮግራምስም፤-ደሮሃብትልማትዳይሬክቶሬት | 3.82 | 0.96 | | | |
| መደበኛ | 3.82 | 0.96 | 0.42 | 43.84 | 10.99 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| /ንዑስፕሮግራምስም :-የዓሣሀብትልማትዳይሬክቶሬት | 3.45 | 0.84 | | | |

| የፕሮግራም / ን. ፕ. ስም | የ2014 አመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | ክንውን | አፈፃፀም ሩብ | አፈፃፀ ም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| መደበኛ | 3.45 | 0.84 | 0.571 | 67.81 | 16.53 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ንዑስፕሮግራም፣የማርናሐርሀብትልማት | 3.15 | 0.51 | | | |
| መደበኛ | 3.15 | 0.51 | 0.427 | 83.24 | 13.57 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ን.ፕሮግራምስም፣የእንስሳትኢንቨስትመንትድጋፍ | 3.08 | 0.45 | | | |
| መደበኛ | 3.08 | 0.45 | 0.2578 | 57.29 | 8.37 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የከተሞችግብርናናእንስሳትኢንቨስትመንትድጋፍናክትት ል | 886.02 | 83.01 | | | |
| መደበኛ | 2.00 | 0.31 | 0.21 | 67.74 | 10.50 |
| ካፒታል | 884.02 | 82.70 | 155.858 | 188.46 | 17.63 |
| የፕሮግራሙስም፡- የእንስሳትናዓሣግብዓትናግብይትዘርፍ | 19.72 | 4.03 | | | |
| መደበኛ | 19.74 | 4.04 | 2.780802 | 68.83 | 14.09 |
| ካፒታል | 0.00 | 0.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምኃላፊ: የእንስሳትናዓሳግብዓትግብይትናአቅርቦትዳይሬክቶሬትዳ | 2.64 | 0.76 | | | |
| መደበኛ | 2.64 | 0.76 | 0.799541 | 105.20 | 30.29 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፣ የግብርናምርትናእንስሳትሃብትግብይትዳ/ት | 4.39 | 0.45 | | | |
| መደበኛ | 4.39 | 0.45 | 0.2 | 44.44 | 4.56 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራም፣ የግብርናግብዓትግብይትዳይሬክቶሬትዳይሬክተር | 3.58 | 0.72 | | | |
| መደበኛ | 3.58 | 0.72 | 0.22 | 30.56 | 6.15 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| ንዑስፕሮግራምኃላፊ፡ የሆርቲካልቸርኤክስፖርትልማትናግብይት | 6.22 | 1.91 | | | |
| መደበኛ | 6.22 | 1.91 | 1.15 | 60.21 | 18.49 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡ግብይትመሰረተልማትስፋፋት | 2.91 | 0.20 | | | |

| የፕሮግራም / ን. ፕ. ስም | የ2014 አመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | ክንውን | አፈፃፀም ሩብ | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|
| መደበኛ | 2.91 | 0.20 | 0.415 | 207.50 | 14.26 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የፕሮግራሙሥም፡- የእንስሳትናዓሣጤና፣ ግብዓትናምርትጥራትቁጥጥር | 192.59 | 54.17 | | | |
| መደበኛ | 99.03 | 33.19 | 16.123 | 48.58 | 16.28 |
| ካፒታል | 93.56 | 20.98 | 20.908 | 99.65 | 22.35 |
| የንዑስፕሮግራምሀላፊ፡ የኢፒዲሞሎጂዳይሬክቶሬትዳይሬክተር | 2.93 | 0.66 | | | |
| መደበኛ | 2.93 | 0.66 | 0.64 | 96.97 | 21.84 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምሀላፊየእንስሳትበሽታመከላከልናቁጥጥር ዳይሬክቶሬትዳይሬክተር | 18.78 | 14.50 | | | |
| መደበኛ | 18.78 | 14.50 | 0.641 | 4.42 | 3.41 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የን/ፕሮግራምሀላፊ፡- የኤክስፖርትቄራኢንስፔክሽንናሰርተፊኬሽንዳይሬክቶሬ | 8.91 | 2.87 | | | |
| መደበኛ | 8.91 | 2.87 | 1.47 | 51.22 | 16.50 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የን/ኘሮግራምስም፡- የኳራንታይንኢምፖርትናኤክስፖርትኢንስፔክሽንናሰር | 59.97 | 12.56 | | | |
| መደበኛ | 11.23 | 2.81 | 2.41 | 85.86 | 21.47 |
| ካፒታል | 48.74 | 9.75 | 9.668 | 99.16 | 19.84 |
| የንዑስፕሮግራም፡ቨተርነሪፐብሊክሄልዝዳይሬክቶሬት | 51.08 | 12.64 | | | |
| መደበኛ | 6.92 | 1.54 | 0.46 | 29.87 | 6.65 |
| ካፒታል | 44.16 | 11.10 | 11.24 | 101.26 | 25.45 |
| የንዑስፕሮግራምስም፡የእንስሳትልየታ፣ ክትትልናደህንነትዳይሬክቶሬትዳይሬክተር | 4.06 | 0.97 | | | |
| መደበኛ | 4.06 | 0.97 | 0.58 | 59.79 | 14.29 |
| ካፒታል | 0.00 | | 0 | 0.00 | 0.00 |
| የንዑስፕሮግራምሀላፊ፡- ሰበታብሔራዊእንስሳትጤናምርመራናጥናትማእከልሃላፊ | 46.86 | 9.97 | | | |
| መደበኛ | 46.20 | 9.84 | 10.56 | 107.32 | 22.86 |
| ካፒታል | 0.66 | 0.13 | | 0.00 | 0.00 |

## 11. የኦዲት ግኝት

በበጀት ዓመቱ በኦዲት ግኙት መሰረት መወራረድና መስተካከል ያለባቸው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 32,049,229 እንዲሁም ተከፋይ ሂሳብ 3,913,291 ብር ነው ፡፡ እነዚህን ሂሳቦች ለማወራረድ በመጀመሪያ ያለፈው ዓመት ሂሳብ በሲሰትም መዘጋት ስለላበት ሂሰቡ የተሰራ ቢሆንም በሲስተም መውጣት ስላበት በእቅድም የተያዘው በ2ኛ ሩብ ዓመት ነው ፡፡ ፡ ስለሆነም ምን ያህል እንደተወራረደ ለማወቅ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ተዘግቶና የሩብ ዓመቱ የሂሳብ ምዝገባ ተጠናቆ የሂሳብ ማስታረቅ ሥራ መሰራት ስላለበት፤ ይህም በአዲሱ ሲስተም ምክንያት ያልተጠናቀቁ ሥራዎች ስላሉና ሥራውም ትንሽ ጊዜ ስለሚወስድ በሩብ ዓመቱ ክንውን ላይ ማሳየት አልተቻለም፡ ፡ በቀጣይ ሩብ ዓመት ሪፖርት ተጠቃሎ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

## 12. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ

የሚ/ር መ/ቤቱን ቅልጥፍናና ውጤታማነት ለማሻሻል የተጀመረውን የሰው ኃይል የሪፎርም ስራ ማጠናቀቅ ሲሆን ባለፈው በጀት ዓመት ተዘጋጅት የነበረውን አደረጃjት በአገር ደረጃ ከተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አስተካክሎ ወደ ሥራ ለመግባት በአዲስ መልክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በተቻለ ፍጥነት እዲጠናቀቅ እየተሰራ ይገኛል፡፡በአዲስ በተፈጠረው አደረጃት የተዋሃዱና የተለያዩ ተቋማትና የስራ ሂደቶችን የማቋቋሚ ደንብ የማዘጋጀት ሥራ እንዲሰራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ሁለተኛው ወሳኝ የሪፎርም ሥራ የፖሊሲ ሪፎርም ሲሆን የማሻሻል ሥራው ተጠናቅ ረቂቁ ለበላይ አካል ቀርቦ እንዲጸድቅ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አኳያ ሁለት ህንፃ የማሻሻያ ስራው ተጠናቋል፤ የአዳራሽ ገንባታና የህዝብ ቤተመጽሃፍት ግንባታ ሥራ ከ70 በመቶ በላይ ተጠናቋል፡፡

## 13. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

በተለያዩ አካባቢዎች የጸጥታ ችግር በመኖሩ በእቅዱ መስረት ድጋፍና ክትትል ለማድረግ አለመቻል፣ እንደ ሀገር የመነሻ ዘር እጥረት ማጋጠሙ፣ በየኮሌጁ ከፍተኛ የሆነ የመሰረተ ልማት ችግር (መንገድ፣ መብራት፣ ውሀ፣ መማሪያ ክፍል፣ ዶርሚተሪ፣ የመምህራን መኖሪያ) ፣ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለ 150% ታክስ አለመነሳት፤የቆዳና ሌጦ ዋጋ መውደቅ፣ የውጪ ምንዛሬ እጥረት፣ በመኖና መኖ ግብዓት ላይ ያለዉ ታክስ ያለመነሳት ችግር፣ ከግርብርና ሚኒስቴር ዕውቅና ውጪ ቆዳ ከውጪ ወደ ሀገር በጉምሩክ በኩል እንዲገባ መደረግ፣ ለአነስተኛ መስኖ ግንባታ ፕሮጀክት የተያዘው በጀት በወቅቱ አለመለቀቁ ተግባራትን በድርጊት መርሀ-ግብር መሠረት ማከናወን አለመቻል፤

## 14. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

**የግብርና እድገት ፕሮግራም**

የግብርና እድገት ፕሮግራም የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ እና ገበያ ተኮር ለማድረግ ታስቦ ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስሮ የተዘጋጀና ይህንንም ግብ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ መንግስታዊ ፕሮግራም ነዉ፡፤

ፕሮግራሙ በሰባት (8) ክልሎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር (ማለትም፤- በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በትግራይ፣ በሲዳማ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በሀረሪ ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር) በሚገኙና በተመረጡ 181 ወረዳዎች እና 4181 ቀበሌዎች ዉስጥ የሚንቀሳቀስ ነዉ፡፡ በፕሮግራሙ ዘመን በድምሩ 3.7 ሚሊዮን አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.6 ሚሊዮን የሚሆኑ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች የፕሮግራሙ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በዚሁ መሰረት 1ኛ ሩብ ዓመት በ2013 ዓመተ ምህረት ግንባታቸው የተጠናቀቁ የግንባታ ፕሮጀክቶች በየግብርና ልማት ድጋፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ማጠናከር፡- በ2013 ዓመተ ምህርት የተጀመሩ የአንድ አነስተኛ የንግሥት ንብ ማባዣና ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታ፣ አንድ የፈሳሽ ናይትሮጂን ቤት እድሳት ግንባታና የሰባት ዘመናዊ የፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያ ግንባታዎች ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም በየግብርና ምርምር በኩል የአንድ የግብርና ምርምር ማእከል አፈር እና እንሰሳት መኖ ቤተ ሙከራ እድሳትና የአንድ የግብርና ምርምር ማእከል አነስተኛ መስኖ ልማት ግንባታ በ42.69 ሚሊዬን በጀት ወጪ ግንባታቸው ተጠናቋል፡፡ አአነስተኛ የመስኖ ልማትን በተመለከተ በ669.99 ሚሊዬን ብር ወጪ የ121 አነስተኛ የመስኖ አውታሮች እና ጥቃቅንና የቤተሰብ መስኖ አዉታር ፕሮጀክቶች ግንባታዎቻቸው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ በዚህ ዓመት ስራ ለማስጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በየግብርና ምርት ግብይትና የእሴት ሰንሰለት ልማት በኩልም የአንድ የከብት በረት ግንባታ ፕሮጀክት፣ የ17 የገበያ ማዕከላት ግንባታ ፕሮጀክቶች፣ የ34 የመጋዘን ግንባታ ፕሮጀክቶች እና የ11 የአነስተኛ ድልድይ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግንባታ ስራዎቻቸው በአጠቃላይ በ318.96 ሚሊዬን በጀት ወጪ ግንባታቸው እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡

## የስደተኞች ተጽዕኖ ምላሽ ልማት ፕሮጀክት

በስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት በመጀመሪያ ሩብ ዓመት  የፕሮጀክቱን አላማ ለማሳካት 4 ዋና ዋና ኮምፖነንቶች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያዉ ኮምፖነንት የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን ተደራሽነት ሲሆን  በበጀት ዓመቱ አዲስ የሚገነቡ ተቋማት ያልታቀዱ ሲሆን ከባለፈው ዓመት የዞሩት 10 ንዑሳን ፕሮጀክት ግን እንዲጠናቀቁ ታቅዷል፡፡ በዚህም 1 የሰው ጤና ማዕከል ማስፋፊያ ንዑስ ፕሮጀክት ተጠናቅቋል፡፡ ቀሪዎቹ በግንባታ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሁለተኛው ዋና ኮምፖነንት ዘላቂ የአካባቢ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ማሻሻል ኮምፖነንት ሲሆን በዚህ ሩብ ዓመቱ ባለፈው ዓመት ከፈሉት ችግኞች ውስጥ በሩብ ዓመቱ 2,850,165 ችግኞች በ1025 ሄ/ር መሬት ላይ ተተክሏል፡፡

ሦስተኛው የፕሮጀክቱ ዋና ኮምፖነንት የኑሮ መሰረት ማሻሻያ ኮምፖነንት ሲሆን በሩብ ዓመቱ በታቀደው መሰረት በ1281 አርሶ አደሮች ላይ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ26 አርሶ አደሮች ማሳ ላይ የአኩሪ አተር ሠርቶ ማሳያ ተካሂዷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 11 ዱ ሴቶች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል  የስራ እድል ፈጠራ (የገቢ ማስገኛ) ስራዎች በፕሮጀክቱ የተደራጁትንና የተጠናከሩትን የመከታተል፣ የመደገፍ እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ የመተግበር ስራ ይከናወናል፡፡

## አካታች እና ቀጣይነት ያለው የአሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት

አካታች እና ቀጣይነት ያለው የአሴት ሰንሰለት ልማት በኦሮምያ እና በደቡብ ክልሎች ፕሮጅከት የሶሰት አምት ፕሮግራም ሆኖ  ፤ በብድር የሚተገበር ነው የፕሮጀክቱ ዋና አላማ  በኦሮምያ እና በደቡብ ክልሎች  የሚግኙ ሁለት የተቀናጀ የግበርና ኢንደስትሪያል ፓርኮች ላይ   የተመረጡ የግብርና አሴት ሰንስለቶችን  ማልማት ነው። ለአሴት ሰንስልት ልማት የተመረጡት ፤በኦሮምያ ክልል ስንዴ እና ቲማቲም ሲሆን ደቡብ ክልል ላይ ደግሞ አቮካዶ እና ፓይን አፕል ናቸው። የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ፡አምራቾች፤የአርሻ ምረምር ተቋማት ፤ትንንሽ እና መካከለኛ ድርጅቶች ፤ግብአት እና አግልግሎት ስጪ ተቃማት ፤እና  ነጋዴዎች ናቸው።

በዚሁ መሰረት በዚህ   ሩብ አመት በኦሮምያ ክልል የገበሪዎች አገልግሎት ማእክል ለመገንባት የኮንትራት ስምምነት ተካሂዳል:: በዚህመ መሰረት አርሲ ኢቲያ 355,200 ብር ፡አንዲሁም  በባሌ አጋርፋ 355,200 ብር የውል ስምምነት ተፈራርመናል። በደቡብ እና በሲዳማ ክልሎች 8 ማእክላት ከሲዳማ ፡እና 7 ማእክላት ከጌዲኦ በድም  15 የዘር እና  ችግኝ ማባዣ ማአክላት ተለይተዋል፡ በሩብ ዓቱ ሪፖርቲንግ ጊዜ 15 የ አቮካዶ እና ፓይን አፕል ችግኝ ማፍያ ጣብያዎቸ ተለይተው 340,000 የአቮካዶ ችግኝ አምርተዋል። በተጨማሪም 8 ነባር ችግኝ ጣቢያዎቸን የማጠናከር ስራ ተሰርቶአል።

የ ገጠር የስራ አድል ፈጠራ ቴክኖሎጂዎችን ማስፍፍት አንጻር በኦሮምያ ክልል 89 አባላት ያሉት 9 የወጣቶች ማህበራት ተመስርተው 1,454,160.00 ብር ቆጥበዋል። በተመሳሳይም በሲዳማ ክልል እና በጌዲኦ ዞን 10 የወጣቶች ማህበራት ተመስርተዋል።

ኢንፍራስትራክቸሮችን ፡ቴክኖሎጂዎችን እና የተለያዩ ፍሲሊቲዎቸን መግንባት እና ከማጠናከር አኳያም

የኦሮምያ ፕሮጅክት ማስተባበሪያ ዩኒት ከ ኦሮምያ ክልል ፡ ዞን እና ወረዳ ሲፒኤ ጋር በመመካከር ስምንት ኮኦፐሬቲቭ ዩንየን (CU) እና ሃያ ፕራይመሪ ኮኦፐሬቲቭ (PCs) የስንዴ ማከማቻ መጋዘኖችን ለመገንባት ፡ በተጨማሪም ሰባት ፕራይመሪ ኮኦፐሬቲቭ (PCs) ለዘር ማከማቻ መጋዘን ለመገንባት የመለየት ስራ ተሰርቶል ።

በተጨማሪም በደቡብ ክልል የገበሬ ማሰልጠኛ መአከሎችን (FTCs) በፕሮጅክቱ ከተመረጡ 15 ወረዳዎቸ እና ቀበሌዎች የመለየት ተግባር ተከናውኖአል።በዚህም መሰረት ሰባ አምስት የገበሬ ማሰልጠኛ መአከሎችን (FTCs) ተመርጧል (ይህም ማልት 5 የስልጠና ማእከላት በወረዳ ማለት ነው)።

የገጠር የገበያ ማእከላትን ለመገንባት በዚህ ሩብ ዓመት በጌዲኦ ዞን አንድ አዲስ ዩኒየን ተመስርቷል, በተጨማሪም በሲዳማ ክልል 22 ቦታዎች ለPC ቢሮ ግንባታ ተለይተዋል።በሲዳማ ክልል የሃያ ሁለት ቦታዎች እንዲሁም በጌዶ ዞን አስራሶሰት ቦታዎችን ለ መገበያያ ሼዶች እና ለቢሮ የግንባታ ልየታ ተከናውናል፡በተጨማሪም ለ ፕራይመሪ ኮፕሬቲቭ ፣ለችግኝ ጣቢያዎቸ እና ለ ሪሰርች ማእክላት የሚያገሉ እቃ ግዢ ለመፈጸም የዲዛይን እና ቢል ኦፍ ካንቲቲ ስራ ከ አግሪካልቸር ትራንስፎርሜሽን ኤጅንሲ ጋር ተካሂዳል።

የብድር እና ሌሎች ፍይናንሻል ውጤቶችን ተድራሽ ለማድረግ ለእሴት ሰንሰለት ትዋናዮቸ የሚውል የተለያዩ የፌይናንሻል አገልግሎቶችን ለመስጠት ኦሞ ማይክሮ ፍይናንስ ከጌዶ ዞን እንዲሁም ሲዳማ ማይክሮ ፍይናንስ ከሲዳማ ክልል ተለይተዋል።

## የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም 1 እና 2

የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ቁጥር አንድ ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ 30 ሚሊዮን UA ወይም 43.3 ሚሊዮን ዶላር የብድር ስምምነት በ15 የአርብቶ አደር ወረዳዎች (በአንድ ወረዳ 5 ቀበሌዎች) ማለትም በአፋር ክልል 6 ወረዳዎች (አዳአር፣ አፍዴራ፣ ቡሬሙዳይቱ፣ ኤሊዳር፣ ኢረብቲ፣ ሀደሌላ) እና በሶማሌ ክልል 9 ወረዳዎች ማለትም (አራርሶ፣ ቀብሪደሀር፣ ራሶ፣ መርሲን፣ ሙባረክ፣ ቁቢ፣ ሀዲጋላ፣ ብርቆት.፣ጎልጃኖ) እ.ኤ.አ February 2013 ጀምሮ መተግበር የጀመረ የ5 ዓመት ፕሮጀክት ሲሆን አንዳንድ ስራዎች በተለይም የውሀ ሀብት ልማት ስራዎች ባለመጠናቀቃቸው እስከ ሰኔ 2014 ዓ.ም. እንዲራዘም ተወስኖ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በበጀትዓመቱ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተፈጥሮ ሀብት ልማት አስተዳደርኮመፖነነት በሱማሌ ክልል በሱማሌ ክልል ቁፋሮው ከተጠናቀቁ የውሀ ጉድጓዶች በሩብ ዓመት የአንዱ የውሀ ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ በማጠናቀቅ በጠቅላላ በ2013 የተሰሩትን ጨምሮ የ5 የውሀ ጉድጓዶች የመስመር ግንባታ ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በአፋር ክልል ዘጠኝ ቁፋሮዋቸው የተጠናቀቁ ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶችን ያሉ ሲሆን የመስመር ዝርጋታ ለማካሄድ የበጀት እጥረት በመግጠሙ ለማከናወን አልተቻለም፡፡

በሱማሌ እና በአፋር ክልል የገጸ ምድር የውሀ ተቋማት ግንባታ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን በሱማሌ ክልል የ 4 ኩሬ ግንባታ በአማካይ 75% ደርሷል፡፡ በአፋር ክልል አንድ የማይክሮ ግድብ ግንባታ

ለማካሄድ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በሩብ ዓመቱ ከተለያዩ አካላት የተነሱ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ ውይይቶችን በማካሄድ የግንባታው ዲዛይን ተከልሶ ኮንትራክተሩ እና አማካሪ ድርጅ ስምምነት ላይ በመድረስ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን ግንባታው 19% ላይ ደርሷል፡፡ በተጨማሪም በአፋር ክልል በ20014 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ ዓመት የአምስት ቢርካ ግንባታ በአማካይ 58% ደርሷል፡፡ በፕሮጀክት ዘመን አዳዲስ በተገነቡት እና ጥገና በተደረገላቸው የውሀ ተቋማት 135,701 የአርብቶአደር ማህበረሰብ እና 731,160 እንስሳት የውሀ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ማልማት እና ማኔጅመንት በሩብ ዓመቱ በአፋር ክልል አንደኛ ሩብ ዓመት 70 ሄ/ር መሬት ላይ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ዘር ልማት ለማካሄድ እንዲቻል 13.5 ኩንታል የመኖ ዘር ወደ ቦታው የማጓጓዝ ስራ ተከናውኗል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ቁጥር ሁለት ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ 28.48 ሚሊዮን UA ወይም 43.57 ሚሊዮን ዶላር የብድር ስምምነት በኦሮሚያ ስምንት እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች ክልሎች ሰባት በድምሩ በአስራ አምስት የአርብቶ አደር ወረዳዎች የሚተገበር የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ስር ያሉ ወረዳዎች አሬሮ፣ ዳአስ፣ መልካ ሶዳ፣ ዱግዳ ዳዋ እና በጉጂ ዞን ስር ያሉ ሰባ ቦሩ፣ ሊበን፣ ጎሮ ዶላ፣ ጊርጃ ተጠቃሚ አርብቶአደር ወረዳዎች ሲሆኑ የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች ክልል ደግሞ በቤንች ማጂ ዞን ስር ያሉ ሚኒት ጎልደያ እና ሚኒት ሻሻ እና ቤሮ፣ በደቡብ ኦሞ ዞን ስር ያሉ ማሌ፣ በነ ጸማይ እና በከፋ ዞን ስር ያለ ጎባ ወረዳ ተጠቃሚ አርብቶ አደር ወረዳዎች ናቸው፡፡ ከግንቦት 2007 ዓ.ም ጀምሮ መተግበር የጀመረ የ5 ዓመት ፕሮጀክት ሲሆን ለሁለት ዓመት ተራዝሞ በመተግበር ላይ የሚገኝ ሲሆን በታህሳስ 2015 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ፕሮጀክት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የተፈጥሮ ሀብት ልማት አስተዳደር በሩብ ዓመቱ አንደኛ ሩብ ዓመት በኦሮሚያ ክልል ሁለት አነስተኛ ግድቦች ግንባታ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን የአንደኛው ግድብ ግንባታ 22% ደርሷል፡፡ የሁለተኛው ግድብ ግንባታ ለማስጀመር ውሀው የሚተኛበት ቦታን በተመለከተ ከአካባቢው ህብረተሰብ ቅሬታ ስለቀረበ ሰፊ ውይይት በማካሄድ እና የዲዛይን ክለሳ በማድረግ ስራውን ለመጀመር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ግንባታው የተጀመረ አንድ የውሀ መስመር ዝርጋታ ለማጠናቀቅ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ግንባታው 100% የተጠናቀቀ ሲሆን ተጨማሪ አንድ የውሀ መስመር ዝርጋታ ግንባታ 98% ደርሷል፡፡ በደቡብ ክልል የተጠናቀቁ ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶችን የመስመር ዝርጋታ ለማከናወን በተያዘው ዕቅድ መሰረት የአንዱ መስመር ዝርጋታ ግንባታ 60% የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪው አንድ መስመር ዝርጋታ ግንባታ 20% ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በፕሮጀክት ዘመን በደቡብ ክልል አንድ ጥልቅ ውሀ መስመር ዝርጋታ የተጠናቀቀ ሲሆን ሁለት የመስመር ዝርጋታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በበጀት ዕጥረት ምክንያት የተቀሩትን ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ ለማከናወን ያልተቻለ ሲሆን ችግሩን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት እየተደረገ ነው፡፡

በሩብ ዓመቱ በኦሮሚያ 3 እና በደቡብ 2 በድምሩ 5 አዳዲስ አነስተኛ የውሀ ተቋማት ግንባታ ለማካሄድ በዕቅድ ተይዞ በኦሮሚያ ክልል አንድ ኩሬ እና አንድ ቢርካ ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን

በተጨማሪ የአንድ ቢርካ ግንባታ 98% ተጠናቋል፡፡ በደቡብ ክልል 2 ምንጭ የማጎልበት ስራ ለማከናወን በዕቅድ ቢያዝም በጀት በወቅቱ ባለመለቀቁ ግንባታው ለመጀመር ያልተቻለ ሲሆን በጀት እንደደረሰ ስራውን ለመጀመር ዝግጅቱ ተጠናቋል ፡፡

በተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ማልማት እና ማኔጅመንት  የእንስሳት መኖ እና የመኖ ዘር ልማት ማካሄድን በተመለከተ በ ሩብ ዓመት በኦሮሚያ ክልል በዝናብ 60 ሄ/ር እና በመስኖ 2 ሄ/ር በድምሩ 62 ሄ/ር መሬት ላይ የእንስሳት መኖ ለማልማት ታቅዶ በ446 ሄ/ር መሬት ላይ በማልማት 27,014 ቤል ድርቆሽ ተሰብስቧል፡፡ በደቡብ ክልል በ200 ሄ/ር መሬት ላይ በመስኖ በማልማት  1,300.00 ቤል ለማምረት ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ በኦሮሚያ ክልል ሁለት እና በደቡብ ክልል አንድ የመኖ መጋዘን  ግንባታ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል የሁለቱ መጋዘን ግንባታ በአማካይ 30% እንዲሁም በደቡብ ክልል የሚካሄደው የመኖ ማከማቻ መጋዘን ግንባታ 70% ደርሷል፡፡

የእንስሳት መሰረተ ልማት ማስፋፋት ኮመፖነንት በአንደኛው ሩብ ዓመት በኦሮሚያ ክልል አንድ እና በደቡብ ክልል አንድ በድምሩ ሁለት ተጀምረው ያልተጠናቀቁ የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ግንባታ ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ በኦሮሚያ ክልል ሁለት የገበያ ማዕከላትን ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን በደቡብ ክልል ሁለት የገበያ ማዕከላት ግንባታ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በደቡብ ክልል የሚገኙት የገበያ ማዕከላት ግንባታቸው 70% እና 45% ደርሷል፡፡ በበጀት ዓመቱ በደቡብ ክልል ጂንካ ከተማ በጥገና ላይ ያለ አንድ የእንስሳት ላቦራቶሪ ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ የጥገና ስራው 90% ደርሷል፡፡

### የክፍለ አህጉራዊ የድርቅ መቋቋሚያና የአርብቶ አደር ኑሮ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት

በአርብቶ አደሩ አካባቢ በተከታታይ የሚከሰተዉን የድርቅና የአደጋ ተጋላጭንት ስጋትን ከእለት እርዳታ ባሻገር በዘላቅ ልማት ምላሽ ለመስጠት የሚያሰችል አቅም በሁሉም ዘርፎች  በማጎልበት የማህበረሰቡን የኑሮ ዋሰትናና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ታሰቦ የተቋቋመዉ ክፍለ አህጉራዊ የአርብቶ አደር ኑሮ መቋቋሚያ ፕሮጀክት ዓላማዉ ድርቅንና ድንገተኛ አደጋን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መከላከልን መሰረት በማድረግ በአካባቢዉ ያለዉን እምቅ ሀብት /የተፈጥሮና የእንሰሳት ሀብት /ላይ ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ  በማፍሰስ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ዘላቂና አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም የ132000 የአርበቶ/ከፊል አርብቶ አደር እማ/አባወራዎች ኑሮ በማሻሻል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡

የዚሁ ፕሮጀክት ዋና ግቦች፡1ኛ የአርብቶ አደሩን የድርቅና አደጋ ተጋላጭነት ከዕለት ደራሽ እርዳታ ፍላጎት በማላቀቅ ዘላቂነት ያለዉን ኑሮአቸዉ እንዲሻሻልና የአደጋ ጉዳትን እንዲቋቋሙ የሚያሰችሉ አቅሞችን በተመረጡ የትኩረት መስኮች ላይ ልማትን በማሳደግ ኑሮቸዉን ማሻሻል፤ 2ኛ. በአፍሪካ ቀንድ ካሉት አገራት ጋር ክፍለ አህጉራዊ መንግስታት በሰላምና የጋራ የልማት ተጠቃሚነትን በጋራ ድንበሮችና ሕዝቦች መካካል ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በኦሮሚያ ክልል 6 ወረዳዎች (ተልተሌ፣ ሞያሌ፣ ድሬ፣ ሚዮ፣ ዲሎ እና ያቤሎ)፣ በአፋር ክልል 5 ወረዳዎች (አባአላ፣ ቴሩ፣ ሰምሮቢ፣ ያሎ እና አፍአምቦ)፣ በሶማሌ ክልል 6 ወረዳዎች (ሺላቦ፣ ሼኮሽ፣አዋሬ፣ ዋርዴር፣ ዱሁን እና ሞያሌ) እና በደ/ብ/ብ/ህ ክልል ( ሐመር፣ ዳሰነች፣ ሱርማ እና ኛንጋቶም) ናቸው፡

በዚሁ መሰረት በተፈጥሮ ሀብት ልማትና አስተዳደር በበጀት ዓመቱ 14 የውሃ ተቋማት ለመገንባት ታቅደው 3ቱ የተጠናቀቁ፣ 5 በቁፋሮ ሂደት፣ 2 በግንባታ ላይ ሲሆኑ 4 በጨረታ ሂደት ላይ ሲገኙ አፈጻጸሙም 67.35 ከመቶ ነው፡፡

በጋራ የግጦሽ መሬት አስተዳደር አጠቃቀምና ዘላቂነት አጠባበቅ አቅም ማጎልበት በኩል በበጀት ዓመቱ 500 ሄ/ር (150 በሶማሌ ክልል፣ 150 ሄ/ር በኦሮሚያ ክልል፣ 100 ሄ/ር በአፋር ክልል እና 100 ሄ/ር በደ/ብ/ብ/ህ ክልል) የመኖ ባንክ ለማልማት ታቅዶ በሩብ ዓመቱ በሶማሌ ክልል በበርአኖ ወረዳ 75 ሄ/ር መሬት ታርሷል፡፡ በኦሮሚያ ክልል 25 ሄክታር ያቤሎ ወረዳ መሬት ታርሶ ዘር ተዘርቷል፡፡ በአፋር ክልል በዱብቲ ወረዳ 100 ሄ/ር የመሬት ሳይት ርክክብ ስራ ተከናውኗል፡፡ የመሬት ዝግጅት ስራ ለማከናወን ማሽነሪ ቀርቧል፡፡ በደ/ብ/ብ/ህ ክልል) 80 ሄ/ር መሬት ዝግጅት ተሰርቶ 40 ሄ/ር መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡

በገበያና ግብይት ማስፋፊት በኩልም ከሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር 168 የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ማናጅመንት ኮሚቴ አባላት ለማሰልጠን ታቅዶ 84 አባላት በኦሮሚያ ክልል (6ቱ ሴቶች) ማሰልጠን ተችሏል፡፡ ይህም አፈጻጸም 72.6 በመቶ ነው፡፡ በሶማሌ ክልል 100 የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ማናጅመንት ኮሚቴ አባላት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህም 6ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ህ ክልል በሱርማ ወረዳ 7 የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ማናጅመንት ኮሚቴ አባላት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ 7ቱም ወንዶች ናቸው፡፡

የኑሮ ዘይቤ ከማሻሻል አኳያም ግብርና ሚኒስቴር አፋር፣ ሶማሌ፣ ኦሮሚያ እና ደ/ብ/ብ/ህ ክልሎች በማስተባበር ከኬንያ ጋር የተቀናጀ የክትባት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

### የእንሰሳት እና የአሳ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት

የፕሮጀክቱ የግብርና ምርትና ምረታማነትና ለመሳደግን የእንስሳትና አሳ አምራቾችንና ፕሮሰስሮችን ለመደገፈ የተቋቋመ ሲሆን 1.2 ሚሊዮን የእንስሳትና ዓሳ አምራቾችና ፕሮሰሰሮች በ58 ወረዳዎች ተተቓሚ ይሆናሉ ፡፡ በዚሁ መሰረት በፕሮጀክት በሩ ዓመቱ በምርታማ ገበሬዎችን ወደ ገበያዎች ማገናኘት ትኩረት መስክ 10560 የጋራ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች የተደራጁ ሲሆን ለእነዚህ ቡድኖች የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 2347 ቡድኖች የገበየ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡

በሁሉም ክልሊች ለሚገኙ የጋራ ፍላጎት ለተደራጁ ግለሰቦች የገበያ ትስስር ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ በደረጃ ሁለት ለተደራጁ 120 ማህበረት ሰነድ ዝግጅት እና በአፅዳቂ ኮሚቴ ማፅደቅ ስራዎች ለ89 ተሰረቷል፡፡

በእያንዳዳቸው ማለትም በኦሮሚያ 23፣በአማራ 15፣በደቡብ 11 በሲዳማ 2፣በትግራይ 4 በቤንሻጉል2፣በጋምቤላ 1፣በአጠቃላይ 58 የወረዳ አፅዳቂ ኮሚቴ በደረጃ ሁለት ለማቋቋም ታቅዶ 58 እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

የእንሰሳት እና ዓሳ ዘርፉን በቢሔራዊ ደረጃ ተቋማትን ማጠናከር በኩል የቢሔራዊ እንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ተቋም ከውጭ ለሚገቡ ጊደሮች እና ወይፈኖች ሚሆን በሆለታ የማቆያ ቤቶች በመገንባት ላይ ሲሆን ግንባታው ባለመጠናቀቁ ምክኒያት እስከ አሁን ጊደሮችን ማስገባት አልቻልንም ፡፡ አሁን ግንባታው የደረሰበት 70 ፐርሰንት ነው፡፡ ይሁንና በአዳአበርጋ ምርምር ማዕከል 200 የሃገር ውስጥ ዝርያዎችን እንዲገቡ ተደርጓል

የቻግኒ ወተት የዳልጋ ከብት ዝርያ ማሻሻያ አስመልክቶ ለዝርያ ማሻሻያው ፕሮግራም የሚውሉ፣ የእንስሳት መረጣ፤የመኖ ልማት ስራ እና የእንስሳት በረት ጥገና ስራ ተከናውኗል፡፡እንዲሁም ለዚሁ ስራ የሚውሉ የማሽነሪ ግዥ ጥያቄ፤የመኖ፤የእንሰሳት መድሃኒት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ወተት የዳልጋ ከብት ዝርያ ማሻሻያ አስመልክቶ1) የቢሔራዊ እንሰሰሳት ዝርያ ማሻሻያ እና የኢትጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በወልቂጤ ምርምር ማዕከል እንዲሁም 2) የቢሔራዊ እንሰሰሳት ዝርያ ማሻሻያ እና የኢትጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በወላይታ ሶዶ ጀርሲ ከብቶች ዝርያ ብዜት ማዕከል ውስጥ ለማካሄድ የመግባቢያ ስምምነት ተከናውኗል፡፡

የክልል የዶሮ ብዜት ማዕከላትን መደገፍ; በጋምቤላ፣በቤንሻንጉል፣በአማራ፣በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልል የሚሠሩ የመንግስት ማዕከላትን መሠረት ያደረገ ድጋፍ ለማዕከሉ ለማቅረብ የሚሰሩ የመንግስት ማባዣ ማዕከላት ልማት እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ችግሮች እና ችግሮች ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፡፡በተጨማሪም የዋጋ ተኮር ሥራው በመሠረታዊ የዶሮ እርባታ አያያዝ ስርዓት ውስጥ ለክልል ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ተጠናቅቋል፡፡

የእንሰሳት ጤና በተመለከተ የዶሮ ፈንግል በሽታ ቁጥጥር ስትራቴጅ የመጀመሪያ ድራፍት ተዘጋጅቷል የPPR monitoring assessment tools2 በመጠቀም የቦችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ ቁጥጥር እና መከላለከል እንደ ሃገሪቷ ነባራዊ ሁኔታ ታይቶ በ78 ፐርሰንት ደረጃ 2 ላይ መድረሳችንን ያየንበት ውይይት አካሂደናል፡፡

የእብድ ውሻ በሽታ ለማጥፋት እና ግንዛቤ ለመፍጠር በአርባምንጪ እና በሆሳእና ከተማ የክትባት ዘመቻ ተካሂዷል፡፡

የእንስሳት መኖ እና የግጦሽ ለማሻሻል ለእንሰሳት እርባታ ልማትሠራተኞችአቅምግንባታ-ተለይተው በተሰጡት የሥልጠና ፍላጎቶች ላይ በመኖ ምርት ላይ የአሰልጣኞች ሥልጠና ለ 42 (39 ወንዶችና 3 ሴቶች) አመጋገብ እና አርሶ አደር ልማት ተሰጥቷል፡፡

### የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም

ፕሮግራሙ በአማራ፣ኦሮሚያ ትግራይ፣ደቡብ፣ ሲዳማ፣አፋር ፣ሶማሌ ሀረር እና ድሬዳዋ ክልሎች በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር የመቋቋም አቅማቸውን ማሳደግ የተቋቋመ ነው፡፡

ፕሮግራሙ 7.8 ሚሊዮን በገጠር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የምግብ ክፍተት በመሙላት እና ተጠቃሚዎችን ቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብትን በመጠበቅ እና በመንከባከብ ረገድ ከምግብ ዋስትና ችግር በማላቀቅ በዘላቂነት የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ለማስቻል በመንግስትና በልማት አጋር ድርጅቶችድጋፍ እየተከነወነ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በሩብ ዓመቱ ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ጥሬ በገንዘብ ወይም እህል ለመላክን የምግብ ክፍተትን ለመሙላት በታቀደው መሰረት በመጀመሪያ ሩብ ከ2013 ወደ 214 በጀት ዓመት ብር 83,698,247 ተሸጋግሮ ከነበረ ውስጥ ብር 44,621,668 (53 %) ለተጠቃሚዎች ክፍያው ተፈፅሟል፡፡ በተመሳሳይም ከ2013 ወደ 2014 በጀት ዓመት የተዘዋወረ እህል 320,738.70

ኩንታል  ዉስጥ 241597.73 ኩንታል (75%)  ወደ ወረዳ ተጓጉዞ ለተጠቃሚዎቹ ተከፍሏ፡፡ ተከፍለው ያላለቁ የገንዘብም ሆነ የእህል ክፍያዎች በሀገራችን በተወሰኑ አካባቢዎች ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት  እና ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች በመሆኑ የፀጥታ ሁኔታው በተሻሻለበት አካባቢ ክፍያው የሚፈፀም ይሆናል፡፡

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ለፕሮግራሙ ቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ገንዘብ ለመላክ በታቀደው መሰረት በ2014 የ3 ወራት (ከሀምሌ 2013 እስከ መስከረም 30, 2014 ዓ.ም) ክፍያ ብር 375,569,630 ለመላክ ታቅዶ የአምስት ወራት ክፍያ ማለትም ከሀሜሌ እስከ ህዳር ወረ ክፍያ የሚሆን ብር 1,462,127,920 (389 %) ተላልፏል፡፡ ከዚህ ውስጥም ወረዳ ከደረሰው ውስጥ ወይም በመጀመሪያዉ ሩብ ዓመት መከፈል ከሚገባው ውስጥ 544,185,000 ብር 497,956,621(92%) በፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ ማኑዋሉ መሰረት ለተጠቃሚዎች መከፈሉ በክትትል ተረጋግጧል፡፡

በአዲሱ ልማታዊ ሴፍትኔት (PSNP 5) ትኩረት በማግኘት ለሰብዓዊ ድጋፍ ለሚሹ/የዕለት ደራሽ ተጠቃሚዎች ምላሽ ለመስጠት እና ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ ወረዳዎችን የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ጂኦግራፊያዊ አሻራ ተከትሎ ለመሸፈን ለማስፋፋት የዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ስራዎች መካከልም የሾክ ሪስፖንሲቭ ሴፍቲኔት ተግባራዊ ለማድርግ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳሽ ቦርድ (Dashboard) አስፈላጊ በመሆኑ በቴክኒክ ቡድን ተቋቁሞ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳሽ ቦርድ ተዘጋጅቶ የሚመለከታቸው አካላት ሁለት ጊዜ አስትያይት ተሰቶበታል፡፡

ፕሮግራሙ በሚተፈበርባቸው ወረዳዎች የተፈትሮ ሀብትን በመጠበቅና በመንከባከብ የማህበረሰቡን የወል ጥሪት በመስረራት በዘላቂነት የምግብ ዋስትና ችግርን ለመፍታትና ለመቀነስ እንዲያስችል የሚከናወኑ የማህበረሰብ የልማት ስራዎች በፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ ማንዋል መሰረት የስርዓተ ፆታ፣ ማህበራዊ ጉዳዮችን እና የስርዓተ ምግብን አካተው መተግበራቸውን ክትትል በማድረግ በማረጋገጥ የሚከናወኑ የማህበረሰብ የልማት ስራዎች ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያና ለስርዓተ ምግብ ፕሮግራም አስተዋፅኦ በሚያደርጉበት አግባብ እንዲተገበሩ በዚህም ልክ የክልሎች እቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡ ፡

ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በዋናነት ቋሚ ቀጥታ ተጠቃሚዎች እና ግዜያዊ ቀጥታ ተጠቃሚዎችን በአከባቢያቸው ከሚገኙ የተለያዩ የማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ትስስር ለመፍጠር የታቀደ ሲሆን የማህበራዊ አገልግሎቶችን መጠቀም የሚገባቸውን የፕሮግራም ተጠቃሚዎች እና ፍላጎታቸውን መለየት እና ከማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ትስስር እንዲፈጠር አመቺ አስቻይ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት  በታቀደው መሰረት በመጀመሪያው ሩብ ዓመትቅንጅታዊ ስራውን በውጤታማነት ለመተግበር የሚያስችል በግብርና ሚ/ር፣ በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር እና በጤና ሚ/ር የሚፈረም የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን ተከናውነዋል፡

### ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮግራም

ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮግራም ለመምራት እንዲረዳ የ15 ዓመት ስትራቴጂክ የኢንቨስትመንት ማእቀፍ እ.ኤ.አ ከ 2008 እስከ 2024 የሚቆይ አሰራርና ግብ አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ መግባቱ ይታወሳል፡፡ ይህ ማእቀፍ ዘላቂ የመሬት አያያዝ ስራዎችን ወጥና ተደጋጋፊ ለማድረግ እንዲሁም ውጤታማ የተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅና አጠቃቀም ልምዶችንና ሥርዓትን ለማስፋፋት እና ዋነኛ

እንቅፋት የሆኑትን ማነቆዎች በመለየትና በመተንተን 6.7 ቢሊዮን ብር ገደማ ወጭ የሚጠይቁ በ4 ዋና ዋና ኮምፖነንቶች የተጠቃለሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አቅዶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ፕሮግራሙ በሰባት ክልሎች በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ ሲዳማ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ በ271 ተፋሰሶች ዉስጥ በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ተፋሰሶች ወስጥ 900,000 ቤተሰቦች (በአጠቃለይ 4.2 ሚሊዮን ሰው) ከፕሮጀክቱ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

በዚሁ መሰረት በሩብ ዓመቱ በፕሮጀክቱ የተሠሩ የሥነ-አካላዊና ሥነ-ሕይወታዊ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ ተስማሚ ግብርና ሥራዎች በአጠቃላይ ያመጡትን አዎንታዊ ለውጥ ለመገምገም የሚያስችል ጥናት በአማካሪ ድርጅቶች እንዲካሄድ በታቀደው መሠረት ሁለት ቢጋሮች ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ ሩብ ዓመት በሲዳማ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ ክልሎችና በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልላዊ መንግሥት በመስክ ላይ የተካሄዱ መልካም ተሞክሮ ሥራ ሠነዶች ተዘጋጅቷል፡፡

የፕሮጀክቱ የአማካይ ዘመን የዕቅድ አፈፃፀም የሚገመግም ሚሽን የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ክልሎች ባለሙያዎች በማሳተፍ በጋራ በመሆን ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ ሪፖርቱም ከማኅበረሰብ ተፋሰስ አስከ ፌደራል ደረጃ የተከናወኑ ሥራዎች በየፈርጁ በማገናዝብ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ዋና ዋና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች፡ በበጀት ዓመቱ 450.38 ሄክታር (94 %) የወልና 616.77 ሄክታር (65.7%) የእርሻ ማሣ ላይ በድምሩ 1,067.2 ሄክታር (75.2%) መሬት ላይ የተለያዩ የሥነ-አካላዊ የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተስማሚ ግብርና በዚህ ሩብ ዓመቱ ዕቀባ ዕርሻ ከማስፋፋት ጋር በተያያዘ 947.5 ሄ.ር (23%) መሬት ለመሸፈን ተችሏል፡፡ ክንውኑ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ሥራው የሚካሄድባቸው አብዛኛው የንዑስ ተፋሰሶች በመኸር ወቅት የተሸፈነው ሰብል ባለመሰብሰቡ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሰብል ማፈራረቅ የሚውሉ የዘር ግብዓቶች በወቅቱ ለማቅረብ ባለመቻሉ ነው፡፡

የገቢ ማስገኛ ሥራዎች በፕሮጀክቱ ምክንያት በተለያዩ በገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተሳተፉ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ብዛት 5,282 ሲሆን አፈፃፀሙም (60%) ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ በፕሮጀክቱ ምክንያት በገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተሳተፉ ሴቶች ብዛት 2,525 ሲሆን አፈፃፀሙም (72%) ለማከናወን ተችሏል፡፡

የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር በሩብ ዓመቱ 118,771 ማሣዎች ሁለተኛ ደረጃ ሠርተፊኬት የተዘጋጀላቸው ሲሆን ይህም ከሩብ አመቱ ዕቅድ 55% ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መሬት ሠርተፊኬት የተሰጣቸው ቤተሰቦች ደግሞ 34,132 ወይም (63%) ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል 24,507 ወይም (70%) ሴቶችና ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር የያዙት ሆኖ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል፡፡ የሥራዎችን ዝርዝር ከታች ባለው ሠንጠረዥ 3 ተመልክቷል፡፡

የተሳተፋዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም

ፕሮግራሙ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/፣ሲዳማ እና ትግራይ ክልሎች የምግብ ዋስትና ችግር ባለባቸው 104 ወረዳዎች እና 157 ቀበሌዎች የሚተገበር ሲሆን ዓላማውም የመስኖ አውታሮችን

በመገንባት 18,400 ሄክታር በመስኖ እርሻ በማልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብት መራቆትን በመቀነስ፣ የግበዓትና ግብይት ስርዓት እንዲሻሻል በማድረግ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸውን 108,750 አባ/እማ ወራዎችን በምግብ እና በስርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የገቢ አቅማቸው እንዲጎለብት ማስቻል፡፡

በዚሁ መሰረት በሩብ ኣመቱ የአነስተኛ መስኖ መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት  አንጻር በበጀት ዓመት በአራቱ ክልሎች 4 የመስኖ ፓምፖች (የደ/ብ/ብ/ሕ/ 1፣ በኦሮሚያ 1፣ በአማራ 1 እና በትግራይ 1) በቻይና መንግስት ዕርዳታ) ለመገንባት ታቅዶ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ እና ኦሮሚያ ክልሎች የጥናትና ዲዛይኑን ረቂቅ ሰነድ ሪፖርት ቀርቦ እየተገመገመ ሲሆን የአማራ ክልልም በማጠናቀቅ ላይ ነው፡፡ የትግራይ ክልልን ግን በወቅታዊ ሁኔታ መስራት አልተቻለም፤በተመሳሳይም ለዘመናዊ ኩሬ ግንባታ የሚሆን ቦታ መረጣና ዲዛይን በ3ቱም ክልሎች እየተሰራ ነው፡፡

የመስኖ ተቋማት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ጥራት ማረጋገጥ አኳያ የመስኖ ተቋማቱ ጥራት የሚረጋገጠው በተሳትፎአዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም መመሪያ መሰረት ሲሆን የመስኖ ግንባታ ስራ ከመጀመሩ በፊት ሁሉም ቴክኒካዊ ስራዎች በትክክል መሰራታቸውን፣ ወጪ ቆጣቢና የማህበራዊና አካባቢያዊ ደህንነት መስፈርቶችን  ወይም መመሪያዎችን ተከትሎ ዲዛይን መከናወኑ ያረጋግጣል፡፡ በዚህ በጀት ዓመት በክልሎች 4 አነስተኛ የአፈር ግድቦችን ለመገንባት የጥራት ማረጋገጫ ቢጋር ተዘጋጅቶ ለይሁንታ ለአበዳሪ ድርጅቱ ተልኳል፡፡

በያዝነው ሩብ ዓመት በአነሰስተኛ መስኖ ግንባታ 2 ተቋማት ግንባታለማጠናቀቅ ታቅዶ የክረምት ዝናብ ወደ የዘገየባቸው አካባቢዎች የሚገኙ  የ4 የመስኖ አውታሮችን ግንባታ ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

አማራጭ የውሃ ምንጭ ለማቅረብ አኳያ  በመስኖ አውታሩ ተጠቃሚ ያልሆኑ አጎራባች አርሶአደሮችን ኑሮ ለማሻሻል የተለያዩ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎች በማቅረብ ገቢውን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ውድ ያልሆኑና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ ታስቦ እየተሰራ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በ2014 1ኛ ሩብ ዓመት 12 በፀሐይ ሃይል የሚሰሩ ፓምፖችን  ለመትከል ታቅዶ በጣለው ሃይለኛ የክረምት ዝናብ ምክንያት በተፈለገው ጥልቀት ለመቆፈር ስላልተቻለ ወደ 2ኛው ሩብ ዓመት ተሸጋግሯል፡፡

ለአርሶ አደሩ የገበያ ትስስር  ከመፍጸር አንጻር  በዚህ ሩብ ዓመት የግብርና ግብይትና ገበያ ትስስር ሥራዎች ውስጥ፡ 2 የመስኖ ግብአት ገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት ለማቋቋም ታቅዶ ክንውኑ 1 ሲሆን አፈጻጸሙ 50% ነው፡፡ እንዲሁም 3 የመስኖ ግብአት የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት ለማጠናከር ታቅዶ  ክንውኑ 1 ሲሆን አፈጻጸሙም 33.3% ነው፡፡ የ16 ማህበራት የቢዝነስ ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በሂደት ላይ ነው፡፡

## 15. ማጠቃለያ

በዓለምና በሀገራችን የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ እንዲሁም በሰሜኑ የሀገራችን የተወሰኑ አካባቢዎች የተከሰተ የፀጥታ ችግር በእርሻው ዘርፍ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመከላከል በየደረጃው የሚገኘው ባለሞያ እንዲሁም አርሶ አደሩ የኮቪድ ፕሮቶኮል ተግባራዊ በማድረግ የምርት ስራውን ከወትሮ በላቀ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በፀጥታ ችግር ምክንያት

ሊደርስ የሚችለውን የምርት ጉድለት ለመቅረፍ አንፃራዊ ሰላም ባላቸው አካባባዊዎች የምርት ጉድለቱን ማካካስ በሚያሥችል አግባብ የመኸር ወቅት የሰብል ልማት ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች የተከሰተው የፀጥታ ችግር እንዲሁም በአንበጣና መሰል ተባዮች በአፈፃፀሙ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያሳድር በቀጣይ በምርት አሰባሰብና ክምችት ወቅት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ የተፈጥሮ ሀብት ለግብርና ልማትና ትራንስፎርሜሽን ወሳኝ መሰረት በመሆኑ ሀብቱን የመጠበቅ እና መልሶ እንዲያገግም ለማስቻል ከባለድርሻና ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር በመስኖ የሚለማ መሬት ሽፋን በማሳደግ ስር ለሰደደ የምግብ ዋስትና ችግሮች የተጋለጡ የኅ/ሰብ  ክፍሎችን የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንፃር የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ሥራ ፈላጊ ዜጎችን መረጃ በማደራጀት፣በገጠር  አከባቢዎች  ጎልቶ ሚታየውን የሥራ አጥነት ተግዳሮቶችን ከመፍታት አንፃር የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በመፈፀም ለሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ረገድ በተለያዩ ገቢ ማስገኛ ሥራ መስኮች በማሠማራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ያሉ ተግባራት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## 16. አባሪ ፡ የቁልፍ ውጤት አመልካቾች ዝርዝር አፈፃፀም

**ሰብል ልማት**

| ተ.ቁ | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2013/ | የ 2014 ዕቅድ | የሩብ ዓመት ዒላማ | የሩብ ዓመት አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ሰፋፊ እርሻ ልማት** | | | | | | |
| | • በቆሎ | በሺህ ሄክታር | - | 119.5 | 119.5 | 84.79 | 71 |
| | • ስንዴ | በሺህ ሄክታር | - | 157.6 | 157.6 | 103.13 | 82 |
| | • ገብስ | በሺህ ሄክታር | - | 4.2 | 4.2 | 2.61 | 62 |
| | • ማሽላ | በሺህ ሄክታር | - | 88 | 88 | 53.7 | 61 |
| | • ጤፍ | በሺህ ሄክታር | - | 12 | 12 | 3 | 25 |
| | • ሩዝ | በሺህ ሄክታር | - | 42.9 | 42.9 | 2.9 | 7 |
| | • አኩሪ አተር | በሺህ ሄክታር | - | 36 | 36 | 28 | 78 |
| | • ቦሎቄ | በሺህ ሄክታር | - | 18 | 18 | 1 | 6 |
| | • ማሾ | በሺህ ሄክታር | - | 18.4 | 18.4 | 11 | 60 |
| | • ሰሊጥ | በሺህ ሄክታር | - | 314.8 | 314.8 | 102 | 33 |
| | • ሱፍ | በሺህ ሄክታር | - | 20 | 20 | 0.95 | 5 |
| | • ጥጥ | በሺህ ሄክታር | - | 203.9 | 203.9 | 117 | 57.38 |
| | • ቡና | በሺህ ሄክታር | - | 121.9 | 121.9 | 119.24 | 98 |
| | • ሻይ | በሺህ ሄክታር | - | 7.4 | 7.4 | 7 | 95 |

## ገበያ ተኮር የእንስሳትና አሳ ምርትና ምርታማነት

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ 2014 ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የሩብ ዓመት አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| የእንስሳት ምርት | | | | | |
| አጠቃላይ የወተት ምርት | | 7,443 | 2076.6 | 2,026 | 98 |
| የላም ወተት ምርት | ሚልየን ሊትር | 5922.7 | 1695.5 | 1773 | 105 |
| የፍየል ወተት ምርት | ሺ.ህ ሊትር | 191.9 | 48.4 | 47 | 97 |
| የግመል ወተት ምርት | ሚልየን ሊትር | 1328.4 | 332.7 | 206 | 62 |
| አጠቃላይ የቀይ ስጋ ምርት | | 422.391 | 118.3 | 139.75 | 118.13 |
| የበሬ ስጋ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 261 | 74 | 93.5 | 126.4 |
| የበግ ስጋ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 91 | 25 | 21 | 84.0 |
| የፍየል ስጋ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 69 | 19 | 24.7 | 130.0 |
| የግመል ስጋ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 1.391 | 0.3 | 0.55 | 183.3 |
| ቆዳና ሌጦ | | 16,381,470 | 3,854,615 | 4,260,000 | 111 |
| የዳልጋ ከብት ቆዳ | ቁጥር | 1,991,650 | 623,571 | 530,000.00 | 85.0 |
| የበግ ሌጦ | ቁጥር | 7,682,510 | 1,541,355 | 2100000 | 136.2 |
| የፍየል ሌጦ | ቁጥር | 6,707,310 | 1,689,689 | 1630000 | 96.5 |
| የማር ምርት | ሺ.ህ ቶን | 138 | 6.9 | 7.2 | 104.35 |
| የባህላዊ ቀፎ | ሺ.ህ ቶን | 131.9 | 5.9 | 6.12 | 103.73 |
| የሽግግር ቀፎ | ሺ.ህ ቶን | 2.2 | 0.55 | 0.57 | 103.64 |
| የፍሬም ቀፎ | ሺ.ህ ቶን | 3.9 | 0.45 | 0.51 | 113.33 |
| የሰም ምርት | ሺ.ህ ቶን | 9 | 0.45 | 0.5 | 111.11 |
| የአሳ ምርት | | | | | |
| የአሳ ምርት ከመደበኛ የውሃ | ሺ.ህ ቶን | 78 | 15 | 11.25 | 75 |
| ከአኳካልቸር | ሺ.ህ ቶን | 0.91 | 0.12 | 0.13 | 109.94 |
| የደረቀ አሳ ምርት | ሺ.ህ ቁጥር | 9.00 | 0.5 | 0.35 | 70.00 |
| በጨው የታጀሌ የአሳ ምርት | ሺ.ህ ቁጥር | 5.00 | 0.3 | 0.08 | 26.67 |
| የሚያስፈልግ የአሳ ጫጩት መጠን | ሚ. ቁጥር | 207 | 51.75 | 0.44 | 0.85 |
| አጠቃላይ የዶሮ ስጋ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 76.00 | 7.60 | 15.00 | |
| የዶሮ ምርት (ስጋ) - ስፔሻላይዝድ | ሺ.ህ ቶን | 40.80 | 4.08 | 5 | 122.55 |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ 2014 ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የሩብ ዓመት አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| የዶሮ ምርት (ስጋ) - የተሻሻለ | ሺ.ህ ቶን | 19.50 | 1.95 | 6 | 307.69 |
| የዶሮ ምርት (ስጋ) - ባህላዊ | ሺ.ህ ቶን | 15.70 | 1.57 | 4 | 254.78 |
| አጠቃላይ የእንቁላል ምርት | ሚሊዮን | 3,254.70 | 325.47 | 343.00 | 105.39 |
| የዶሮ ምርት (እንቁላል)- | ሚሊዮን | 2,926.30 | 292.63 | 240.00 | 82.01 |
| የዶሮ ምርት (እንቁላል)-የተሻሻለ | ሚሊዮን | 224.80 | 22.48 | 43.00 | 191.28 |
| የዶሮ ምርት (እንቁላል)-ባህላዊ | ሚሊዮን | 103.60 | 10.36 | 60.00 | 579.15 |
| **የእንስሳት ምርታማነት በምርት** | | | | | |
| የወተት ምርታማነት | | | | | |
| የወተት ላም ምርታማነት | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 1.55 | 1.55 | 2.3 | 148 |
| የወተት ላም ምርታማነት | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 6.74 | 6.74 | 13.30 | 197 |
| የወተት ላም ምርታማነት (Exotic) | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 13.76 | 13.76 | | |
| የፍየል ወተት ምርታማነት | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 0.5 | 0.5 | 0.32 | 64 |
| የግመል ወተት ምርታማነት | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 3 | 3 | 4 | 133 |
| የስጋ ምርታማነት | | | | | |
| የበሬ ስጋ ምርታማነት | ኪሎ/እንስሳ | 112.1 | 112.1 | 112.1 | 112.1 |
| የበግ ስጋ ምርታማነት | ኪሎ/እንስሳ | 10.8 | 10.8 | 10.8 | 10.8 |
| የፍየል ስጋ ምርታማነት | ኪሎ/እንስሳ | 8.7 | 8.7 | 9 | 9 |
| የግመል ስጋ ምርታማነት | ኪሎ/እንስሳ | 255.4 | 255.4 | 255.4 | 255.4 |
| የዓሳ ምርታማነት | | | | | |
| የአሳ ምርታማነት | ኪግ/መ.ኩ | 1 | 0.9 | | |
| አሳ የተጨመረባቸው የኩሬ ብዛት | ቁጥር | 1800 | 400 | 389 | 97% |
| **ዝርያ ማሻሻያ** | | | | | |
| አጠቃላይ የተመረተ የአባለዘር | በዶዝ | 1,400,000 | 350,000 | 345,760 | 99 |
| በኢንስቲትዩት የተመረተ አባለዘር | በዶዝ | 1,000,000 | 250,000 | 244,780 | 98 |
| በክልሎች የተመረተ አባለዘር | በዶዝ | 400,000 | 100,000 | 100,980 | 101 |
| አጠቃላይ የተሠራጨ የአባለዘር | በዶዝ | 1,200,000 | 300,000 | 198915 | 66 |
| በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨ | በዶዝ | 900,000 | 225,000 | 155,965 | 69 |
| በክልሎች የተሠራጨ የአባለዘር | በዶዝ | 300,000 | 75,000 | 42950 | 57 |
| አጠቃላይ የተመረተ ፈሳሽ | በሊትር | 385,000 | 96,250 | 77055 | 80 |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ 2014 ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የሩብ ዓመት አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|
| በኢንስቲትዩት የተመረተ ፈሳሽ | በሊትር | 65,000 | 16,250 | 14082 | 87 |
| በክልሎች የተመረተ ፈሳሽ | በሊትር | 320,000 | 80,000 | 62973 | 79 |
| የተሠራጨ ፈሳሽ ናይትሮጂን | በሊትር | 346,000 | 86,500 | 52525 | 61 |
| በኢንስቲትዩት የተሠራጨ ፈሳሽ | በሊትር | 58,000 | 14,500 | 9859 | 68 |
| በክልሎች የተሠራጨ ፈሳሽ | በሊትር | 288,000 | 72,000 | 42666 | 59 |
| **የእንስሳት ጤና አገልግሎት** | | | | | |
| የክትባት ምርት | ሚሊዮን ዶዝ | 390 | 88 | 70 | 80 |
| የክትባት አቅርቦት | ሚሊዮን ዶዝ | 352 | 79 | 44 | 56 |
| መድኃኒት(በብሔራዊ እንስሳት | ሚ/ቦላስ | 22 | 1 | 0 | 10 |
| መድኃኒት(በብሔራዊ እንስሳት | ሳቼት | | | | |
| የኤክስፖርት ቁራዎች የጤና | | | | | |
| የቅድመ እርድ ምርምራ | ሺህ ቁጥር | 1858 | 464.5 | 531.927 | 115 |
| የድህረ እርድ ምርመራ | ሺህ ቁጥር | 1838 | 459.5 | 520.078 | 113 |
| ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ ለወጭ | ቶን | 15500 | 3875 | 3,714.92 | 96 |
| ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ | ቶን | 1600 | 400 | 345 | 86 |
| ደህንነቱ እና ጤንነቱ ተሟልቶ ወደ | ዶዝ | 12000 | 3000 | 2725 | 91 |
| **የእንስሳት ሀብት ኢንቨስትመንት** | | | | | |
| በተሰጠ ኢንቨስትመንት ፈቃድ | | | | | |
| በወተት ከብት እርባታ | የማዕከላት | 675 | 175 | 147 | 84 |
| በዳልጋ ከብት ማድለብ | የማዕከላት | 494 | 50 | 35 | 70 |
| የበግና ፍየል እርባታ/ማድለብ | የማዕከላት | 83 | 10 | 8 | 80 |
| በዶሮ እርባታ | የማዕከላት | 275 | 50 | 43 | 87 |
| በንብ እርባታ | የማዕከላት | 56 | 5 | 2 | 40 |
| አኳካልቸር | የማዕከላት | 11 | 2 | 2 | 100 |
| በመኖ ልማት | የማዕከላት | 28 | 7 | 8 | 100 |
| ለገበያ የቀረበ ምርት | | | | | |
| የእርድ ፍየል | ቁጥር | 66,732 | 8,000 | 1,600 | 20 |
| የዕርድ በግ | ቁጥር | 25,206 | 4,500 | 1,300 | 32 |
| የዕርድ ዳልጋ ከብት | ቁጥር | 24,143 | 4,500 | 7,477 | 100 |

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ 2014 ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የሩብ ዓመት አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|
| የስጋ ዶሮ | ቁጥር | 129,682 | 15,000 | 26,497 | 100 |
| እንቁላል | ሚ/ቁጥር | 7 | 1 | 1 | 100 |
| ጥሬ ወተት | ሺ/ሊትር | 4,700 | 1,500 | 2 | 100 |
| ጥሬ ማር | ቶን | 88 | 10 | 8 | 76 |
| የመኖ ምርት /በቆሎ፣አኩሪ አተር፣ | ሺ/ኩ/ል | 48 | 12 | 9 | 75 |
| **የመኖ ልማት** | | | | | |
| ከሁሉም የመኖ ምንጮች | ሚ/ን ቶን | 147 | 20 | 20 | 98 |
| የተፈጥሮ ግጦሽን (Rangeland) | ሚ/ን ቶን | 45 | 4 | 7 | 168 |
| የተሻሻሉ የመኖ ዓይነቶችን | ሚ/ን ቶን | 11 | 4 | 3 | 75 |
| የሰብል ተረፈ ምርትን አሰባሰብ፣ | ሚ/ን ቶን | 65 | 3 | 3 | 83 |
| የኢንዳስትሪ (ስኳርና ሌሎች) | ሚ/ን ቶን | 7 | 2 | 1 | 73 |
| የወል ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን | ሚ/ን ቶን | 18 | 7 | 5 | 73 |
| የግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬትና | ሺ.ህ ቶን | 1,140 | 440 | 1 | >100 |
| የመኖ ዘር ምርታማነትን | ሺ.ህ ቶን | 3 | 0 | 0 | 100 |
| በሁሉም ስነ ምህዳር በመስኖ | ሂ/ር | 21,466 | 466 | 215 | 46 |
| ከሚከናወኑ የመኖ ልማት ስራዎች | ሚ/ሜ/ቶን | 3 | - | | |
| የሰብል ተረፈ ምርት መኖን | ሚ/ን ቶን | 6 | - | | |
| **የቴክኖሎጂና የግብዓት አቅርቦት** | | | | | |
| የዶሮ ሀብት ልማት | | | | | |
| አጠቃላይ የአንድ ቀን ጫጩት | ሚ/ን ቁጥር | 27 | 3 | 2 | 57 |
| የስጋ ጫጩት | ሚ/ን ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 120 |
| የእንቁላል ጫጩት | ሚ/ን ቁጥር | 6 | 1 | 0 | 40 |
| ጥምር ጠቀሜታ ያላቸው | ሚ/ን ቁጥር | 20 | 2 | 1 | 47 |
| የአሳ ሀብት ልማት | | | | | |
| ለአይቆች ምርታማነት የሚጨመር | ሚ. ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 1 |
| ለአኳ ካልቸር የሚያስፈልግ የአሳ | ሚ. ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 1 |

## የግብርና ምርቶች የወጭ ንግድ

| የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | በ2013 የተደረሰበት | የ2014 ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት | የሩብ ዓመቱ አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የተላከ መጠን** | | 572,863.1 | 659,235 | 142,153 | 172,453 | 121 | |
| ቡና | በቶን | 248,311.65 | 280,000 | 70,881 | 86,288 | 121.74 | |
| ሻይ | በቶን | 1814.46 | 1922.03 | 667 | 343 | 51.51 | |
| ቅ/ቅመም | በቶን | 12,880.25 | 14028 | 3,153 | 2,289 | 72.62 | |
| አበባ | በቶን | 101,578.88 | 118,875 | 26,830 | 27,260 | 101.60 | |
| አትክልት | በቶን | 173,115.13 | 200,768 | 29,261 | 47,352 | 161.83 | |
| ፍራፍሬ | በቶን | 35,162.81 | 43,642 | 11,361 | 8,921 | 78.52 | |
| **የተገኘ ገቢ** | | 1457.1 | 1,625.0 | 370.51 | 476.417 | 129 | |
| ቡና | ሚ/ን ዶላር | 907.035.60 | 1,014.9 | 239.84 | 327.868 | 136.70 | |
| ሻይ | ሚ/ን ዶላር | 2.9 | 3.07 | 1.13 | 0.636 | 56.28 | |
| ቅ/ቅመም | ሚ/ን ዶላር | 15.7 | 17.24 | 3.56 | 4.998 | 140.39 | |
| አበባ | ሚ/ን ዶላር | 470.6 | 508.052 | 110.05 | 122.582 | 111.39 | |
| አትክልት | ሚ/ን ዶላር | 47.5 | 65.9 | 11.3 | 15.586 | 137.93 | |
| ፍራፍሬ | ሚ/ን ዶላር | 13.4 | 15.9 | 4.63 | 4.747 | 102.53 | |

## ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

| ፕሮግራም | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | በ2013 የተደረሰበት | የ2014 ዒላማ | የአንደኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የሩብ ዓመቱ አፈፃፀም | አፈፃፀ ሙበመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተፋሰስ ልማት | ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራት የተቋቋመላቸው ተፋሰሶች | ቁጥር | | 1000 | 900 | 728 | 80.8 | |
| | የልማት ዕቅድ የተዘጋጀላቸው ተፋሰሶች ብዛት | ቁጥር | | 1800 | 900 | 728 | 80.8 | |
| | በልየ ልዩ ተከላዎች የተሸፈነ መሬት ስፋት | በሺ. ሄ/ር | | 2200 | 2200 | 2076 | 94.4 | |
| | ዘርፈ-ብዙ ጥቅም የሚሰጡ የዕፅዋት ችግኞች ብዛት | ቢ/ን ቁጥር | | 6 | 6 | 6.7 | 111.66 | |
| መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም | የተለካ ማሳ ብዛት | ቁጥር (በሚሊዮን) | | 2.6 | 0 | 0.503 | | |
| | የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ተጠቃሚዎች (አባወራ/እማወራ) | ቁጥር (በሚሊዮን) | | 0.743 | 0.286 | 0.088 | 30.77 | |
| | አባወራ | ቁጥር (በሚሊዮን) | | 0.52 | 0.2 | 0.062 | 31 | |
| | እማወራ | ቁጥር (በሚሊዮን) | | 0.223 | 0.086 | 0.026 | 30.23 | |
| | የተሰራጨ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ብዛት (በማሳ) | ቁጥር (በሚሊዮን) | | 2.6 | 1 | 0.309 | 30.9 | |
| አነስተኛ መስኖ ልማት | ሀ. ያደገ የመስኖ ሽፋንና አጠቃቀም | | | | | | | |
| | ለመስኖ ልማት ዝግጁ የሆነ የመሬት ስፋት | በሽህ ሄ/ር | 846.77 | 37.8 | 1.36 | 0.57 | 41.91 | የዝናብ ወቅት |
| | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር | በሽህ ቁጥር | 4374.00 | 298.30 | 29.83 | 1.28 | 4.30 | የዝናብ ወቅት |
| | ሐ. የተስፋፋ የመስኖ መሰረተ ልማት | | | | | | | |
| | በማህበረሰብ የሚተዳደሩ አዳዲስ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ብዛት | ቁጥር | 597 | 197 | 10 | 9 | 91 | |
| የአፈር ለምነት ማሻሻያ | ከከፋ የአፈር አሲዳማነት ያገገመ መሬት ስፋት | በሄ/ር | | 72,000 | 0 | 9058 | 0 | |
| | ከከፋ የአፈር ጨዋማነት ያገገመ መሬት ስፋት | በሄ/ር | | 3,450 | 0 | 0 | 0 | |
| | የአፈር ጨዋማነት ካርታ የተዘጋጀላቸው ወረዳዎች ብዛት | ወረዳ | | 15 | 0 | 0 | 0 | |
| | በማንጣፈፍ የለማ ኮትቻ አፈር | በሄ/ር | | 650,000 | 550,000 | 523,415 | 95 | |

ግብርና ምርምር

| ተ.ቁ | ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2013/ | የ2014 ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የሩብ ዓመት አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምርምር ጥናቶች | ቁጥር | 2,417 | 2,584 | 2,224 | 2,088 | 94 |
| 2 | የምርምር ውጤቶች | | | | | | |
| | ቴክኖሎጂ | ቁጥር | 107 | 133 | 8 | 8 | 100 |
| | መረጃ | ቁጥር | 415 | 358 | 16 | 17 | 100+ |
| 3 | ቴክኖሎጂ ብዜት | | | | | | |
| | አራቢ ዘር (የሰብል ዝርያዎች) | ኩንታል | 1,985.42 | 1,352 | 50.4 | 38.9 | 77 |
| | | ቁርጥራጭ | 371,200 | 372,200 | - | - | - |
| | | ችግኝ | 11,000 | 91,950 | 2,500 | 13,490 | 100+ |
| | | ቀንበጥ | - | 22,000 | - | - | - |
| | ቅድመ-መስራች ዘር (የሰብል ዝርያዎች) | ኩንታል | 7,884 | 9,539.22 | - | 0.4 | 100+- |
| | | ቁርጥራጭ | 45,000 | 8,152,000 | - | - | - |
| | | ችግኝ | 232,500 | 24,000 | - | - | - |
| | | ግንጠይ | - | 1,000.00 | - | - | - |
| | መስራች ዘር (የሰብል ዝርያዎች) | ኩንታል | 700.8 | 7,029.35 | 60 | 16 | 27 |
| | | ቁርጥራጭ | - | 670,000 | - | 3,200.00 | 100+- |
| | | ችግኝ | 1,025,600 | 913,850 | 58,350 | 51,693 | 89 |
| | | ግንጣይ (sucker) | - | 62,100 | 600 | 600 | 100 |
| | የእንስሳት መኖ ዝርያዎች | ኩንታል | 465.52 | 589.03 | 11.5 | 5.28 | 85 |
| | | ቁርጥራጭ | 60,500 | 122,000 | 3,000 | 2,500 | 83 |
| | | ችግኝ | 147,700 | 25000 | 25000 | 38500 | 100+- |
| | | ዝንጣይ | 5,315,000 | 5,385,000 | 1,155,000 | 4,175,000 | 100+ |
| | | ጉንቁል (tiller) | - | 200,000 | - | - | - |
| | | እጅብ | - | 702,000 | - | - | - |

| ተ.ቁ | ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2013/ | የ2014 ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የሩብ ዓመት አፈፃፀም | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | (clump) | | | | | |
| | ጊደሮች | ቁጥር | 120 | 160 | 46 | 45 | 99 |
| | በጎች | ቁጥር | 270 | 320 | 205 | 120 | 59 |
| | ኮርማዎች | ቁጥር | - | 25 | 5 | 5 | 100 |
| | የዶሮ ጫጩት | ቁጥር | 409,000 | 423,000 | 80,000 | 8,358 | 10 |
| | የዓሣ ጫጩት | ቁጥር | 1,100,000 | 1,150,000 | 190,000 | 162,300 | 85 |
| | እንቁላል ጣይ የሐር ትል | ቁጥር | 1,500 | 1,550 | 500 | 800 | 100+ |
| | ፍየል | ቁጥር | - | 100 | - | - | - |
| | እናት ንብ | ቁጥር | - | 70 | 35 | 35 | 100 |
| | የወተት ላሞች | ቁጥር | - | 230 | 70 | - | - |
| | የራይዞቢያ ሕያው-ማዳበሪያ (ባዮፈርቲላይዘር) | ፓኬት | 10,000 | 7,000 | 1500 | 1548 | 100+ |
| | የቨርሚ ኮምፖስት ትል | ኩንታል | 1 | 2 | 0.5 | 0.81 | 100+ |
| | ቨርሚ ኮምፓስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) | ኩንታል | 20 | 30 | 7.5 | 17.75 | 100+ |
| | የቅድመ-ምርትና ድሕረ- ምርት የግብርና መሳሪያዎች | ቁጥር | 545 | 203 | 20 | 20 | 100 |
| 4 | **ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ** | የተሳታፊ ቁጥር | 38,687 | 30,883 | 9,878 | 9,500 | 96 |
| 5 | **ቴክኖሎጂ ማስፋፋት** | የተሳታፊ ቁጥር | 50,232 | 20,914 | 8,411 | 11,802 | 100+ |
| 6 | **የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ስልጠና** | የተሳታፊ ቁጥር | 45,112 | 60,963 | 10,247 | 10,481 | 100+ |

### ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፋትና ውጤታማ ማድረግ

| ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | | መለኪያ | የ2014 ዕቅድ | የአንደኛ ሩብ | የአንደኛ | የሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት | | ቁጥር | 1000 | 100 | 363 | >100% |
| ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከርና ማዘመን | | ቁጥር | 21,058 | 2,106 | 410 | <100% |
| የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባለት ዕድገት በገጠር | | በመቶኛ | 48 | 45 | 48 | >100% |
| የላቀ አገልግሎት የሚሰጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት | | በመቶኛ | 45 | 43 | 45 | >100% |
| የኅ/ሥራ እና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ በግብርና ዘርፍ ላይ | | በመቶኛ | 15 | 11 | 11 | >100% |
| የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትን ማሳደግ | | | | | | |
| የአፈር መዳበሪያ አቅርቦት | | በመቶኛ | 98.5 | 9.83 | 33 | <100% |
| በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚባዛ ምርጥ ዘር መጠን | | በቶን | 38,600 | 3,860 | | ሪፖራቱ |
| የፀረ-አረም፣ የፀረ-ተባይ እና በሽታ ግብዓቶች አቅርቦት | | በቶን | 581 | 58.1 | - | |
| በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቀርብ የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት እና | | በቁጥር | 125 | - | - | - |
| የኅ/ ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ግብይት ማሳደግ | | | | | | |
| የኅ/ሥ/ማህበራት የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይት መጠን በቶን | | በቶን | 1,680,000 | 168,000 | 66,293.80 | <100% |
| ኅ/ሥራ ማህበራት ግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት መጠን በቶን | | በቶን | 16 | 2,301.77 | 5,175 | >100% |
| ኅ/ሥ/ማህበራት ግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት በዶላር | | በዶላር | 168,235,294 | 16,823,529 | 23,959,685 | >100% |
| የኅ/ሥ/ማህበራት የእሴት መጨመር እና መሰረተ-ልማት ግንባታ | | | | | | |
| በግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙ በግብርና ምርት ማቀነባበሪያ | | በቁጥር | 111 | - | - | - |
| የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ማዕከላት ግንባታ | | በቁጥር | 2 | - | - | - |
| የኅ/ሥራ ማህበራት የግብይት መረጃ ማዕከላት ማቋቋም | | በቁጥር | 8 | 2 | - | - |
| የኅ/ሥ/ማህበራትን የፋይናንስ ተደራሽነት ማሳደግ | | | | | | |
| ከአገራዊ የግለሰብ ቁጠባ (House hold saving) ውስጥ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ | | በመቶኛ | 7 | - | | በጥናት |
| የሚሰበሰበው የቁጠባ | | በብር | 3 | 0.28 | 469,818,73 | >100% |
| የሚሰጥ ብድር | | በብር | 3 | 0.28 | 411,437,91 | >100% |
| የሥራ ዕድል ለዜጎች መፍጠር | ቋሚ የሥራ ዕድል | በቁጥር | - | - | | |
| | ጊዜአዊ የሥራ ዕድል | በቁጥር | 1,1200,000 | 112,000 | 84,861 | <100% |